

# ሳሚቱ እምቧ ትላለች

## ህብረት

## ታደሰ ሻንቆ

***ነሃሴ 1999***

# ማውጫ


1. መግቢያ ---------- 3

2. የአስተሳሰብና የአተያይ ችግር ---------- 3
   - አሮጌነት፣ጥራዝነጠቅነትና ቅጂነት ---------- 3
   - በተጻራሪነት መተያየት ---------- 7
   - የጠላትነት ፖለቲካ ውጤት ---------- 8
   - በልማትና በለውጥ ላይ ማኩረፍ ኪሳራው ለራስ ---------- 12
   - ብሄርተኝነትና ኢብሄርተኝነት ---------- 15
     - ጥንተኝነት የትምክህት ጥሬ ሀብት ---------- 16
     - ብሄርተኝነትና አዳላጭነቱ ---------- 19

3. የመፍትሄ አቅጣጫዎች ---------- 23
   - ህብረብሄራዊ አደረጃጀት ---------- 23
   - የታደሰ ኢትዮጵያዊነት ---------- 25
   - ልብ እንግዛ ---------- 29

4. መደምደሚያ ---------- 33

# 1. መግቢያ

በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ህይወታችን ረገድ ተወርዋሪ ለውጥ ማምጣት የወቅቱ ቁልፍ ጉዳይ ከሆነ ውሎ ቢያድርም ብዙም የጎላ እርምጃ አልታየም። ለዚህም ሁለት ዋና ችግሮችን መጥቀስ ይቻላል።

ኣዲስ ለውጥና ግንባታ ብዙ ጊዜ ሲሆን እንደታየው ኣስቀድሞ የኣስተሳሰብና የኣመለካከት እርሾውን ይደግሳል። አሮጌ ኣስተሳሰቦችን የሚበጣጥስ የኣዲስ ንቃትና የተሃድሶ እንቅስቃሴ ያቀጣጥላል። ይህ በኢትዮጵያ ኣንድ ኣብይ ጉድለት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዥነት የኢትዮጵያን ህዝቦች ኣጠቃላይ ይሁንታ ለማግኘትና የምልኣተ ህዝብ የለውጥ ማእበል ለማስነሳት የሚያስችል የፖለቲካ ተቀባይነት መታጣት ሁለተኛው ችግር ነው።

ይህ መፅሃፍ እነዚህን ችግሮች ነካክቶ ባለንበት ሁኔታ ቢያንስ በእጅ ያለ የማቃለያ መላ ለማስታወስ ይሞክራል።

# 2. የኣስተሳሰብና የኣተያይ ችግር

ዘመኑ የእውቀትና የመረጃ ኣቢዮት እንደመሆኑ በለውጥ ተፀናዋችነትና በልሽቀት ላይ ውጊያ ለመክፈት ከመቼውም ዘመን የበለጠ የተመቸ ነው። ውጊያው የግድ የዲሞክራሲን መሟላት ቅድመ ሁኔታ የሚያደርግ አይደለም። ከ1983 ወደዚህ፣ ቢጠብም ቢሰፋም ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ሃሳብን የመግለፅ እድል ተከፍቶ የነበረ ቢሆንም የኢትየጵያ ዘመነ ተሃድሶ መወለጃ ሊሆን አልቻለም። ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያ ምሁራን (ኣዲስ ነገር ያመጡ የመሰሉትም ጭምር) ያሮጌ ኣስተሳሰብና የግልብነት ሰለባዎች ነበሩ።

### አሮጌነት፣ ጥራዝ ነጠቅነትና ቅጂነት

በ1960ዎች፣ በተለይ የ1966 አብዮትን ተከትሎ፣ አዳዲስ አስተሳሰቦች የኢትዮጵያን ማህበራዊ ህሊና ነቅንቀው ነበር። ሆኖም በኢትዮጵያ ከነበረው ህይወት ጋር የሚስተጋበር ለውጠኝነት ያስገኛቸው አልነበሩም። ከዚህ ይልቅ በአለም ሲነፍስ በነበረው ሶሻሊዝም ርእዮት ከመጠመቅና የዚያ ርእዮት ሰባኪና ተሰባኪ ከመሆን የመጣ ነበር። የኢትዮጵያን ሶሲዮ ኢኮኖሚያዊ ባህርያትን መሰረት አድርጎ ለለውጥ ከመጎዝ ይልቅ በመፅሃፍ መጠጣ የተገኘ የአምስት ስርአት መዋቅርንና የመደቦችን ትንታኔ በኢትዮጵያ ላይ የመለጠፍ ግልብነት ችግር ሲፈጥር ታይቷል። ሰባኪነቱም ተሰባኪነቱም ህልመኝነትና ፋኖነቱም ተካዚዶ መራራ ልምድ፣ ውርጁ ስርአትና አስተሳሰብ ጥሎ አልፏል።

ከደርግ መደላደል በኋላ እስከ 1983 አካባቢ ህወሃት ይዞት የነበረው የማርክሳዊ-ሌሊናዊነትና የላባደራዊነት ቅብጥርጥር የሞተን ከማስነሳት ልፋት የማይለይ በመፅሃፍ መጣጭነትና በተውሶ ርእዮት አምላኪነት የመታወር ምርጥ መገለጫ ነበር።

የብሄርተኛ ትጥቅ ትግሎች በኢትዮጵያ አጀማመር በጊዜው በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና በእስያ የነበረው የሃርነት ትግልና የፋኖነት ንፋስ ያነሳሳው እንደነበር ሁሉ የብሄር ብሄርሰብ ፅንሰሃሳቦችና የእስከመገንጠል መብት አስተሳሰብም ከኢትዮጵያ ህዝቦች ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታ የመነጩ ሳይሆኑ ከማርክሳዊ-ሌኒናዊ አብዮታዊነት የተለቃቀሙና ለጠባብ የስልጣን ፍላጎቶች ማሞያ ሲሰራባቸው የቆዩ፣ በኋላም

ከክልልተኝነት ወደ ጠቅላይ ገዢነት የተሸጋገረው ህወሃት ለጠቅላይ አገዛዙ መሰወሪያ ቢሆነኝ ብሎ የተገለገለባቸው ናቸው:: የብሄር/ብሄረሰብ ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝቦች አጠቃላይ የዲሞክራሲ ጥያቄ አካል እንጂ በተገላቢጦሽ የሁሉ ነገር መፍቻ ሆኖ አያቅም:: አሁን አይደለም:: የመገንጠል ጥያቄ የጥቂቶችና የርእዩት ኮራጆች ችግር እንጂ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ችግር አልነበረም:: ዛሬም አይደለም::

የ«ብሄር»ና የ«ብሄረሰብ» ፅንሰሃሳባዊ ልዩነት ከጆሴፍ ስታሊን  የተቀዳ ነው:: በዚሁ መሰረት ሁለቱም  በታሪካዊ ልውጠት የተገኙ የጋራ ባህል/ ስነልቡናና የጋራ ቋንቋ ይዞ በጋራ መልክአምድር ውስጥ የመኖር ፀባዮች የሚታዩባቸው ሲሆኑ፣ ብሄር ግን የካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ትስስርን የሚጨምር ነው:: የኛ ፖለቲከኞች በእነዚህ መመዘኛዎች የኢትዮጵያን ህዝቦች ባህርይ ሲለኩ መለኪያና እውነታ አልገጣጣም ይላሉ:: አንድ ቋንቋ በሚናገር ህዝብ ውስጥ የተለያየ የባህል ይዞታ ስፍራ ለይቶ ይገኛል:: አንድ ወጥ የቦታ አያያዝን ለማግኘት ሲለፋ ሌላ አይነት የህዝብ ስብስብ ተሰንቅሮ ይገኛል:: ከሰሜን ሸዋ ተነስቶ ወደላይ ቢወጣ ኦሮሞው አማራውና ትግሬው ከቋንቋ በስተቀር በብዙ ነገር ተመሳስሎ ይገኛል:: የከረዩው ኦሮሞ በመሃልና በምራብ ካለው ኦሮሞ ይልቅ አፋሩን ይመስላል:: ወደ ደቡብ ምስራቅ ወረድ ሲሉ ኦሮሞው፣ ኣደሬው፣ ሶማሌውና ሌላ ብሄር መጡ ውጥንቅጥ በሃረር ልጅነት በሚገለፅ መወጋገንና መላላስ ተያይዘው እናገኛለን:: የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩት የጉራጌ ማህበረሰቦች (የሃይማኖት ልዩነት ኖሮም እንኳ) አንድ ነን የሚያሰኛቸው የኣኗኗር፣ የተጣጣሪነት፣ የስራ ወዳድነትና የስነልቦና ተመሳሳይነት ኣላቸው:: ዛሬ «የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች» እየተባሉ የሚጠሩትንም ሆነ ሌሎች ትንንሽ ማህበረሰቦችን ከ«ብሄሮች ሉኣላዊነት»ና የመገንጠል መብት አስተሳሰብ ጋር  ልናዛምድ ብንሞክር በኣያሌ ጎጦች ኣዙሪት ውስጥ መግባት ይሆናል:: የሆነ ሆኖ የኢትዮጵያን ህዝቦች ኣይነተኛ ባህርይ በደንብ የተረዳ ኣጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥ ሳይቻል፣ የስታሊን መስፈርትም እንዳለ ተይዞ፣ አንዱ በኢትዮጵያ ብሄረሰብ እንጂ ብሄር የለም ሲል፣ ሃገረ ብሄር የመሆን ፍላጎቱ እንዳይቀርበት የፈለገ ደግሞ የለም ብሄር ኣለ እያለ ቆይቷል:: ዛሬ ባለንበት ወቅት ኣንዱ ህዝብ «ብሄር» ሌላው «ብሄረሰብ» እየተባለ የሚጠራበት መመዘኛ ከፅንሰሃሳባዊ ኣመጣጡ ጋር ምን ያህል ልዩነትና ኣንድነት እንዳለው ኣይታወቅም:: የኢትዮጵያን ህዝቦች ማህበራዊና ስነልቦናዊ ኣቀነባበር በደንብ ያነጠረ የማህበረሰብ ኣፈረራጅ ግን እስካሁን የለም::*

ለሰዎች ማህበረሰባዊ መወራረስና የኣብሮነት ስነልቦና ቦታ ባልሰጠ ግልብ መመዘኛ ፖለቲከኞች ከዚህ እስከዚህ ኦሮሞ፣ከዚህ በመለስ ጉራጌ/ኣማራ ወዘተርፈ እያሉ የተላላሱ ማህበረሰቦችን ቆርጠዋል ወይም ወገንህን ፈልግ የማለት ያህል ረብሸዋል:: ኣሁንም ማህበረሰባዊ ቅንብርና ባህርይ በሂደት የሚለወጥ መሆኑን ያልተረዳ ኣመለካከት ችግር እየሆነ ነው:: ሊቆምና ድንበር ሊበጅለት የማይችለውን ማህረሰባዊ እንቅስቃሴና የመላላስ ሂደት በወሰን ለመለየትና ባለበት እንዲረጋ ለማድረግ ይሞከራል::

ኣንዳንድ ታሪክ ኣወቅን ባዮች በሚኒልክ የተጠቃለለች ኢትዮጵያን መፈጠር የብሄር ብሄረሰቦችን የነፃ ሃገርነት እድገት በመቶ ኣመት ያሳጣ ማለታቸው የቆየና ዛሬም የሚሰማ ቢሆንም ከእውነትነት ይልቅ ምኞታዊነት የሚያጠቃው ኣስተሳሰብ ነው:: በዛን ጊዜ «ብሄሮች»ን በየበኩል ነጻ ሃገር ወደመሆን የሚወስድ ታሪካዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ሁኔታ ፈፅሞ ኣልነበረም:: በፍፅማዊ የስልጣን ይዞታዎች ውስጥ በካፒታሊዝምና በከበርቴው ኣዲስ እድገት ፊዩዳላዊነትን ሲበጣጥሱ ኖሮ ከኣሮጌ ቀፎ የመውጣት ኣይነት ባህርይ የታየበትን የኣውሮፓ ብሄራዊ መንግስታት ኣፈጣጠር ታሪክን ለኢትዮጵያ መመኘት ሰማይና ምድርና ከማገናኘት የማይሻል ነው:: ታሪክ

---

* በቋንቋ ቤት ህዝቦችን ለመግለፅ ያህል ከ«ብሄር»/«ብሄረሰብ» አንዱን መጠቀም የሚቻል ቢሆንም ቅር የሚለው እንዳይኖር ሁለቱንም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የአንድ መጣሪያ ያህል እጠቀምበታለሁ::

በሄደበት ጎዳና ላይ ወደሁዋላ እያዩ ምኒሊክ እንዲህ ባያደርግ ኖሮ ብሎ ማሰብ የሰው ልጅ እሳትን ባያገኝ ኖሮ መዳብና ብረትን ኣቅልጦና ጦር ሰርቶ ባልተዋጋ ነበር ብሎ የመቆጨትን ያህል ከንቱ ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ የራሱ ልዩ ኣካሄድና ፀባይ ያለው ነው። በሃገረ ኢትዮጵያ ግንባታ ውስጥ ታላቅ ሚና ያለውን የኦሮሞ ህዝቦችን ስርጭት እንውሰድ። የኦሮሞ ጎሳዎች ባንድ ጋብቻ መወሰንን ግድ ባላደረገ የትዳር ሁኔታ፣ ከተወላጅ እኩል ባለመብት በሚኮንበት ጉዲፈቻና ኦሮሞ ያልሆነን ወደራሳቸው በመቀላቀል ዘይቤያቸው ቁጥራቸው የሚበራከት ነበር። እንቅስቃሴያቸውም በቁጥር መበራከት በሚቀሰቀስ ሰፊ የመሬት ፍላጎትና ኣንድ የገዳ ዘመን ካስገኘው መሬት አልፎ ይዞታን የማስፋት ውስጣዊ ግፊት ነበሩት። የሰሜንና የደቡባዊ ገዢዎች የበላይነት ትግል ላይ እየደረሰ የነበረውን የሁለት በኩል መዳከም እያስተዋሉና የበኩላቸውን ምት እያሳረፉ አጥለቅላቂ እንቅስቃሴ ወደምእራብ፣ ወደመሃል፣ ወደምስራቅና ወደሰሜን እስከትግራይ ድረስ አድርገዋል። የተራዘመ የማስቆም ትግል ባይገጥማቸውና በራሳቸውም ላይ ማህበራዊ ልውጠት ባይደርስ ኖሮ እንቅስቃሴያቸው ኤርትራንም የሚሸፍን በሆነ ነበር።

ከላይና ከታች የነበረው የሁለት በኩል የበላይነት ትግል ዘረፋና ማስገበር ከሚያስገኘው የሲሳይ ጥቅም ጋር የተያያዘ ከመሆኑ ሌላ፣ ከሞላ ጎደል የበላይነትን ይዘው የመጡት የሰሜኑ ገዢዎች እንደገዢነት-መኳንንትነት ደረጃቸው የነበራቸው የጋሻጃግሬ ብዛት፣ የዘምቶ ኣስገባሪነትና የምርኮ ኣፋሽነት የኣኗኗር ባህሪያቸው በየነበሩበት ተወስኖና ተቻችሎ ከመኖር ጋር የሚቃረን፣ መዋዋጥንና የሰፊ ግዛት መፈጠርን የሚጠይቅ ነበር። ምኒሊክ መደምደሚያ ሆነ እንጂ የመስፋፋቱ ትግል ኣዲስ ኣልነበረም። የምኒሊክ ከሌሎቹ ነጋሲያን ሁሉ የተረገመና «የብሄርች» ፀር ሆኖ ሳይሆን የሃይል ብልጫ ኣግኝቶ የፈፀመውን ሌላውም ነጋሲ/ኣሚር ብልጫ ኣግኝቶ ቢሆን ኖሮ ወደሁዋላ የማይልበት ተግባር ነበር።

ይህንን ሁኔታና የውጪ ወራሪዎች/ቅኝ ገዥዎች ይፈጥሩ የነበረውን ተጨማሪ ጫና ያላገናዘቡ፣ በዘመነ መሳፍንት ተፈጥሮ የነበረውን ቁርጥራጭነት ከምእራብ አውሮፓ የብሄራዊ መንግስታት ኣፈጣጠር ጋር የሚያምታቱና እያንዳዱ ቁራጭ ግዛት ነፃ ሆኖ ቢቀጠል ኖሮ ብለው የሚቆጩ ግልቦች እንዳልታጡ ሁሉ በዛሬው የ21ኛው ክፍለዘመን ልዩ አለማዊ ሁኔታ ውስጥ ተቀምጠው ለኢትዮጵያ አሮጌ መፍትሄ የሚያስቡላት የኋሊት ተጓዦች ኣሉ። እስከኣሁንም ዘመኑንና የኢትዮጵያን ህዝቦች እውነታ በትክክል የተረዱ አይመስሉም። አንዳንዶቹ የቅኝ/የመነጠል ጥያቄ ሲሉ ይኸው ግማሽ ምእት አመት ሊሞላቸው ጥቂት ነው የቀራቸው። ዛሬ በሃገራዊ ገዥነት ላይ ያለው ህወሃትም የተጓዘበትን ክልልተኛነት ገና አራግፎ ያልጨረሰ ነው።

ወያኔ/ ኢህአዴግ ያባዛው ብሄርተኛ አስተሳሰብ፣ ኣደረጃጀትና የዘረጋው ህገመንግስትና መንግስታዊ ኣወቃቀር ከውጪቀድቶ ለጣፊነት፣የህወሃት ዋና ገዢ የመሆን ፍላጎት፣ ልነጠል ባይነትና ጎጠኝነት በተለያየ ደረጃ የተቻቻሉበት ነው ማለት ይቻላል። ማህበራዊ ተዛምዶንና ኣናሳ ጉድኝትን ከልማት አቅም ስርጭት፣ ተግባብቶ ከመተዳደርና ከማደግ እድል ጋር ያገናዘበ ህዝብና ምሁራኑ በደንብ የመከሩበትና በሂደትም የሚቃና የኣስተዳደር አከላለል ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ወደትግራይ የተካተቱ ስፍራዎች የቅዋሜ ምንጭና ለህወሃትም «እኔ ስልጣን ላይ ከሌለሁ..» እያሉ ማስፈራሪያ ባልሆኑ ነበር። እነጋንቤላና ቤንሻንጉልም በሰፊ የአስተዳደር ይዞታ ውስጥ እኛነታቸው እንደተጠበቀ በቅርብ እገዛ የተሻለ የልማት እርምጃ ባሳዩ ነበር። ዛሬ ባለው ሁኔታ ግን ከሁሉ በፊት የክልል ይዞታ የግዛት ድርሻ ተደርጎ ይወሰዳል። ሁሉም በየክልሉ እንዲወሰን/እንዲሰባሰብ የልማት ጥረትም በክልላዊ ደረጃ እንዲጠብ የሚገፋ ኣስተሳሰብ ኣለ። እያንዳንዱ ክልል በሁሉ ነገር ራሱን ይቻል በማለት ሽፋን የፌዴራል አውታሮችን ኣስቀናንሶ በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን የ«ብሄሮች ሉአላዊነት» በተግባር ለማረጋገጥ (ትንንሽ ሃገር ለመፍጠር) የሚጥሩ (በፓርላማው ውስጥም) አልታጡም። እነዚህ መሳሪያ ኣለማንሳታቸው እንጂ መነጠልንና ህዝበ ውሳኔን ከሚጠይቁት ብዙም የማይለዩ ናቸው።

የዚህ ኣይነቱ ኣስተሳሰብ በዛሬዋ እየተሰባሰበች ባለች ኣለም ራስን የመቻል/የነፃነት ኣስተሳሰብ ሳይሆን አሮጌ ጥበት (ጎጠኛነት) ነው።

በሌላ ኣቅጫጫ ምእራባውያን የሚለፍፏቸውን መፈክሮች እንዳሉ የሚያመልክ፣ የኣውሮፓና የኣሜሪካ ኢኮኖሚ የኣስተዳደግ ታሪክ በገበያ ብቻ የተመራ ሳይሆን የመንግስት ሚና የነበረበትና ዛሬም ጣልቃ የሚጋባበት መሆኑን፣ የኢትዮጵያም ልማት የመንግስት ሚናን የሚጠይቅ መሆኑን ያላጤነና የመሬት መሸጥ መለወጥን የሚሰብክ፣ መሬት ቢሸጥ ዛሬ ባለው ላይ ምን ያህል ማህበራዊ ቀውስና የጉርስ የለሽ መኣት ሊፈጥር እንዲሚችል (ይህንን ለማስወገድም የሰፋፊ እርሻዎች ልማት ከትናንሽ የገበሬ ማሳዎች ልማት ጋር፣ የትናንሽ ማሳዎች መቃለልም ከኢንዱስተሪ ልማት ጋር ተግባብቶ መሄድ እንዳለበት) ያልጨበጠ ኣመለካከት አለ። ሊታለፍ የማይችል የታሪክ ግዴታ ነው ብሎ በአውሮፓ የታየውን፣ ዛሬም በላቲን አሜሪካና በእሲያ ውስጥ(በህንድ ጭምር) የሚታየውን የእጦተኞች ሲኦል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመጣ የሚሰብክም አልታጣም።

በዚህ በኩል ህወሃት/ኢህኣዴግ መሬትን ወደሸቀጥነት ከማዞር መቆጠቡና ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ የማያስከትል መንገድ መምረጡ የሚያስመሰግነው ኣስተዋይነት ነው። ችግሩ ይህ አስተዋይነት ዲሞክራሲያዊ አገዛዝና እኩልነትን ከማረጋገጥና የህዝቦችን ወዶ ተነቃናቂነት ከማምጣት ሌላ አስተዋይነት ጋር መገጣጣም ኣለመቻሉ ነው። የመሬት መሸጥ የተከለከለ ቢሆንም የመሬት «ወረራ»ና ሽያጩ ማገጃ ያጣው፣በመንግስት መስሪያቤቶችና የልማት ስራዎች ውስጥ ሙስናና ዘረፋው ጣሪያ የጠበበው ለዚህ ነው። «ወረራ» የሚለው ቃል ከመሬት ጋር የተያያዘውን ህገወጥነት ጥሩ ኣድርጎ ይገልፀዋል። ኢህኣዴግ ይህንን ቃል መጠቀሙም ችግሩን ለመቆጣጠር አለመቻሉን ያመነበት ነው። ነገር ግን ከተቃዋሚዎች ጋር ተባብሮ መስራት ዛሬም ፍርሃቱ ነው።

መንግስታዊ ወሳኝ የስልጣን ክፍሎች በህወሃቶች መያዛቸው ግድ መሆን ያለበት መስሎዋል። ቀዳማዊ እመቤት ኣዜብ መስፍን ወደየክልሉ ሲሄዱ የየብሄር ብሄረሰብን ልብስ ማድረጋቸው በምሳሌነት እንደሚያሳየን የብሄር ብሄሰቦች «ስልጣን» ለህወሃት ቡድን እንደ ብዙ ኣልባሳት ሆኖ የሚያገለግል ነው። ደርግን የጣልኩና የብሄሮችን መብት ያረጋገጥኩ እኔ ነኝና ጠቅላይ ገዢነት የኔ ነው የሚል ኣስተሳሰብ ከዲሞክራሲ መንገድ ኣርቆታል።

በእርዳታና በምርኮ ሃብት ላይ ብድርና «ግዢ»ን ጨምሮ ያደራጃቸው ዘርፈብዙ ኩባንያዎች የትርፍ ኣራቢነት ባህርይ ከመያዛቸው በስተቀር ከቀድሞው ጊዜ ምርኮ ኣስገቢነትና ኣስገባሪነት ጋር የሚገናዘቡ ናቸው። በሌላ በኩልም ህወሃት ያለኢኮኖሚ ጉልበት ፖለቲካዊ ጉልበት እንደማይኖር ተምሯልና በግል ባለሃብቱ የሚታዘዝ ኣለዚያም በቀላሉ የሚፈነቀል እንዳይሆንና የመንግስቶች መንግስት ሆኖ ለመቆየት ያስችለኛል ያለውን የራሱን የኩባንያዎች ኤምፓየር መፍጠሩም ነው። የትግራይ ህዝብ እንደሌላው ህዝብ በስሙ እየተነገደበት ነው። ዛሬ ለህወሃት/ኢህኣዴግ ዋና የተቃውሞ ምንጭ የሆነበትም ይኸው የስልጣን ስስቱና የኩባንያዎች መረቡ ነው። ከዚህ አካሄድ ኣለመውጣቱና የተቃዋሚ ኣያያዙ እጅ ለእጅ ተያይዞ በልማት መራባረብን የሚቃረን ሊሆንም ችሏል።

ህዝቦች ከተባበሩና ከተፋቀሩ ይፈነግሉናል በሚል ፍርሃት የህዝቦች ኣስተሳሰብ፣ ተዛምዷቸውና መተሳሰባቸው እንዲቆራረጥ ማድረግ፣ ብሎም እንደይተማመኑና እንዲሸካከሩ ማድረግና የተቃዋሚ ድርጅቶችን መሰባበር፣ ከዚህም አልፎ በኣሁኑ ጊዜ ያሉትን ከተሞች የትምክህትና የተቃውሞ ጎሬ እያሉ መፈረጅና የህዝብ ጥንቅራቸውን «በዘዴ» የመቀየር ስራ ውስጥ መግባት ከጎጠኝነት የማይሻል ጥፋት ነው። ከኣንድ ኣካባቢ ወደ ሌላ ኣካባቢ ሄዶ የመስራትና የመኖር ነባር ማህበራዊ እንቅስቃሴ በመረበሹና

በመደናቀፋም ብሶተኛና ችግርኛ ከየትኛውም ክልል የሚጎርፍባት ኣዲስ ኣበባ ልትፈነዳ ደርሳለች::

ባጭሩ የኢትዮጵያ ህዝቦች የተሃድሶና የለውጥ አብዮት ጉዳይ ከኣሮጌ ጎጠኝነት፣ ከምስራቃዊ ያመለካከት ቅሪትና ከምእራብ አምልኮ ጋር ሁሉ የሚጓተት ነው::

## በተፃራሪነት መተያየት

በሶሻሊስት ኣመለካከት እንመራለን ይሉ የነበሩት የቀድሞ ታጋይ ተማሪዎችና በሂላ የፈጠሯቸው የፖሊተካ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውን የማይታረቁ ኣድርገው የሚመለከቱ ነበሩ:: እስከዛሬ ድረስ ችግሩ እንዳለ ነው:: ኣንዱ ሌላውን ጠላት ኣድርጎ ይወስደዋል:: በበኩሌ እነዚህን የመሳሰሉ በጎ ነገሮች ኣሉኝ ብሎ ከመቀስቀስ ይልቅ ተቃራኒዬ እኩይ ባህርይና ኣላማ ኣለው እያሉ ህዝብ ስለሌላው የፖለቲካ ወገን ስጋትና ጥላቻ እንዲሰማው ማድረግ ዋና አትኩሮታቸው ነው::

ከተቃዋሚዎች ኣኳያ ኢህኣዴግ ገና ከሶሻሊዝምና ከስታሊናዊ ስልት ያልተላቀቀ፣ ብሄራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ብቃት የሌላው፣ ጎሰኝነትን ያባዛና ሃገሪቱን ወደመፈራረስ የወሰደ ተደርጎ ሲሳል ቆይቷል:: በኢህኣዴግም በኩል ተቃዋሚዎች ትምክህተኛና ነፍጠኛ፣ ፀረሰላም፣ ጥገኞች፣ ከህዝብ ይልቅ ለግዛት ኣንድነት የሚጨነቁ፣ የድሮውን ስርኣት የሚናፍቁ፣ ህገመንግስቱን ለማፍረስና ህዝብን በዘር ለማጨፋጨፍ የተንቀሳቀሱ ኢንተርሃሞዮች ተብለዋል:: ኣሉታዊ (negative) የቅስቀሳ ዘዴ ከመለመዱ የተነሳ ዘዴው በበጎ ኣድራጎት ስራዎችም ውስጥ ገብቶ ተንፀባርቋል:: በ1999 ኣ.ም. ውስጥ በኤድስ ወላጆቻቻቸውን ያጡ ህፃናትን ፍቅር ሰጥቶና ተንከባክቦ ጥሩ ዜጋ ለማድረግ እንዲቻል በተካሄደ የቴሌቪዝን ምክክር ላይ ማህበራዊና ሰብኣዊ ሃላፊነታችንን አጉልቶ ከማሳየት በተጨማሪ ዛሬ ካልተንከባከብናቸው ነገ የንብረታችንና የህይወታችን ደህንነት ኣደጋ ላይ የሚወድቅበት ቀውስ ይመጣብናል የሚል ኣስፈራሪ ገለፃ ሲደጋገም ተሰምቷል::

ሁሉም የፖለቲካ ወገኖች በየተቃራኒያቸው ላይ የሚደረድሩትን ውንጃላ በህዝብ ውስጥ ኣስርፆ ተከታያቸውን ለማብዛት ከመጣር በስተቀር ከልብ ተቀራርቦ በመሃላቸው ያለውን የባላገራ ፖለቲካ ለመቀየር ኣለመጣራቸው ብዙ ጉዳት እያደረሰ ነው:: ምናልባት ለምርጫ ጊዜ ታክል ካልሆነ በቀር የሁለቱም ወገን አቋሞች በክርክር እብቅና ፍሬያቸው የሚወጣበት መድረክ የለም:: ሁለታችንም ተሳስተን ቢሆንስ? ትክክለኛው ነገር ከሁለታችን ውጪ ቢኖርስ? በሁለታችን በኩል መልካሙና መጥፎው ኣንድ ላይ ተሰናኝቶ እንዳለስ? የሚል ያልተዘጋ ኣመለካከት እንዳይኖር ከልክለዋል:: ኣንዱ የሌላውን ጥሩ ቢናገር ትልቅ ፖለቲካዊ ሽንፈት ተደርጎ ይወሰዳል::

ባለፈው የምርጫ ጊዜ በሁለቱም ወገን ስልጣን ቁልፍ ጉዳያቸው እንደነበር ነጥሮ ታይቷል:: የዶክተር ብርሃኑ ነጋ መፅሃፍ በቅንጅት ኣመራር ቦታ ላይ ለመቀመጥ የነበረውን ትግል፣ የራስን ድርጅት ኣባላት እጩ ተመራጭ ለማድረግ የነበረውን ሽሚያ፣ በውህደትም ሆነ በሌላ ጊዜ የነበሩ የውስጥ ሽኩቻዎች ምን ያህል ውስጠ ወይራነትና ማሸንክነት እንደነበራቸው ኣስጢኗል:: የኢህኣዴግ መንግስት ህገወጥነትን ለመግታት በወሰደው እርምጃ የራሱንም የህግ ኣክባሪነት ውሃልክ ኣስገምቷል:: ኣስጊ የሚባል የተቃውሞ ስብስብ እስኪበታተን፣ ዝምታና ፍርሃት እስኪሰፍን ድረስ የተካሄደው የፀጥታና የፕሮፓጋንዳ ክንዋኔ ለስልጣን ይጠቅም ይሆናል፣ ለሚለፋለት ልማት ግን ጉዳት ነበር::

ኢህኣዴግ ለብዙ ጊዜ ኣጥቶት የነበረው ሰፊ ተወዳጅነትና በተስፋ (optimisim) የተሞላ የትግል ተነሳሽነት በተቃዋሚዎች በኩል ተገኝቶ ነበር:: ግን ኢህኣዴግም ተቃዋሚ

ዎቹም ኣያያዙን ስላላወቁበት ኣብሮ ከ«ሁከት» ጋር ተመታ። ፈጣን የኢኮኖሚና የመልካም ኣስተዳደር ግንባታ የሚፈልገው የዚያ ኣይነት ሁለንተናዊ ድጋፍና መነሳሳትን ነው። ዝምተኝነትና ኩርፊያ በሰፈነበት ሁኔታ ውስጥ የሚካሄድ ልማት ደካማ ነው። ኢትዮጵያን ከድህነትና ከትርምስ የማውጣት ተልእኮን ከቡድናዊ ግብግብ በላይ ማስበለጥ ቢኖር ኖሮ ተቃዋሚዎች በኣናዳጅ ተረብና ሽርደዳ ውስጥ ባልገቡ ነበር። ኢህኣዴግም በህዝቡ ውስጥ የታየውን ኣስዳነቂ ተነሳሽነት ለመጨበጥ ሲል ተቃዋሚዎች «ያንድነት/ ብሄራዊ መንግስት»ን በሚጠይቁት ሰኣት የማይጥመውን ኣስጥሎ ተባብረው የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ባልገደደው ነበር።

«ሁከት» የማስወገድ እርምጃ ከተከናወነ በሂላ ባገር ውስጥ ያሉ ህጋዊ ተቃዋሚዎችና ኢህኣዴግ ተቀራርቦ መወያየትና መደራደር ጀምረዋል። ጅማሯቸው ግን በሃገሪቱ ዙሪያ-መለስ ልማት ላይ ተባብሮ የሚያሰራ ሊሆን ቀርቶ ከተለመደው መወነጃጀል ሊያወጣቸውና ኣንዱ የሌላውን መልካም ለማየት ገና ኣላስቻላቸውም። ከሶማሊያው እስላማዊ ፍርድቤቶች ህብረት በኩል ግልፅና ተጨባጭ ኣደጋ ተደቅኖብናል የሚል ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ ያለድምፅ ውሳኔውን ለማፅደቅ እንዲቻል የውሳኔ መስጫ ቀኑ ተላልፎም የተፈገለው ሙሉ ስምምነት ሳይገኝ መቅረቱ ይታወሳል። በዚያን ወቅት የድጋፍ ድምፅ የነፈጉት ተቃዋሚዎች ኣቋም በጤና ኣልታየም ነበር። ከስብሰባው እለት (ህዳር 21፣1999) በሂላ በመንግስት መገናኛብዙሃን ሲነፍስ የነበረው ነቀፌታና ውግዘት ተገቢነት አልነበረውም። በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የመንግስት ተጠሪ የሆኑት ሽፈራው ጃርሶ በመግለጫቸው የተቃዋሚዎቹን ኣቋም የሃገር ክህደት ነበር ያሉት።

በወቅቱ የተቃዋሚዎች ለሃገር ተቆርቋሪነት የሚያጠራጥር ኣልነበርም። ውሳኔው በመግባባት እንዲፀድቅ ጊዜ ተስጥቶ እንመካከር የሚለው ሃሳብም የመጣው ከነሱው በኩል ነበር። ጉዳዩ ውስብስቦሽ ሊያመጣ የሚችል እንደመሆኑ የኣቋም ልዩነት ቢፈጠር የሚገርም ኣልነበረም። በምክር ቤቱ ውስጥ ከተቃዋሚዎች ኣንዱ ሲሉት የተሰማው «ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶች» የሚለው ይውጣ ጠላት የሚያበዛ ነው፣ ታላቋ ኣሜሪካ እንኳ መውጫ ባጣችበት ጣጣ ውስጥ እንዳንዘፈቅ በጣም መጠንቀቅ ኣለብን የሚል ነበር። ይህ ለሃገር ማሰብ እንጂ ክህደት ኣይደለም። የፓርቲዎች የመቻቻል ጥንካሬ የሚረጋገጠውም እንዲህ ባለ ከባድ ሁኔታ ውስጥ በሚያሳዩት ጠባይ ነው። ያም ሆነ ይህ በኣዲስ መንፈስ ወደ ሶስተኛው ሺህ መግባት ከፈለግን የተለያዩ ሃሳቦችን በጤናማነት መቀበል መልመድና በፅንፍ ከማሰብ መውጣት ያስፈልገናል። ኣለዚያ በሃገራችን የመልካም ኣስተዳደር ግንባታ ጥረት ውስጥ የሚታዩ በጎ ጎኖችን እንደሌሉ አድርጎ አንዱ ሲኮንን ሌላው ከ200-400 ኣመት እድሜ ያለው የምእራብ ዲሞክራሲ ከኛ ጋር ኣይወዳደርም እያለ ድክመትና ጥፋት መሸፋፈን ይቀጥላል። ፖለቲካ ሳይንስ እንጂ ማንም እየተነሳ የሚፈተፍተው ኣይደለም እያሉ ህዝብን ከተቃዋሚ ፖለቲካ ኣርቃለሁ ሲባል በሌላ በኩል ለፈጣን ልማት የሚያስፈልገው የተራ ህዝብ ፖለቲካዊ መነሳሳት ኣልገኝ እንዳለ ይቀራል። በሃገርና በልማት ጉዳይ ኩርፊያ የለም የሚለው ቅስቀሳ ኢህኣዴግም ለሃገርና ለልማት ብሎ ተቃዋሚዎቹን ያቅርብ የሚለውን ቁምነገር ማካተትና በተቃዋሚ ዙሪያ ያለውን ኩርፊያ ማምከን ሳይቻለው ይቀራል። ባጭሩ የእርቅ ነገር ሲነሳ መልሱ ማን ተጣላና እንደሆነ ይቆያል። መወነጃጀልና መማረር እየተደጋገመና ወደ ህዝብ እየተላለፈ ጉዳት ማድርሱ ኣይወገድም።

## የጠላትነት ፖለቲካ ውጤት

የኢህኣዴግም ይሁኑ የተቃዋሚዎቹ ወገኖች ወደ ህዝብ በሚደርሱባቸው የመገናኛ መንገዶች እስከዛሬ የለቀቁት ቅስቀሳ ኣስተሳሰብን አጠማሂል። የሁለቱም ወገን ፖለቲካና ቅስቀሳ የሚመራው እውተኛውን ነገር በማስጤንና ወደ እውነቱ በመሳብ ሳይሆን «ተፃራሪን» ከፋፍሎ በማድከም፣ ጭራቅ ኣስመስሎ በህዝብ በማስጠመድና ህዝብን የራስ መሳሪያ በማድረግ ኣላማ ነው። ስለሆነም ለዚህ ኣላማ ይጠቅማል የሚባልን ነገር ሁሉ መተግበር (utilitarianism) እንዲሁም ባጭበርባሪ ሎጂክ፣ በስሜት ነዘራና በቋንቋ

«ውበት» የሰውን ኣእምሮ መስለብ (sophistry) በፖለቲካ ፅሁፎችና ንግግሮች ላይ ተለቆ ኖሯል:: የሚጠቅም ከመሰለ የቆየ ታሪክ ቢሆን የቅርብ፣ ሃሜት ቢሆን የተፈጸመ፣ የተጣራ ቢሆን ባይሆን፣ ኣልባሌ ቢሆን ባይሆን፣ በብሄር ብሄረሰቦች ግንኙነት ላይ ጠንቅ ይትከል ኣይትከል ኣያስጨንቅም:: የመረጃውን ዋጋና ተመራጭነቱን የሚወስነው «ጠላት»ን ለማጥቃት ያለው ርባና ነው:: የ«ጠላት»ን መልካም ስራና ገፅታ የሚናገር መረጃ እንደሌለ ተደርጎ ይታለፋል፣ ይደበቃል:: ካስፈለገም በሚፈለገው ኣይነት ይስተካከላል ወይም ከሃሰት ጋር ይለወሳል:: ግምትና ጥርጣሬ የተፈፀመ ተደርጎ ይቀርባል:: የባላጋራን ስም በደንብ ለማጥፋት የሚያዋጣ ነውር ከባዶ ሜዳ ላይ ተፈጥሮም ቢሆን ይደፈደፍበታል:: የትውልድ ስፍራ፣ አስተዳደግና የብሄር ብሄረሰባዊ ውልደት ሳይቀር ለፖለቲካ ውጊያ ተግባር ውለዋል:: ህዝብ የቀረበለትን ኣምኖ እንዲውጥ «ጀግና»፣ «ኣርቆ ኣስተዋይ»፣ «ኩሩ» በመሳሰሉት ጣፋጭ ሃረጎች ማሞካሸት ኣንድ ዘዴ ነው:: ባንድ ብሄር ብሄረሰብ ላይ ከቀድሞ ጅምሮ ተፈፀመ የሚባል በደልንና ስድብን እየደረደሩ በስሜታዊነት ማጥመድ ሌላው ዘዴነው:: ትምክህተኛ/ነፍጠኛ ኢህኣዴግን ለተቃወመ ሁሉ የሚሰጥ ስም እስኪመስል ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል:: በነዚህ ሁሉ መንገዶች መገራረፍ ያድጋል:: በጣም ኣዋጣ (ኣሳመመ) የተባለ ውንጀላ ተመላልሶ ይሽከረከራል:: ያመመውና የበገነው በተራው የበለጠ ጥቃት ኣሰናድቶ ይሰነዝራል:: በባሰ ይባስ እልህ ወደ ህዝብ የሚሄደው የእንካሰላንቲያና የቅስቀሳ ጎጂነት እየጨመረ ይሄዳል::

በግሉ ፕሬስ ዘንድ፣ በተቃውሞ የሬዲዮ ስርጭቶችና ኢህኣዴግ በሚሞካሽባቻው መገናኛ ዎች ዘንድ ይህ ሲተገበር ቆይቷል:: መምህር ገብረኪዳን ደስታ <u>የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ</u> በሚል መፅሃፋቸው መሰል ችሎታቸውን ኣሳይተዋል:: ጥፋተኛ ስትባል አትከላከል ቢቻል በባሰ ካልተቻለም በዚያው ጥፋት ከሳሽህን መልሰህ ክሰስ የሚለውን የገዢውን ቡድን ስልት በደንብ ቀስመውታልና ኣጥንት ድረስ ዘልቆ የሚያሳምም ያፀፋ ጥቃት ለማድረስ እነ ፕሮፌሰር ጥላሁን በገቡበት አረንቋ ውስጥ ገብተዋል:: ጥላቻን በጥላቻ መልሰዋል:: ተቃውሞ እየበዛ ከሄደ ህዝብ በፍርሃት ተሞልቶ ከጀርባህ እንዲሰለፍ የሆነ አስደንባሪ ጠላት(scarecrow) ፈጥረህ ገትር በሚለው ስልት መሰረት ከተቃዋሚ መሃል ቀንደኛ ፀሮች -- የሸዌ ኣመራ ትምክህተኞች -- ብለው ለይተው እነሱን የማይቀረቡ ጭራቆች ኣድርጎ በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ለማስነከስ፣በዚህም በትግሬነት ላይ የተንጸባረቀውን መጥፎ ስሜት ወደነሱ ለማዛወርና ኢህኣዴግ ህወሃትን ለማስመስገን አቅደዋል:: ለእቅዱ መሳካት ያዋጣሉ ያሏቸውን የዱሮና የዛሬ መረጃዎችን መርጠዋል፣ ከፍላጎታቸው እንደሚስማሙ አዛብተው ተጠቅመዋል:: ቅጥፈትህ እውነት እንዲመስልልህ በልበሙሉነትና በትእቢት (arrogance) ሙላው በሚለው ስልት መሰረት የለየት ውሸትም በኩራት ደርድረዋል::

ፕሮፌሰር ጥላሁን ትግሬን በካንሰርነትና በከሃዲነት እንዳሰቡት ሁሉ መምህር ገብረኪዳንም «አማሮች እንኳን ሊገዙህ ልትገዛቸውም ምቹ አይደሉም» ከሚል አሰተሳሰብ ጋር (የይምሰል ማስተካከያ ኣድርገው) መስማማታቸው (ገፅ 88)፣ «አንኮበራውያን» ከምኒሊክ ጅምሮ በትግራይ ህዝብ ላይ ዘረኛ ጥላቻ ነበራቸው በትግራይ ህዝብ ላይ ሲያሴሩና ግፍ ሲሰሩ ነበር የሚል ስእል መሳላቸው፣ የሸዌነትም ሆነ የሸዌ ኣማራ ክልልተኝነት (regionalism) እንኳ በሌለበት «የሸዋ (አንኮበራዊ) ብሄርተኝነት» የሚባል ሃረግ ፈጥረው ሸዋንና ምኒሊክን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ጋር ለማቃረን መልፋታቸው፣ «ትግሬ ጉራጌ ካገራችን ይወጣ ሲሉም ኢትዮጵያውያን ስለሆናችሁ ከሀገራችን ከሸዋ ውጡ ማለታቸው ነው» በማለት አስቂኝ ትርጉም መስጠታቸው (ገፅ 211)፣ ምኒሊክን ኣርክሰው ዮሃንስን አፅድቀው መፃፋቸውና ኢህኣዴግን እንከን አጥተውለት «በ14 አመት ታምር ሰራ» ብለው ማሞካሸታቸው(ገፅ 218) ከላይ ለተጠቀሰው ችግር ኣብነት ነው:: ምኒሊክ ተዋግቶና ድል መትቶ መዝረፉ የሌሎችም የዘመኑ ነገስታት ባህርይ መሆኑን ማየት የከለከላቸውና በትግራይ ህዝብ ላይ ብቻ እንደተፈፀመ አድርገው እንዲያቀርቡ ያደረጋቸው፣ ስልጣን ከሰማይ ተሰጠን ይሉ የነበሩ ነገስታትን ስልጣንን በህዝብ የሚሰጥና የሚነፈግ አድርገው ባላማሰባቸው ለመንቀፍ

ያደረሳቸው (ገፅ 88)፣ የእነምኒሊክ ዘመንን የታሪክ አካሄድ አስቶ ዘረኛውና ትምክህተኛው አንኮበራዊ ስርኣት የትግራይንና የኢትዮጵያን ህዝብ መቶ ኣመት ወደ ሂላ ጎተተ ያስባላቸው ይሀው ችግር ነው።

ወደ ሂላ ተመልሰው እንደ ጥምቀት ባሉ በኣላት ላይ በኦሮሞና በትግሬ ዘፋኞች መሃል ይነሱ የነበሩ ኣምባጓሮዎች በትምክህተኞች ተንኮል የሚጀመሩ ነበሩ ማለታቸው፣ የጉራጌውና የኦሮሞው፣የሌላውም መዘለፊያ ነበሩ ያሏቸውን ኣባባሎች አሰባስበው መደርደራቸው ዋና ጠላት ያሏቸውን የሸዋ ኣመራ ተቃዋሚዎች ኣባሪ ኣሳጥቶ ለመነጠል ዘዴ መሆኑ ነው። በኣቡነ ጳውሎስ ላይ የሚወረወረውን ነቀፌታ «እንደጠላት ከተፈረጀ» ብሄር ከመወለዳቸው ጋር ማያያዛቸውና (ገፅ 247) ታቦትም የዘረኝነት ሰላባ ሆነ ማለታቸው (ገፅ 249)፣ በግንቦት 30 1997 በኣ. ኣ.ዩንቨርሲቲ የነበረውን ቅዋሜ በፀረ ትግሬ መፈክር ማቅለማቸው ከብሄር ጥላቻ በቀር ፍሬ ያለው ፖለቲካዊ ምክንያት የሌለ ማስመሰላቸው ነው። የትግራይ ህዝብ ፍትሃዊ ኣመለካከት ያለው ለመሆኑ ምሳሌያዊ አባባልና ራስ ስሁል በገዛ ልጃቸው ላይ የሰጡትን ፍርድ በኣስረጂነት መጥቀሳቸው (ገፅ 233-235)፣ በተደጋገሚ ትግራይን የኢትዮጵያ መሰረት አድርገው መናገራቸው በትግሬነት ላይ የተንፀባረቀውን ኣፍራሽ ኣመለካከት ኣሳፍረው መርታታቸው ነው።

ፍላጎትና ጥቅም ከህዝብና ከነባራዊ እውነታ ጋር ሆድና ጀርባ ሲሆን የሚደረገውና የሚባለው ሁሉ ደነዝነት/ድድብና ዋና ባህርይው ይሆናል። «የኣማራ ነፍጠኛ/ትምክህተኛ ...» የሚል ማስፈራሪያ (scarecrow) ተሰቅሎ 16 ኣመት ሲሰራበት ተኖሯል። ማስፈራሪያ ምስሉ ኣርጅቶ ኣእዋፍ ኣናቱ ላይ ተቀምጠውበት ታዩ(ገዢውን ቡድን በመትፋትና በምርጫ ራቁት በማስቀረት)። ኣሁንም ይሰራል ብሎ ማሰብና መውተርተር ድንዘት ነው። ወያነ/ኢህኣዴግ በኤርትራ ጉዳይ አያያዝ ላይ የሰራውን የፖለቲካ ጥፋት፣ ወደ 70ሺ ሰው ቀጥፏል የሚባለውን የቅርብ ጦርነትና ዛሬም ያልተላቀቀንን ጣጣ አስቀምጦ ለኤርትራ ችግር ያበቃን ምኒሊክ ነው እያሉ መራቀቅ መካንነት ነው። ከንጉሰ ነገስትነት በፊት የሸዋ ገዢ የነበረውን ንጉስ ምኒልክን ከአፄ ዮሃንስ ጋር እያነፃፀሩ ትንሹን ንጉስ ትምክህተኛ ማለት ድንቁርና ነው። መቶ ኣመት ወደሁዋላ ርቆ የምኒልክን ጭካኔ ሲያዩ የቅርቡን የወያኔ/ኢህኣዴግ ጨካኝ የሃይል እርምጃ ኣለማየት ህሊናቢስነት ነው። ከጥንት ጀምሮ የሸዋ ትምክህተኝነት የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው ብሎ መቀስቀስና በሁሉ ነገር ማእከል ካልተሆነ ኣደጋ ነው ብሎ ማወጅ ወደገደል የሚወስድ የመጨረሻ እውርነት ነው። ፖለቲካዊ መካረር ውስጥ የሚገኘው ይህ ትውልድ ኣልፎ ኣዲስ ትውልድ እስኪመጣ ስልጣንን ኣናስቀምስም የሚል ኣስተሳሰብ ያለው ካለም ጤና ያጣ ነው።

በህትመት ስራዎች፣በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ብሎም በኣሉባልታ ህዝብን ወደራስ ለማድረግና ከፖለቲካ «ጠላት» ጋር ለማቃረን የሚሰራበት ወልጋዳ ኣስተሳሰብ (sophistry ) መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የድቀት ኣዝመራም ነው። ባስተሳሰብ ቀናነት ላይ የደረሰው ጉዳት በቀላል የሚመዘን ኣይደለም። በስልጣን ላይ ያሉት ገዢዎች ምን ቢናገሩ፣ምን በያቅዱና ቢሰሩ ፈጽሞ በበጎ ኣለመቀበል፣ሁልጊዜ መጠራጠርና ክፉ ክፉውን ማሰብ የደዌ ያህል ተዛምቷል። የደዌው ጥልቀትም በጦርነት ሲተጋተጉ የነበሩትንና አሁንም እሳትና ጭድ የሆኑትን ሸኣቢያንና ኢህአዴግን ውሽታቸውን ነው ብሎ እስከማሰብ እንፉጭ ያደረገና የእግር ኳስ ወይም የሩጫ ውድድር በሳተላይት ስርጭት እየተካሄደ እያለ መብራት ቢጠፋ ወይም ስርጭቱ ቢቋረጥ ኣውቀው እንዳናይ ነው እስከማለት ኣስተሰሰብን ያጠቆረ ነው።

ጥርጣሬ እየተስፋፋና የሰዎችን ልቦና እየመዘመዘ ሲፈጥር የነበረው ጥላቻና ሁከት ሌላ ኣዝመራ ነው። «የኣማራ ትምክህተኝነት»ን የሁሉ ነገር ማመካኛ ያደረገ ቅስቀሳ ቀደም ጉዳት አድርሷል። ጠባብነት ጉዳት ኣድርሷል። ገዢው ቡድን በጭካኔ የተሞላ የፀጥታ ሃይል ማዘጋጀቱ፣ ተቃዋሚዎቹን በስለላ፣ መስሎ በመስረግ፣ በአሳፋሪ ወጥመድና በለየለት የሃሰት ክስ የመሰባበር ተግባር ውስጥ ይበልጥ እየተዋጠ መምጣቱ፣ ከህወሃት

ጋር የተያያዙ ኩባንያዎችም ሙያተኛ በመቅጠር ላይ ፖለቲካዊ መመዘኛ እስከመጠቀም መሄዳቸው ከጠላትነት ፖለቲካ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው:: «ወጣቱ ማንዴላ» እስከመባል ገንነው የነበሩት ልደቱ ኣያሌው በምርጫ 97 ጊዜ «እንስሳ አይደለሁም በጎሳ አላስብም ... ጠቅላይ ሚንስትሩ ትንሿን ጣት እያሳዩ » ሌላ ሌላም በማለት የነገር ክብሪት ከመሆን አንስቶ ኣፈንግጦ እስከ መክፋፈል በሂላም ለኢሕአዴግ የተቃወሚ ወዳጅ እስከመሆን መፈናጠራቸውም ለነበረባቸው የውስጥ ኣርበኝነት ሃሜት የሚስማማ ነው::

በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ የፓርቲ ኣደረጃጀት ኣሳሳችነት፣የመልካም ኣስተዳደር ኣለመጎልበትን ከትውልድ ቦታና ከብሄራዊ ውልደት ኣንፃር የሚተረጉሙ ቅስቀሳዎች ኣለመተማመንና ጥላቻን ሲያመርቱ ቆይተዋል:: ከግንቦት 1997 ምርጫ በፊትና በሂላ ከጥላቻ ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥቃቶች ደርሰዋል:: ኣንድ ጥላቻ ሌላ የጥላቻ እሳት እየወለደ መጥቶ ኣንከበራውያን ቀድሞም ዛሬም የትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላት የሚል የጥላቻ እሳት ኣሳቀፈን:: የመምህር ገብረኪዳን መፅሃፍ በትግራዊ ላይ የሚንፀባረቅ ኣፍራሽ ስሜትን ኣላስወገድም:: ሊያስወግድ የሚችል ነገርም ኣላዋጣም:: ከወደ ሸዋ በትምክህተኝት ስም ተነካን ተዘለፍን የሚል መራራ ስሜት እንዲነሳ መንደርደሪያ ሰጠ:: የትግራይ ህዝብ መቶ ኣመት በረዘመ «ጥቃትና ቂም» ታሪኩን እንዲመለከት፣«ሸዋ ትምክህተኞችን»ም በጠላትነት እንዲጠምድ ከመጋበዝ ያልተለየ ነገር ኣደረገ:: በሁለቱም ኣቅጣጫ የሚግል ከተገኘ ተያይዞ ጉዞ ወደ ቃጠሎ መሆኑ ነው:: የጥላቻ ቆንጆ የለውም:: ከጥላቻ መልካም ፍሬ ኣይፈራም::

የኣክሱም ስልጣኔን ማወደስ የመጣው ከኢህአዴግ በሂላ ኣይደለም:: እንደራስ ኣሉላ የመሳሰሉት ጅግኖች የትግራይ ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ጌጦች ናቸው:: በኣፄ ሃይለስላሴም ሆነ በደርግ ዘመን ኣፄ ዮሃንስ ከቴዎድሮስና ከምኒሊክ ጋር ተወዳሽ ነበሩ:: በትግራዊነት ላይ ዛሬ የሚታየው ድፍርስ ስሜት የትግራይን ህዝብ ከሌላው ኣርቆ ከማየት ወይም የኢትዮጵያዊነትና የጀግንነት ታሪኩን ከመጠራጠር የፈለቀ ኣይደለም:: ገብረኪዳን የምኒሊክን ከጣሊያን ጋር መደራደር ከብዙ ምክንያቶችና ሌሎቹ ገዢዎች ካደረጉት ጋር ማገናዘብ እንዳቃታቸው ሁሉ፣የእነፕሮፌሰር ጥላሁን ይልማ ኣይነቱ ግልብም ከጣሊያን የተመሳጠሩትን የትግራይ መሳፍንት ብቻ በእይታው ውስጥ ኣስገብቶ ድርጊታቸውን ከትግሬነታቸው ጋር ኣዛምዷል:: ቅኝ ገዚዎች ካንበረከኩት የትኛውም ህዝብ ውስጥ መሳሪያ የሚሆናቸውን ክፍል የመፍጠራቸውን የኣለም ኣጠቃላይ እውነት መረዳት፣ፋሺስት ጣሊያን በኣምስት ኣመት የኢትዮጵያ ቆይታው እንኳ ብዙ የባንዳ ኣይነት መፍጠሩንና ከድል በሂላም ያለሃፍረት በኢትዮጵያ ላይ ለመንፈላሰስ የቻሉ ባንዶች እንደነበሩ ማመዛዘን የተሳነው የታሪክ መሃይም ባንዳነትንና ብሄርን ሊያገናኝ ሞክሯል:: ይህንን መሳዩ የእነ ፕሮፌሰር ጥላሁን ነውረኛ ኣመለካከት መንስኤ ሳይሆን የውጤቱ የከፋ መክሰቻ ነው:: የሸዋ ትምክህተኞች በተንኮላቸው የፈጠሩት ኣይደለም:: (ገብረኪዳንም እንዲገባቸው ከፈለጉ የበቀለ ሹሜን የሰሚ ያለህ! መፅሃፍ በኢንተርኔት ላይ ፈልገው/ኣስፈልገው እንዲያነቡ እጠቁማቸዋለሁ::) የነውረኛው ኣመለካከት ስርጭትም ቢሆን በሸዋ ትምክተኞች ዘንድ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የገባ ነው:: ትግሬ ግለሰቦች ለምን ስልጣን ላይ ተቀምጠው እናያለን ባይነትም ኣይደለም ምክንያቱ:: ምክንያቱ ትግራዊ የበላይነትን የሚያጎለብት ኣገዛዝ ተመሰረተ ነው:: የሸዋ ትምክህተኞች ደመኛ ተደርገው ቢቀመጡ ወይም የመምህር ገ/ኪዳን ኣይነት መፅሃፍ በየወሩ ቢታተም ችግሩ ኣይወገድም:: የኣፄ ዮሃንስ ኣፍቃሪዎችና የምኒሊክ ኣፍቃሪዎች የመሸናነፍ ክርክር ቢገጥሙም የሚያስገኙት ጥቅም ኣይኖርም:: የራስ ስሁልንም ፍርድ መጥቀስ የዛሬውን የማይፈለግ ጥላቻ በመቀነስ ጠብታ ታህል ኣይሰራም ወይም ለዛሬዎቹ መሪዎች «ፍትሃዊነት» ኣስረጅ ኣይሆንም::

ህገወጥነት፣ የፍትህ እጦትና ሙስናው በተለይ ከ1997 ምርጫ ወዲህ ኣይን ሊያወጣ ደርሷል:: ጎሰኛ መጠቃቀሙ ከኣዲስ ኣበባ እስከ ክልሎች ይጦፋል:: እንዲያውም «ይለይለት!» በሚል መንፈስ የሚካሄድ ይመስላል:: ሳይመሽ ይችን ታህል ትድረስኝ

በሚል ፌደራል ፖሊሶች አቁሞ የከተማ ኪስ ቦታ በጉልበቱ የያዘ ኣለ። ወታደሮች የክ/ከተማ አስተዳደርን በቡድን ተጭነው የቤትመስሪያ ቦታ ለመውሰድ ችለዋል። ከጥቂት ኣመታት በፊት ምንም ያልነበረው የንግድ ፎቅ/ፎቆች ገትሮ ይገኛል። በህገወጥ መንገድ ባዶ ቦታ ላይ ልዩ ልዩ ንግድ የከፈተው፣ ቤት እየሰራ የሚቸበችበው በኮንትሮባንድ የሚናጥጠው አይወራ። ያንድ ሰሞን ዘመቻም መፍትሄ አይሆንም። ከየትኛውም ጎሰኝነት መሪነቱን የያዘው ትግራዊ ጎሰኝነት መሆኑም ጉድ ተብሎ ያበቃለት ነው። ለስልጣን ቁጥጥርና ለገንዘብ እንቅስቃሴ «ገዢ» የሚባሉ መዋቅሮች በህወሃት ሰዎች እጅ ውስጥ መግባታቸውም ከበፊቱ ብሶበታል። በቁርጥ «የኢንዶውመንት ይዞታ» ከሚባሉት ሌላ በግልና በአክሲዮን ሽፋን ሀብት ማደርጀቱ ሰፍቷል። ኣድላዊ ኣስተዳደር ኣለ የሚል እምነትና የእምነቱ ኣራጋቢዎች የሚጠፉት ይህን መሰሉን ብልሽት ኣስወግዶ መልካም ኣስተዳደርን ከዳርዳር በማጎልበት ነው።

## በልማትና በለውጥ ላይ ማኩረፍ ኪሳራው ለራስ

ለደርግ ኣምባገነንነት ቅዋሜን ማሳያና መጉጃ ሆነው ስር እየሰደዱ የመጡት ኩርፊያ፣ ከዳር ቆሞ ማየት፣ ችሎታን መሸፈጥና ኣውቆ ማጥፋት በኢህኣዴግ ኣስተዳደር እንደመደናገጥ ያሉባቸው አጫጭር ወቅቶች የተከሰቱ ቢሆንም በደምሳሳው ዛሬም ተንሰራፍተው እናገኛቸዋለን። የችግሩን ጥልቀት ለመረዳት በኣካባቢ ፅዳትና በመንገዶች እንክብካቤ ላይ ያለውን መፍቻ ያጣ ብልሽት ማየት ይበቃል። የኣዲስ ኣበባ ከተማ የፅዳትና የውበት ኣጠባበቅ ደንብ ከወጣ የቆየና ነዋሪና ተማሪውን ለማንቀሰቀስ የተሞካከረ ቢሆንም ወረትን ሊሻገር የቻለ ለውጥ የለም። በ1999 ውስጥ የኮሌራ ወረርሽኝን አደጋ በማስመርኮዝ ፅዳትን ለማነቃቃት ቢሞከርም የኣዲስ ኣበባ ቆሻሻም ሆነ ነዋሪው ኣልተነቃነቀም ማለት ይቻላል። የኣደባባዮችና የተክሎች ኣጥሮች በግጭት ኣልቀዋል። ወንዞች ላይ ብከላው ጠንቷል። በላስቲክና በዶንያ የተቋጠሩ ቆሻሻዎች መንገድ ላይ ተጥለው መመልከት የሚያስገርም መሆኑ ቀርቷል። የተደፈኑ የፍሳሽ ጉድጓዶች በፅዳት ሰራተኞች ቆሻሻቸው ተዝቆ መስራት ከመጀመራቸው መደፈን ይጀምራሉ። የአስፋልት ዳርቻ የእግረኛ መንገዶች ለእግረኛ ክብደት ተመጥነው ቢሰሩ(ቢነጠፉ) ሳምንትም ሳይቆዩ መኪኖች እየወጡ ያፈላልሷቸዋል። የብርቱ ቀለበት መንገዳችን የፍሳሽ ማሳለፊያዎች መደፈን ብቻ አይደለም በብረት ክዳናቸውም ላይ ስርቆት ተፈጽሟል። ብርቅነቱ ሳያረጅ በጎርፍ ምክንያት መቦርቦር ጀምሮታል። መንገድ ቢሰራ በተክሎችና በሳር ለማስዋብ ቢጣር፣ ዛፍ በዘመቻ ቢተከል <u>ተንከባክቦ የማቆየቱ ችግር</u> ሁሉም ተበለሻሽቶ እንዳልነበር እንዳይሆን እያሳሰበ ነው።

የመንግስት ሰራተኛውን በብቃትና በፍላጎት ማነስ በገፍ ከስራ ውጭ ማድረግ ፈፅሞ ዘላቂ ያሰራር ተሃድሶን ኣያስገኝም። ያለፉት የማባረር ተሞክሮዎችም ለኣጠቃላዩ ኩርፊያ ፖለቲካዊ መፍትሄ እስካልተገኘ ድረስ ውሃ ወቀጣ እንደሚሆን አረጋግጠዋል።አውቆ በማጥፋትም ይሁን ሲጠፋ ዝም ብሎ በማየት የኢህኣዴግን መንግስት ያንጨረጨረ የሚመስለው ጥቂት አይደለም። በፅዳትም ይሁን በሌላ የልማት ተግባር ላይ ልባዊ ተሳታፊ ቢሆን ኢህኣዴግን የደገፈ ወይንም የኢህኣዴግን ዝናና ስልጣን የጠቀመ የሚመስለው ሞልቷል። ኣይደለም ይህ በስራ መለገም እንደሰላማዊ የትግል ስልት እንዲተገበር የሚመከርም ሆኗል።

መፍትሄ የተነፈገው ፖለቲካዊ ብሶተኝነትና ኢህኣዴግን ወድቆ የማየት ፍላጎት ህሊና ከማሳጣቱ የተነሳ በግብርና ምርትና በውጪ ንግድ የታየውን የቅርብ ጊዜ እድገት ኣንዳች ድርቅ መጥቶ ድራሹን ቢያጠፋለት እስከመመኘት የደረሰ ሰው እናገኛለን። የባሰም ኣለ። «የኢትዮጵያ ሕዝብ ደባ ቢሰራበትም ፀብ ቢለኮስበትም አይለያይም፣ደርግ በወደቀበትና መንግስት በሌለበትም ጊዜ ተሳስቦ ኖሯል» የሚል መከራከሪያ ላይ ቆሞ «ኣሁንም የፈለገው ኣይነት ቀውስ መጥቶ ድብልቅልቁ ቢወጣ » ብሎ የሚመኝና ኢህኣዴግን በዚህ ኣይነቱ መንገድም ለመገላገል የሚመኝ ሰው እያጋጠመ ነው። ይህኛ

ው አስተሳሰብ ተበራክቶ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ የፈጠረ ቀን እንጃልን:: ተፈጥሮም ከሆነና ድንገት የሚከሰቱብን አጋጪ ድርጊቶች የዚያ ውጤት ከሆኑ ኣስተሳሳቡን የሚያመክን መፍትሄ ካልተገኘ ኢትዮጵያ እሳት የሚንቀለቀልባት ገሃነም እንዳትሆን ያሰጋል::

በትግል ዘዴነት ፖለቲካዊ ቡራኬ የተሰጠው የስራ ልግመት ሰሚ ካገኘ ሌላው የኣዘቅት መንገድ ነው:: በመንግስታዊ የስራ ዘርፎች ውስጥ ግልጽነትን፣ተጠያቂነትንና ፈጣን አሰራርን ለማስረጽ የሚደረገውን ጥረት መና የሚያስቀርና ሙስናን የሚያስፋፋ ነው:: በፖሊስ ተግባር ላይ የሚደርስ የስራ መበደል በህብረተሰቡ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ችግር መገመት ያዳግታል:: ልግመት በህክምና ሙያ ውስጥ ቢውል የሚዘገንን በደል ይሆናል:: ተመራማሪና ፈጣሪ የተማረ ሃይል በማፍራት ረገድ ገና ባልተሳካለት የትምህርት መስክ ውስጥ መለገም ቢታከልት የ«ትውልድ ግድያ » የሚባለውን መፈፀም ይሆናል:: ይህ ኣይነቱ የትግል ስልት በድርብርብ ችግር ወደ መላጋት እንጂ ወደ ደሞክራሲና ፍትህ ኣያደርስም::

የዲሞክራሲ መጀማመሪያው ዲሞክራሲያዊነትና ዲሞክራሲን ለማስገኘት የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው:: የዲሞክራሲያዊ መንግስት መቋቋሚያው እውነተኛ የህዝብ ድምፅ ነው:: በእውነተኛ የህዝብ ድምፅ የተቋቋመ መንግስት መኖር ግን ለዲሞክራሲ መኖር ዋስትና አይሆንም:: ለዲሞክራሲ መቋቋም ዋስትናው መራጩ ህዝብ መብቶቹን አለማስነካቱና ስርኣቱ ቀጣይነት ማግኘቱ ነው::

ለዲሞክራሲና ለሰብኣዊ መብቶች መረጋገጥ የሚካሄደው ትግል በስብሰባና በሰልፍ በመጮህም ሆነ በምርጫ ውድድር በመሳታፍ ብቻ የተገደበ ኣይደለም :: የትግሉ ግንባርና መልክ ብዙ ነው:: ኢኮኖሚ፣ፖለቲካ፣ማህበራዊ ኑሮ፣ ባህል፣ ስነምግባርና ኣስተሳሰብ ሁሉ የትግል ሜዳዎች ናቸው::

ሰብኣዊ መብቶች ሰጪና ተቀባይ የማይኖርባቸው በተፈጥሮ የተቀዳጀናቸው ናቸው ሲባል በተደጋጋሚ ይሰማል:: እኛ የምንገኘው ግን በስልጣን ላይ ያለ ኣካል ሲያሻው ሊነጥቀን በማናስችልበት ማህበራዊ ልማት ውስጥ ኣይደለንም:: መብቶቻችን በየእለቱ በምንኖረው ህይወት ውስጥ ስር የያዙ መሆናቸው ኣጠያያቂ ነው:: ከፖለቲካ በመለስ ባሉ ጉዳዮች እንኳን ከራሳችን የተለዩ ሃሳቦችን ለመስማት ቻይ የሆንን፣ሃሳባችን ሲተች የኩርፊያና የሃሜት ቀስት የማናስፈነጥር ምን ያህሎች እንሆን ይሆን?

ለዲሞክራሲ ስንታገል ኖረናል:: ዛሬም እንዲሚላ እንታገላለን:: ትግሉ ግን የታጋዮቹን መታደስም ይመለከታል:: ዲሞክራሲን እየዘመሩ በኢዲሞክራሲያዊ ኣስተሳሰብና ኣሰራር በፓርቲ ደረጃ ጭምር መጠመድ ኣንድ ጥኑ ችግራችን መሆኑ ሊካድ ኣይችልም:: ዲሞክራሲያዊ ነኝ እያሉ በመረጃና በእውቀት መከራከርን በውይይት ኣለመግባባትን መፍታትን ለመለማመድ ኣለመጣር ይጋጫሉ:: ብዙ ሰዎችና ቡድኖች በዚህ ግጭት ውስጥ ይገኛሉ:: ዲሞክራሲያዊ ነን በሚሉ ማህበሮችና ድርጅቶች ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ኣወሳሰንን ኣክብሮ፣ ተመራጭን በየተወሰነ ዘመን ውስጥ እያደሱ፣ ወሳኝነት ባንድ ግለሰብ እንዳይሰባሰብ ኣድርጎ፣ ከኣመራሩ መርሃግብርና ፍላጎት ውጪ ስብሰባ የማስጠራት/የመጥራት መብትን ኣስከብሮና የኣመራሩን ስራ በየጊዜው ማወቅ መከታተልና መመርመር (ቃለጉባኤ ባስፈለገ ጊዜ እስከማየት ድረስ) የሚቻልበት ስርኣት ዘርግቶ በመንቀሳቀስ በኩል ድክመቶች ኣሉ:: የፓርቲ ኣመራር ላይ እኔ ካልተቀመጥኩ ፓርቲው እንዳይሆን ይሆናል ባይነት ከኢዲሞክራሲያዊነት ወይም ከፓርቲ የውስጥ ዲሞክራሲ የለሽነት ጋር የተያያዘ ነው:: በዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ውስጥ በልዩ ልዩ መድረኮች ሃሳብን ማንሸራሸርና ሃሳብን በሃሳብ መርታት ይቻላልና ፓርቲን ለመምራት ግድ ወንበር ላይ መተናነቅ ኣስፈላጊ ኣይሆንም:: ይህ በኛ ሃገር ገና ነው:: የዲሞክራሲ ደንቦች እንደ ወግ እቃ በህገደንብ ውስጥ ከመስፈር ባለፈ እውነተኛ መተዳደሪያ ሲሆኑ አይታዩም:: የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን በዲሞክራሲያዊ ባህርይ ኣርኣያ ሊሆኑ ቀርቶ ከድርብ አቋም የተላቀቁ አልሆኑም:: በይፋ ፕሮግራምና በመድረክ ላይ የሚንፀባረቅ

አፋዊ አቋም፣ በድብቅ ደግሞ የሚራመድ እውነተኛ አቋምና ባህርይ በብዙዎቹ ላይ ይታያል:: በዲሞክራሲያዊነት ለውጥ እንዳይቀጥሉ አንድ ትልቅ ችግር የሆነባቸውም ይህ ድርብ (dual) ባህርያቸው ነው:: በኣሜሪካና በኣውሮፓ ዲሞክራሲ ውስጥ የሚኖሩ ብዙ ፖለቲካ ቀመሶች የዚህ ችግርና የጥላቻ ፖለቲካ ተጠቂና አባዢዎች መሆናቸው ደግሞ ኣስከፊ ገጽታ ነው:: የብሄር ብሄረሰቦችን መብትና እኩልነትን እየዘመሩ ከስር ሙስናውን የሚያካሂዱ የክልሌን ወይም የብሄሬን ልጅ ዛሬ ካልጠቀምኩማ በሚል ኣስተሳሰብ የሚጓዙ ሰዎችን ለማግኘት ብዙ ድካም ኣይጠይቅም:: በጭፍን ጥላቻዎች ህሊናቸው የታመመና ህመማቸውን የሚያዛምቱ ሰዎች በህብረተሰባችን ውስጥ መኖራቸው ኣሌ የማይባል ሃቅ ነው::

«የሰው ልጅ ነፃ ሆኖ የሚወለድ ፍጡር ነው::» ይህ ታዋቂ ኣባባል ቁምነገር የሚኖረው የሰው ልጅ እንደሌሎች እንስሳት በደመነፍሳዊ ባህርይ ያልታሰረ የማሰብና አኗኗሩን የመለወጥ ተፈጥሯዊ ችሎታ (potential) ያለው ከመሆኑ አኳያ ስንመለከተው ነው:: የሰውልጅ በተፈጥሮ ያገኘው ድፍን ችሎታ ህይወት የሚያገኘው በማህበራዊ ኣግባብ ውስጥ ብቻ ነው:: ሰው ማህበራዊ ፍጡር ነው የሚባለውም ለዚህ ነው:: ማህበራዊ ኣግባቡ በቁሳዊና መንፈሳዊ ይዞታው ግለሰቡን ይቀርፅና ያሰማራል:: ግለሰቡም በደምሳሳው ለራሱና ለማህበሩ ህልውናና ቀጣይነት የሆነ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: የግለሰቡ ነፃነት መኖርም ሆነ መጥበብና መስፋት ከህብረተሰቡ የልማት ደረጃ ጋር የሚሄድ ነው:: የተባበሩት መንግስታትን የሰብኣዊ መብቶች ዝርዝር ኣንቀፆችን ያስተዋለ ሰው እንደኢትዮጵያ ድሃ ከሆኑ ሃገሮች ይልቅ በኣውሮፓና በኣሜሪካ ምድር ያለ ሰው ሰፊና ከስም ያለፉ ነፃነቶች እንዳሉት መረዳት ኣያዳግተውም:: ይህንን የተረዳ ሰው ለልማት የሚደረግ ትግል በሌላ ፈርጅ ለዲሞክራሲና ለሰብኣዊ መብቶች መሟላት የሚደረግ መሆኑ ኣይጠፋውም::

ትንሿን ምሳሌ እንውሰድ:: ከየግቢ በሚወጣ ቆሻሻ የኣጥር ውጪ ኣካባቢን መበከልና የፍሳሽ ቱቦን መድፈን በጤናማ ኣካባቢ የመኖር መብትን በገዛ እጅ መርገጥ ነው:: በተቃራኒው ከኣካባቢ ነዋሪ ጋር ተመካክሮና የኣካባቢን ፅዱነት ማስከበር የያንዳንዱ ሰው ጥቅም ነው:: ጥቅሙ በጤና በኩል ብቻ ኣያበቃም:: ይህን በመሰለው የልማት ተግባር ውስጥ ንቁ ተሳታፊነትን እየተለማመደ የመጣ ህዝብ በፖለቲካውም መስክ መብቱን ለማለት ብርታት ያገኛል::

በተገኘችዋ ቀዳዳ ትንሿን ሙስና ማጋለጥ ስንጀምር ትልቁንም ሙስና ለመታገል ድፍረት እናዳብራለን:: የወጣቱን ስራኣጥነት ለመቀነስ የሚካሄደውን ጥረት የተቃውሞ ሃይልን በማዳከሚያ ዘዴነት ከመውሰድ ይልቅ ልማትነቱን ማየትና ማገዝ ጤናማ ይሆናል:: በስራ መስኮች ውስጥ ትጉህነትና ስነምግባራዊነት እንዲሰፍን መጣጣርም <u>ለሰብኣዊ መብቶችና ለመልካም ኣስተዳደር መታገል ነው::</u>

ለሰው ልጅ ክብር መስጠትና ይህንን የሚቃረኑ ክፋቶችን የመታገል ተሞክሮ ማዳበር መንግስታዊ የሆኑ የህግና የመብት ጥሰቶችን ወደ መታገል ያደርሳል:: በመድሃኒትና በምግብ ሸቀጦች ላይ የሚከናወን ሃሰተኛ ስራ፣መርዛማ የፋብሪካ ውጤቶችን ወደ ወንዝ መልቀቅ፣ በእድሜና በስሜት ላልበሰለ ልጅ መኪና ማስያዝ፣ ያለበቂ ችሎታ መንጃ ፍቃድ መስጠት ወይም መቀበልና ንብረትና ሰው በግጭት እያጠፉ ችሎታን ማሻሻል ለራስም ይሁን ለሌላው ሰው ክብር ኣለመስጠት ነው:: በሴቶችና በልጆች ላይ ለሚደርስ ካስተዳደግ የመጣ መበላሸት ራስን ተጠያቂ ኣድርጎ ኣለመፀፀትና ከፀፀት አለመማር ለሰው ልጅ ያለንን ኣክብሮት ዝቅተኛነት ይጠቁማሉ:: በህፃናትና በታዳጊ ወንዶች ላይ የሚፈፀም ግብረሰዶምና የ9 ወር ጨቅላም የማይምር የሴት ልጆች ወሲባዊ ጥቃት መበርከት የባህርይ ለውጥ ከማድረግ ይልቅስ በዘግናኝ ጥቃት ብልግናቸውን ማርካት የቀለላቸው ሰዎች መኖራቸውንና የፈረንጆቹን ከወሲብ ጋር የተያያዙ የልሽቀት ህመሞች ለመከላከል ኣቅም ያጣን መሆናችንን ያመለክታል:: ስለ ኣድሏዊ የአገልግሎት ኣሰጣጥ እየተማረርን ግን በኣዲሱ ትውልድ መልካም ኣስተናነፅ ላይ ኣለመልፋት የሚጋጩ

ነገሮች ናቸው:: የታክሲ ረዳትን ዘለፋ ጠጥቶ የሚሄድ፣ እንደ እቃ ታጨቅ ሲባል የሚታጨቅና በመንገድ ሴብነትና ሌላ ኣይነት ጥቃት ሲካሄድ እንዳለየ ኣይቶ የሚያልፍ ሰው፣ሹም የሚሰራውን በደል ለመቃወም ሃሞት ይቸግረዋል:: ከቤት እስከ ደጅ ካሉና ትናንሽ ከሚመስሉ በደሎች ጋር ተስማምቶ የሚኖርና ለሰው ልጅ ያለው ኣክብሮት ዝቅተኛ የሆነ ህብረተሰብ ሰብኣዊ መብቶቹን በጥንካሬ ታግሎ የመቀዳጀትና ሳያስነጥቅ የማቆየት ኣቅሙ ማነሱ ኣይቀርም::

ዛሬ በየቀኑ የሚራቀቀው የመረጃ ቴክኖሎጂ ተራውን ዜጋ መረጃ ፈልፋይ፣ መዝጋቢና ኣስተላላፊ እንዲሆን የሚያስችል ነው:: ከኪስ ሳይወጡ ንግግርን ልቅም ማድረግ የሚያስችሉ የድምፅ መቅረጫዎች በኤሌክትሮኒክ ገበያ ውስጥ ተደርድረዋል:: የጉቦና የስርቆት ክንውኖችን፣በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን፣የቤትን በሃይል መደፈርና ድብደባን የመሳሰሉ የመብት ረገጣዎችን ሳይታወቅ በሞባይል ካሜራ መቅለብ የሚቻልበት ጊዜ ውስጥ ገብተናል:: የመረጃ ቴክኖሎጂን የተዛመደ ህብረተሰብ በሽፍንፍን ለሚካሄድ ዝርፊያና የመብት ጥሰት አይመችም:: አንድ ግለሰብ ላይ የተፈፀመ የፖሊስ ድበደባን የምታሳይ መረጃ ኣገር ያዳረሰ የቁጣ ማእበል ልትፈጥር የምትችልበት የዲሞክራሲና የሰው መከበር ዘመን በኢትዮጵያ ተረጋግጦ ማየት የሚፈልጉ ወገኖችም በየሙያቸውና በምክርቤት ተሳትፏቸው በምርጫ ሰሞን ውርውር ብቻ ሳይወሰኑ በሁሉም የልማት ግንባሮች ተዋዳቂ መሆናቸው ወሳኝ ነው::

## ብሄረተኝነትና ኢብሄረተኝነት

ጊዜው በዲሞክራሲና በግንባታ ላይ መረባረቢያ ቢሆንም ከብሄረተኝነትና ከኢብሄረተኝነት መስመር የሚመጡ ችግሮች እየተፈታተኑን ነው:: በብሄረተኝነት መስመር ውስጥ የብሄር ብሄረሰቦችን ተፈቃቅዶ መተሳሳር የሚያምነው «ዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት»፣ የብሄር ሃብት ለብሄሩ የሚል ብሄርተኝነት፣ ከባሰም መገንጠልን የሚጠይቅ ከዚህም ከመረረም በኢትዮጵያዊነት ላይ ጥላቻ ያዳበረ ወገን ያጋጥማል:: በኢብሄርተኝነት መስመር ውስጥ የሚታዩ አዝማማያዎች የኢትዮጵያዊነት ብሄርተኝነትን የተመረኮዙ ናቸው ማለት እንችላለን:: ዝርዝራቸው ብዙ ነው:: 1) የሚደረገው ኣንዱም የማይጥመው፣ ኢትዮጵያ ኣንድም ወዳጅ የሌላት፣ ሁሉም በሆዷ ያቀፈችውን ሃብት ኣውጥታ እንዳትጠቀም የሚመቀኟት፣ የምታምነው ቢኖር ፈጣሪዋን ብቻ የሚል ከሰማያዊ ተስፋ በቀር በሃዘንተኝነትና በጨለምተኝነት የተጨበጠ ኣመለካከት 2) የኢትዮጵያን የቀድሞ ስልጣኔና ገናናነት ውዳሴ የሚያጠብቅና የተቀነሰ ግዛትን ሁሉ ኣስመልሶ ኢትዮጵያን እንደነበረች ለማቆየት የሚያስብ፣ ያለውን መንግስት ከጠላት የሚቆጥር፣ ፅንፈኝነቱ ከፍ ካለም በብሄርተኝነትና በብሄር መብት ላይ ጥላቻ ያዳበረ 3) ለኣፉ የብሄሮች መብት መሟላትን የሚቀበል ግን የተረሳ ባህል ህይወት እንዲያገኝ መደረጉን ወደሂላ መሄድና ስልጣኔን መቃረን አድርጎ የሚያይ፣ ሌላው የመብት አተገባበርም የማይጥመው 4) ከመገንጠል በመለስ የብሄሮች መብት ታውቆ በእኩልነትና በዲሞክራሲ ተከባብሮ መኖር ይቻላል የሚል እምነት የያዘ 5) ዲሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶች ከተከበሩ ሌላው ችግር ሁሉ ይፈታል የሚል 6) ባሉት አስተሳሰቦችና ሲከሰቱ በነበሩ ተሞክሮዎች እየተረበሸ ከየት እንደሚሆን ግራተጋብቶ፣ ብቻ ምንም ሆነ ምንም ሃገር ተጠብቃና ሰላም ሆና የሚኖርበትን ሁኔታ እየተመኘ ያለ በብርካቴ ይገኛል::

በብሄርተኝነትም ሆነ በኢብሄርተኝነት መስመር ውስጥ የሚታዩት አዝማሚያዎች የጠራ ወሰን የሰሩና የጠጠሩ ሳይሆኑ እንደፋሳሽ የመዋለልና የመቀላቀል ፀባይ የሚታይባቸው ናቸው:: ሁለቱም የከረሩና ጥላቻ የጠገቡ የተገንጣይነትና የትምክህተኝነት ዋልታዎች ያሏቸውና ከነዚህ ሁለት ዋልታዎች በኩል እንደገመድ ጉተታ የሚሳሳቡ ናቸው:: እንደፓርቲዎች የግንኙነት ኣይነትና እንደሁነቶች ገርነትና መራራነት ከኣዝማሚያ ኣዝማሚያ ያለው የድጋፍ ክምችትና የስበት ሃይል ለውጥ ያሳያል:: ባንድ ወቅት ደንዝዞ

የነበረ ዝንባሌ በሌላ ወቅት ተነቃንቆ ሲዛመት ይገኛል:: ወደ ዲሞክራያዊነት ወደመቻቻል እያጋደለ ነው የተባለ ብሄርተኝነት ወይም ኢብሄርተኝነት በተቀየረ ሁኔታ ወደ ኢዲሞክራሲያዊነት፣ ወደ ጥላቻና ወደ ጠበኝነት ሲንሸራተት ተስተውሏል::

ሲጣሉ፣ ሲያጣሉና ሲያጋጩ የምናገኛቸው ብሄርተኝነትና ኢብሄርተኝነት አንዳቸው ያንዳቸው ሳቢና አበልፃጊ በመሆንም የሚረዳዱ ናቸው:: ብዙ ጊዜ ለብሄርተኝነት የምንሰጠውን የጠባብነት ባህርይ በኢብሄርተኝነት ውስጥም እናገኘዋለን:: በቅርፁ ሰፊ ሃገራዊ እይታ ያለው የሚመስለው ግን በእይታው ውስጥ ብሄሮችንና መብታቸውን ማስተዋል የሚፀናወተው፣ ከነበረው የተለየ አደረጃጀትን መምጣት እንደሃገር መናድ የሚቆጥረው፣ ለኣንድነት እታገላለሁ ቢልም ከናት ቋንቋው ውጪ የሌላ ብሄር ቋንቋ ማወቅ ለኣንድነት ያለው ጥቅም የማይገባውና ለብሄር ብሄረሰቦች አክብሮትን በመንሳት የሚጮህለትን ኣንድነት የሚቦረቡረው ዝንባሌ የግልብነትና የጥበት ቋት ነው:: በሆነ ነገር (በታሪክ በስልጣኔ በሃብት ወዘተርፈ) ላይ የተመሰረተ ኩራት ወደትእቢትና ሌላውን ወደ መናቅ ሲሸጋገር ትምክህት ይሆናልና የብሄረተኛ አስተሳሰቦችን አቅርበን ከተመለከትንም ከትምክህት ጋር የስጋ ዝምድና ሊኖራቸው እንደሚችል እናጤናለን:: ባንድ ብሄር ብሄረሰብ ውስጥ ትክክለኛው ወይም ዋናው የብሄሩ ክፍል እኔ ነኝ የሚል መታበይ ከክልልተኛነት ጋር ተጣብቆ ሊገኝ ይችላል:: ከዚህም ባለፈ ዋናው የሃብት ምንጭ ወይም የስልጣኔ መሰረት እኔ ነኝ የሚል ትምክህት ከብሄረተኝነትም ጋር ሊዛመድ ይችላል::

«ዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት» የሚባለው ኣስተሳሰብና የኢፌድሪ መደራጀት የትምክህተኝነትንና የብሄርተኝነትን በጥባጭነት ሊያመክንና ጉዳታቸውን ሊያደርቅ ኣልቻለም:: ኣሁንም ብሄርተኝነትና ትምክህተኛነት እየተጫጫሩ ጉዳት ያደርሳሉ:: ኣሁንም የብሄርተኝነት ንጠት ከፍና ዝቅ እያለ ይገኛል:: ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትም ቢሆን የተናጋበትን የዳርድንበር ሃይማኖተኛነትና የኣንድ ህዝብነት ኣመለካከት ባዲስ ራእይና ግንዛቤ የማደስ እርምጃው ገና እንደከመ ነው:: በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ዛሬም በታሪክ ሃብቶች ራስን ከማሞጋገስ አልተሻገረም:: ዛሬም የሄደ ግዛትን በግድም በሆነ በውድ ወደማስመለስ አስተሳሰብ ቀርቦ ይገኛል:: ዛሬም በተለያየ ስፍራ የሚገኙ ውህዳን የሚባሉ ወገኖች ባልታወቀ ኣንድ ጎደሎ ቀን ያልተጠበቀ ግጭት ተከስቶ መዘረፍ፣ መባረርና መገደል ይደርስብን ይሆን ወይስ ባእድነት ሳይሰማን መኖራችን ይቀጥል ይሆን? የሚል ጥያቄ አብሯቸው እየኖረ ነው:: ከኣፍ እላፊ ጨዋታ ተነስተው በብሄር ወደ ተባደነ ጥል የሚቀየሩ የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎች ውዝግቦችና በጌድኦ ውስጥ ተከስቶ የነበረው ሁከትና ጥፋቱ በህብረተሰባችን ማህበራዊ ኣብሮነት ውስጥ መጠገን ያለበት ስንጥቃት መፈጠሩን፣ <u>ይኸውም ባንድ ግለሰብ ላይ የተሰነዘረ ዘለፋ በሌሎች የብሄር ባልንጀሮቹ ላይ የተሰነዘረ ያህል እየመሰለ፣የአንድ ግለሰብ የአፍላፊ ጥፋትም በኣጥፊው ሰው ብሄር ወገኖችም የተፈፀመ ያህል ተደርጎ እየታሰበ መሆኑን ይጠቁመናል:: የዚህ ኣይነት ኣስተሳሰብ ባይኖር የግለሰቦች ፀብ በግለሰባዊነቱ በታየ ነበር</u>:: እስከ ግለሰብ ፀብ የወረደ ብሄረሰባዊ ወገንተኝነት በተለያየ ስፍራ እያዳገመ መንፀባረቁ በጥበትም ሆነ በትምክህት የሚመጣ ተንኳሽነትን ለማሳፈርና ወጣቶቹን ለመግራት የቻለ የፖለቲካ ሃይል አለመኖሩን ያሳያል:: በክርክር ሲበለጡ ኣናዳጅ ንግግሮችን እንደ መበለጫ መጠቀም፣ በክርክር ላይ ኣናዳጅ ንግግሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ በማወቅ በትግስትና በሂስ ከማረም ይልቅ በጉልበት ወደ መፍታት ፈጥኖ መዞሩ ዛሬም የችግር መፍለቂያ ድክመቶች ናቸው:: እነዚህን ድክመቶች ተጠግተው ጠባብ ብሄረተኝነትና ትምክህት የህብረተሰቡን መልካም ግንኙነት ይቆረጥማሉ:: ከዚህ አኳያ የሃገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች ፖለቲካዊ ኑሮ ገና አልሰከነም::

## ጥንተኛነት የትምክህት ጥሬ ሀብት

ጥንታዊ የሆነና የተለመደ ነገር ላይ ለውጥ ለማድረግ መሞከር ከኣሪምስ ስራ ወይም ከክህደት የሚቆጠርበት አመለካከት (obuscurantism) በኢትዮጵያ ውስጥ ረዥም

ታሪክ አለው። ለውጥን በመፃረርና በመቅጨት ለዘመናት ሲሰራ ኖሯል። ዛሬም ይኸው ድፍንቅል ጥንተኛነት ከሃቀኛ ኢትዮጵያዊነት፣ የሃገር ቅርስንና ማንነትን ጠብቆ ከማቆየት ጋር ራሱን ኣመሳስሎ ተሃድሶንና መሻሻያን በታሪክና በሃገር ላይ በደል ማድረስ አድርጎ ይፀናወታል።

የሩቁን ትተን ከቅርብ እንነሳ። ለኢትዮጵያ ኣንድነት መቀጠል ህይወት እስከመክፈል እንዋደቃለን ባዮች፣ በአረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለማት ላይ ኢፌድሪ (በኣዲስ የኣንድነት ምልክትነት) ያከለውን ውስን ጭማሪ መቀበል መከራ ሆኖባቸው ነበር። ዛሬም ገና አልዋጥ ያላቸው ጥቂት አይደሉም። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ከኣሁኑ ያለፈ ለውጥ ቢሹ ኖሮ ያንን መቀበል ለለውጥ ጠሎቹ ከኣድማስ ውጪ ይሆንባቸው ነበር። ኦሮሚኛ የግእዝ ፊደልን ትቶ የላቲን ፊደልን በመፃፊያነት ሲመርጥ የነበረው ኢትዮጵያን እንደመካድ የቆጠረ ጫጫታ አይረሳም። ነገር ግን የግእዝ ፊደል የነበረበትን የፊደል ትርፈትና ያቀጣጠል መፋለስ ኣርሞ የተሻለ የተመራጭነት እድል እንዳያገኝ የከለከከሉት ራሳቸው የለውጥ ተፀናዋቾቹ ነበሩ። የኣማርኛን ፊደል የማሻሻል ጉዳይ በደርግ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚነሳ ነበር። በባህል ሚንስቴር የቋንቋ ኣካዳሚ በኩል የተካሄደውና ትርፍ ፊደሎችን ከመቀነስና የግእዝ ረድፍን ንባብ ከማስተካከል ያልራቀው ለውጥ እንኳ ይፋ ለመውጣት የኢህኣዴግን ዘመን ጠብቋል። በደርግ የመሰረተ ትምህርት መርሃግብር ውስጥ ፊደል ላልነበራቸው ቋንቋዎች በግእዝ ላይ ተመስርቶ ፊደል በተቀረፀላቸው ጊዜ (በተጠቀሚው ልማድ ላይ ግርታ ይፈጠራል/ ተቀባዩ ይቃወማል የሚል ኣንዳች ችግር በሌለበት አዲስ ሁኔታ ውስጥ ) ቅጥያዎቹ ስርኣት የገቡ  የፊደል ገበታ ማዘጋጀት ሞት ሆኖ በኣማርኛና በግእዝ ኣፃፃፍ ላይ ያሉ የቅጥያ ችግሮች ወደሌሎችም ቋንቋዎች እንዲዛመቱ ተደረገ። ያ ሁሉ የመሰረተ ትምህርት ልፋትም መና ቀረ።

ታፍኖ ኖሮ በቅርቡ የወጣው ውሱን የፊደል ማሻሻያም ቢሆን በመጠኑ በትግሪኛ እንጂ በአማርኛ ውስጥ እየሰራ አይደለም። ህፃናት ጥቂት ግንድ ፊደሎችና ቅጥያዎች (ለምሳሌ በኣማርኛ ቢበዛ 27 ግንድና 7 ቅጥያ፣ በድምሩ 34 ብቻ) መማር ሲገባቸው በመቶ ቤት ውስጥ የሚቆጠሩ ፊድሎችን በመማር ብዙ ጊዜ ያጠፋሉ። እንደችግሩም ከሆነ የምን ፊደል መቀነስ ብቻ የቅጥያዎች የስርኣት ብልሽት መስተካከል ኣለበት የሚል የለውጥ ግፊት መምጣት በተገባው ነበር። ግን በለውጥ ተፀናዋቾቹ ወገን ትንሺም ማሻሻያ ከሃጢያት ተቆጥራ የተባበሩት መንግስታት በቅርስነት የመዘገባቸውን የኢትዮጵያ ፊደሎች ወያኔ እያጠፋ ነው የሚል የቅዋሜ ትግል ተፈጥሮባታል።

የኢትዮጵያ «ሚሊኒየም» አከባበር ዝግጅት ጽ/ቤት ይጠቀምበት በነበረ ምልክት ላይ የምንሰናበተውን ሺኛ ዓመት የሚያመለክተው ቁጥር «2» በመሆኑ የኢትዮጵያን «ሚሊኒየም» እናከብራን እየተባለ የኢትዮጵያን ቁጥር ትተን እንዴት በኣረብኛ ቁጥር እንጠቀማለን የሚል ቅዋሜ ኣስቸግሮ «2» ወደ «፪» ተቀይሯል። ሚሊኒየምን በኣማረኛ ለመግለፅ ሺኣመት የሚያንሰው ሆኖ «እስራ» «እልፍ!» እየተባለ ካንዱ ወደሌላው ይታይ የነበረው መዛለል የሚያስገምት ነበር። ወደ ቁጥሩ እንመለስ። ኣረቦች ለኣለም ያበረከቱትና እኛም የራስ ያህል ተቀብለን እለት በእለት የምንሰራበት ቁጥር እንደባእድ ሲቆጠር፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ረዥም ዘመን ከመኖሩ በስተቀር ጥንት ከውጪ የተወረሰውና ከሃይማኖት ጽሁፎች ውጪ እየሰራ የማይገኘው፣ ስለዚህም ብዙ ሰው አጣርቶ የማያውቀው፣ ህፃናትም ላይጠቀሙበት ከሳባ ፊደል ጋር የሚማሩት ቅልጥፍና የለሽ ቁጥር ኢትዮጵያዊ ተባለ። የዚህ ኣይነት ጥንተኛነት  ኣላላውስ ባይነቱ እስከመቼ እንደሚቀጥል ያሳስባል። ኣለም በሰፊው ከሚሰራበት አቆጣጠር 7/8 ኣመታት የሚጎድለው አቆጣጠር ሙጥኝ ብለን ወዲህና ወዲያ አመታት በመቀየር ስለምን እንቸገራለን የሚል ጥያቄ ከዚህ ቀደም የተነሳ ቢሆንም መነጋገሪያ ሳይሆን ተዳፍኖ የቆየው ጥንተኞቹ ሊያያይዙ የሚችሉት ቅዋሜ ተፈርቶ ነው።

ፈረንጅ በማህበራዊ ስነሰብእ-ኢትኖሎጂ ጥናት በሚያናፍሰው ውዥንብር እየነፈዙ የሳይንስና የቴክኖሎጂን አቢዮት ለነጭ ትቶ አሮጌና ጎታች ትውፊትን ከአፍሪከኛነት ጋር

እያዛመዱ በስነፅሁፍና በፊልም ውስጥ ዛርና መናፍስት ውላጁን፣ ድግምትና ንግርቱን መደንቀር እንደኣዲስ ፈሊጥ እኛም ኣገር እየመጣ ነው።

ከክርስቶስ ጋር ዝምድና የሚያስገኘው ንግስተ ሳባ ከንጉስ ሰለሞን የፀነሰችበት ኣፈ-ታሪክ፣ ነገስታት ሰማያዊ ተልእኮ የፈፀመብትና ቅድስናን ያገኙበት ገድል ኣዲስ ጉልበት ኣግኝቶ ኣስተሳሰብን ሲያጣብብ ይገኛል። ሃይማኖትን መቀየር ግላዊ መብት መሆኑን መቀበል ኣስቸግሮ ዛሬም ከክፉ ክህደት ሲቆጠርና ከወዳጅ ዘመድ ሲያቆራርጥ ይታያል።

በኣብይ ፆም ጊዜ ቀድሞ የልኳንዳ ስጋና የፍስክ ምግብ በሆቴል ማግኘት ችግር ያልነበረበት ሁኔታ የሂሊት ተመልሷል።

የትምህርትና የምሁርነት ህይወት ደቅቋል። ሃሳብን በሎጂክ ማውረድ ይቅርና ርእስ ጠብቆ መናገር ችግር ሆኗል። ርእስ ለማስጠበቅ መሞከር በ«ኣፈንክኝ»ባይነት የሚያስቆጣና የሚያስኮርፍ ኣስር ቦታ እየረገጡ ማውራት የሚኮራበት ሆኖ ይገኛል።

አጣርተው የማያቁት ነገር ላይ የምንነት መግለጫ (definition) ሰጪ መሆን፣ ግምትን ወይም በጥራዝ-ነጠቅነት ያገኙትን ያለቀለት እውነት አድርጎ ማቅረብ፣ በመሰለኝ የሆነ ቁጥር አንስቶ በመቶኛ መናገር በማያሳፍር ደረጃ እስከ ተራው ሰው ድረስ ተዛምቷል። በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት የለኝም፣ የሰማሁትን ወይም የመሰለኝን ያህል ልናገር ብሎ ማለት፣ ተሳስቶም ስህተትን መቀበልና ይቅርታ መጠየቅ እራስን ከማሳነስ መቆጠሩ ብሷል። የእንግሊዝኛ ቃላት መወታተፍና የማያቁትን የሚያቁ «መስሎ» እንዳገኙ መቅደድ የኣዋቂነት ማስመስከሪያ ሆኗል። ስለወቅታዊ ጉዳዮች፣ ሰለልማት፣ ሰለጤና ወዘተርፈ ህዝብን ሊያስገነዝቡ በመገናኛ ብዙሃን ቀርበው የማያግባቡ የእንግሊዝ ቃላት የመሰግሰግ ድፍንቅልነት የሚያስጀንን ሙያ ሆኗል። «ሙያው» ከመለመዱ የተነሳ የተለቃቀመ የእንግሊዝኛ ቃላት እየሰኩ መናገር ቀለም ባላየው ዜጋ ሁሉ እንደፈሊጥ ተይዟል። እንዲሁም «ኣማርኛ በእንግሊዝኛ እንዲወረር የተደረገው ሆን ተብሎ ኣማርኛን ለማጥፋት የተቀነባበ ሴራ ስላለ ነው» የሚል ፖለቲካዊ ትርጓሜ አስገኝቷል።

በግልጽ የመነጋገርና የመከራከር ጥረት ገና አበረታች አቀባበል አለገኘም። በሃሜት ውስጥ መዋኘት፣ ያንድን ሰው ፍላጎት ከድርጊቱና ከንግግሩ ከመገመት በስተቀር ፊት ለፊት ጠይቆ ማወቅን መራቅ፣ ከሰው ኣንድ ነገር ፈልጎ በቀጥታ ከመጠየቅ ይልቅስ ዙሪያ ጥምጥም መሄድ ወይም በውለታና በገፀበረከት መጠጋት ዛሬም እንደነበረ ይገኛ ል። በፖለቲካው ሜዳ የሚንፀባረቀው ባህርይ በዚህ ሁሉ የሚወሰን ነው።

በትምህርት ኣለም ያለው ኣዲስ ትውልድ ይህንን የሚለውጥ የተሃድሶ ተስፋ እንዳይሆን የምሁራኑና የፖለቲካ ሃይሎች ችግር ትምህርትቤትም ላይ ይንፀባረቃል። ከሃገር ውስጥ በኩል አሮጌና ኣባይ ኣስተሳሰብ፣ኣሽሙረኝነትና ኣሉባልተኝነት በሞላበት የባላጋራ ፖለቲካ ወጣቱ ይላሳል። ከውጪ በኩል፣ በበታችነት ስሜት ኮራጅ እንዲሆን ያደረገው የባሕርማዶ የባህል ጎርፍ ዱለኛ የኪስ ቲፎዞነትን ኮርጆ አስከመተግበር ድረስ አመንምኖታል። የማሰብ ልምምድ ዋና መሳሪያ የሆነው የቋንቋ ትምህርት ሃሳቦችን/መረጃዎችን የመፈልፈል፣ የማበጠርና በየዝምድናቸው የማያያዝ ክህሎቶችን አከርካሪው ማድረግ ያልቻለ ነው።* እንግሊዘኛ አሁንም ተማሪዎች የማይግባቡበት

---

* እግረመንገዴን ሌላም ኣሳሳቢ ችግር ልጥቀስ። የፌዴራል የስራ ቋንቋ የሆነው ኣማርኛ በትምህርትነት እየተሰጠ ያለበት ሁኔታ በተለይ በሁለተኛ ደረጃና በ11ኛ-12ኛ ደረጃ የ«ተማር ኣልማርም» ትግያ ባህርይን ይዟል። ኣማርኛን በሁለተኛ መግባቢያነት የማያቅ የገጠር ተማሪ በቁጥር ሲጨምር እየታየ ነው። ኣማርኛን የፌዴራል የስራ ቋንቋ ለመሆን ያበቃው በታሪክ ኣጋጣሚ የብዙ ብሄር ብሄረሰብ ተነጋሪነትን ያለተወዳዳሪ ማግኘቱ ብቻ ነው። ይህን ማሟላት ሲያቅተው ወይም የሚተካው ሲመጣ መሰናበቱ

ማስተማሪያ እንደሆነ ነው። ከኣፀደህፃናት ጀምሮ በት/ቤት ውስጥ «በእንግሊዘኛ ብቻ ተናገሩ» ወይም «ሙሉ ትምህርት በእንግሊዘኛ» የሚሉ ትምህርት ቤቶችን የወለደውም ይህው ችግር ነው። (ተማሪዎች መሰረታዊ የመግባቢያ ቅንብሮችን እያጠኑ እንዲሰሩባቸው በማስለመድ ላይ የተመሰረተ ስልት ተግባራዊ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ግን ክህሎቱን ለማስጨበጥ እስከ 8ኛ ክፍል ያለው የእንግሊዘኛ ክፍለ ጊዜ በቂ ነበር፣ ያውም ሲበዛ።) የትምህርትቤት ውስጥ ክበቦችም ቢሆኑ ተማሪዎችን ባለክህሎቶች በማድረግ በኩል ጥሩ ውጤት እንዳያሳዩ የመንግስትን ፍላጎት፣ አቋምና እቅድን የማራመጃነት አላማ ያጠቃቸዋል። ያድርባይነትና የሙስና መማሪያነታቸው ያመዝናል።

መምህርንና መንግስትን «በመዳፈር» ሳይሸማቀቁ አዲስ ነገር መፈለግ፣ መጠየቅ፣ መመራመር፣ መከራከር የትምህርቱ ትርታ አልሆነም። በሁለተኛ ደረጃ ይቅርና በኮሌጅ ደረጃም ይህንን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚሞክር ተማሪ በነጥብ ሊቀጣ ይችላል። በማስተርስ ደረጃ ያለው የትምህርት አካሄድም ገና ኣጥንቶ ከመፈተንና ከመኮረጅ ኣልተላቀቀም። ያለ መግቢያ ፈተና የመንግስት ወረቀት ኣቅርበው ሰተት የሚሉ ልዩ ተማሪዎችም አሉበት።

ያም ሆነ ይህ ጭፍን የባህርማዶ ቀጂነትንና ጥንተኛነትን ከሁለት አቅጣጫ አየታገሉ የኣመለካከትና የባህል ተሃድሶ ማካሄድ መልስ ያጣ ጥያቄ ነው። ጭፍን የባህርማዶ ቅጂነት በሥልጣኔ ከመራመድ ጋር ኣንድ ሆኖ በኩራት አየተስፋፋ መሆኑ ጥንተኛነትና ትምክህተኞችም እውነተኛ የኢትዮጵያ ጠበቃ እኛ ነን ከሚል ማማ ላይ እስከዛሬ አለመውረዳቸው የፖለቲካ ሃይሎቻችንን ጥኑ መሃንነት የሚያጋልጥ ነው።

**ብሄርተኝነትና አዳላጭነቱ**

በኢትዮጵያችን ውስጥ ብሄርተኝነት በ«ዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት» ስም ተሹሞ በስፋት የሚገኝ እንደመሆኑ አዳላጭነቱን ጠጋ ብሎ ማየት ጠቃሚ ነው።

- በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እቅዶች የብዙ ሰዎችን ጥቅም ኣቀራረቦ መያዝና ብዙዎችን ለመሳብ መብቃት ከባድ ስራ ነው። ከዚህ ጋር ሲተያይ በብሄርተኝነት ተባድኖ ድጋፍ መፈለግ ከሁሉም የቀለለ ነው። የፖለቲካ ትግል ልምምድ ትንሽም የሌላቸው፣ ይህ ይቅርና የፖለቲካ ንድፈሃሳባዊ ኣስተሳሰብ ያላበጁ፣ ሰዎች ፕሮግራም ልትባል የማትችል ወረቀት አዘጋጅተው ብሄረተኛ ብሶትን እንያንጎራጎሩ የብሄር ድርጅት ነኝ ሲሉ ኣጋጥሟል። የብሄረተኛ መንገድ የሚጋጩ ኣስተሳሰቦች ያላቸውን ሰዎች፣ ዲሞክራቶችንና ፀረ ዲሞክራቶችንና ፋሽስታዊ ዝንባሌ ያላቸውን ጭምር በብሄር ተቆርቋሪነታቸው ብቻ ኣብረው መንጋፈፍ እንዲችሉ የተመቸ ነው። ብሄረተኛ አስተሳሰብና ኣደረጃጀት በተዘረጋበት ስርኣት ውስጥ ምርጫ ቢካሄድም መራጩ ህዝብ ፓርቲዎችን ባላቸው ፕሮግራም ከማማረጥ ፈንታ ባመዛኙ ብሄር ብሄረሰቡን «ይወክላል» ለተባለ ቡድን እጩዎች ድምፁን የመስጠት ሁኔታ ውስጥ ይወድቃል።
- ኣመለካከቱ ሙሉ ለሙሉ በብሄርተኝት ገደብ ውስጥ የገባ ሰው ብሄሩን ከሌላ ብሄር ጋር በእኩል ኣይን ለማየትና ለመመዘን ይሳነዋል። የብሄሩን ወግና ባህል በሂስ ኣይን ከማየት ይልቅ እንደወረደ መካብ ያጠቃዋል። የብሄሩን ባለታሪኮች ጥሩ ስራቸውን የማብዛትና ድክመታቸውን የመከለል/የማሳነስ ፍላጎት ይስበዋል። የበላይ ከነበረ ብሄር ወይም ገዢ መደብ ጋር ብሄሩ የነበረውንና ያለውን ታሪክ በመረዳት ረገድም በደልና ጥቃትን የማነፍነፍና ከዛ አኳያ አዛብቶና ኣጡዞ

---

ግድ ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ ግን የሚያሳስበው ከኣማርኛ ጎን በብዙ ብሄርብሄረሰብ የመነገርን እድገት በማግኘት ላይ ያለ ሌላ ሃገርኛም ሆነ ኣለማቀፍ ቋንቋ ኣለመኖሩ ነው።

የመተርጎም ፍላጎት የምልከታና የማሰብ ሚዛኑን እየታገለ ያስቸግረዋል:: ብሄራችን ተበድሏል እነዚህና እነዚህ ኣልተሟሉለትም የሚባለው ነገር ብዙ ኣየር እየተሞላ ኣንዳንዴም የትግሉ ሁለንተና ሆኖ ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ጋር የሚያገናኙ ኣበይት ጥቅሞች እንዳይጤኑ ሊሸፍን የሚችለው ከዚህ የተነሳ ነው:: ከሌሎችጋር ያለው የኣብሮነት፣ የእኩልነትና የልማት ትግል ምልከታ ውስጥ ሳይገባ የሚካሄድ የድሮና የዘንድሮ የበደል ድርደራ ወደ ቅያሜ የሚያንሸራትት ድጥ ኣለው:: ከትምክህት ወገኖች ጋር መተራረብ ታክሎበት በፈላ ስሜት መታወር ሊከተል ይችላል:: በሃገራች ተሞክሮ መሰል ችግር እንግዳ ኣይደለም::

- የብሄር ብሄረሰብ ካባ መጎናፀፍ የብሄር ወገንተኝነትን ያጠበቀ ስሜታዊ ድጋፍ የሚገኝበት ጥሩ መደበቂያ መሆን ስለሚችል ስልጣን ፈላጊዎችና ሙሰኞች ሽፋን ኣድርገው ይነግዱበታል:: እነሱ የፈጠሩት ድርጅት የያዘውን ኣቋም የብሄር ብሄረሰቡ አቋም ያደርጉታል:: ድክመታቸው ሲተች በነሱ ላይ የተወረወረውን ትችት ብሄር ብሄረሰባቸው ላይ እንደተወረወረ ኣድርገው ለማምታታት ይመቻቸዋል:: «ድሮም ... ... እየተባልክ ትዘለፍና ትናቅ ነበር ዛሬም ይሀው ...» እያሉ ስሜት ውስጥ መክተት የተለመደ ዘዴያቸው ነው:: ለማምታታትም ጠቅሚቸዋል:: ምክንያቱም ብሄረተኛ ተቧድኖና እንቅስቃሴ የቡድን ማንነትና ፍላጎትን ከብሄር ብሄረሰብ ማንነትና ፍላጎት ነጥሎ በማየትና በመረዳት በኩል የበኩሉን አሳሳችነት ይፈጥራል:: ብሄር ብሄረሰብን በደፈናው ስራዬ ብሎ የሚያወግዝና የሚሳደብ የከተማ እብድ በኢትዮጵያ ሊታይ የቻለው (ከደርግ ውድቀት በሂላ ) ከዚህ አሳሳችነት የተነሳ ነው::
- ለቅስቀሳ የሚውለው በደል ወይም ፖለቲካዊ ጉዳይ ሁሉንም ብሄር ብሄረሰብ የሚመለከት ሲሆን እንኳ የሁላችንም ችግርና ጥቅም ነው ከማለት ይልቅ የብሄረተኛ ትግል የራሱን ብሄር ብቻ የሚመለከት ኣስመስሎ በተናጠል የመጮህ ፀባይ ያጠቃዋል:: የፖለቲካ ጥያቄ የተናጠል ብሄርተኛ ጩኸት ሲሆን ሌላው ወገን የራሱ ብሄርተኛ ንቀናቄ ወይም ሌላ የትግል ኣማራጭ ከሌለው በስተቀር ድርሻው ተመልካችነት ይሆናል:: የብሄርተኛ ንቅንቄ በተፈጠረበት ኣካባቢ ያለ ውሁድ ህብረተሰብ በተለይ ገፎ የሚባል ብሄር ኣባላት በተመልካችነት ላይወሰኑና ምንም በደል ባይደርስባቸውም የብሄረተኛ እንቅስቃሴ መፈጠሩ ብቻውን ስጋታቸው ሊሆን ይችላል:: ብሄረተኛ እንቅስቃሴው ክልላዊ ስልጣን ሲይዝም ስጋታቸው ይቀጥላል:: ትምክህትም ሰለባውን ያበዘል:: የብሄርተኛ ትግሉ ተገንጥሎ የመውጣትን ጥያቄ የጨመረ ከሆነ ደግሞ መገንጠልን ከማይደግፍ ወገን ጋር በሞላ መቃረን ይፈጠራል፤የብሄር ብሄረሰቦች የትግል ሃይል ይከፋፈላል::
- የትኛውም ኣይነት የብሄር ብሄረሰብ ብሄረተኛነት በውስጤ ያለ ሃብትና ጥቅም ቅድሚያ ለብሄር ወገኔ ይሁን የማለት ቁልቁለት ኣብሮት ይኖራል:: በዚህ ቁልቁለት ከተንደረደሩ ማረፊያው ኣድሎኝነት ነው:: እዚህ ውስጥ ከተወደቀ ከሌላው በበለጠ ለብሄር ብሄረሰብ ወገን መታመንና ከሌላው አብልጦ የብሄር ብሄረሰብ ወገንን ማቅረብና መጥቀም ይመጣል:: ጥቅቅሞሹ በግልፅና በድብቅ መንገድ ወደልዩ ልዩ የስራ መስክ፣ወደትምህርት ምዘና፣ ወደኢንቨስትመንትና የመሬት ምሪት ሊሻገር፣ የፖሊስና የዳኝነት ስራን ሊበክል ይችላል:: ሲበክልም ታይቷል:: የኣድሎኝነት ችግር መኖር ከ«ሚዳላለት» ብሄር ውጪ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ቅሬታ ላይ ይጥላል፣ የእኩል ዜጋነት እምነታቸውን ይሰብራል:: ትምክህተኛና ተቃራኒ የሆኑ የፖለቲካ መስመሮችን ያነሳሳል:: ኣድሎ ባልተፈጸመበት ስፍራና ጊዜም በይሆን ይሆናል መጠራጠርና ማማት እንዲራባ ያደርጋል:: ሃሜቱ ደግሞ በፋንታው የብሄርተኛ ሹምን እልህ እያጋባ ማናለብኝነትንና ኣድላዊነትን ያባብሳል:: ይህ ሁሉ የኣካባቢውን ሰላማዊ ኑሮና ልማት የሚበድል ነው::

በደሉ በዚህ ብቻ የተወሰነ ኣይደለም:: «የሚዳላለት» ብሄር የተጠቃሚነት ስም ይትረፈው እንጂ ተበዳይነቱ በእሱ ይብሳል:: ኣድሎን ፈቅዶ እስከተቀበለው

ወይም እስካልተቃወመው ድረስ የነፃነትንና የእኩልነትን ጣፋጭነት ማጣጣም ኣይችልም። በራሱም ላይ ኣድሎ ይጠራል። በብሄር የተጀመረው ማዳላት የዘመድ፣ የትውውቅና የሽርክና ድር እየሠራ ይስፋፋልና «የብሄር ወገኖች»ም የኣድሎ ተጠቂነት ኣይቀርላቸውም። እንዲያውም «የብሄር ወገኔ» «ለብሄሬ የቆመ» ባይነት ሚዛናዊ ኣስተውሎቱን እያደበዘዘበት የጥቅመኞች መነገጃ መሆኑን ለማጤን ከሌላው የበለጠ ጊዜ ሊወስድበትና ብዙ ሊጠቃ ይችላል።

- በኣድላዊነትና በጥበት ስሙ የጎደፈ የኣስተዳደር ኣካባቢ ወደስፍራው ሊመጣ የሚችለውን ተወላጅ ያልሆነ አልሚ የማስቀረት ጉዳትም ያስከትላል። የክልል ልማት በክልል ተወላጅ የሃገርም ልማት በሃገር ተወላጅ የሚያልቅ ኣይደለም። በዛሬው የግሎባላይዜሽን ዘመን ልማት ሊሳካ ከተፈለገ ባለሃብትንና ባለቴክኖሎጂን ከየትም ይሁን ከየት እየሳቡ ልማትን እንዲያስፋፉ ኣድርጎ የመንከባከብ ብልህነት ነው። <u>ሃገርነት ይቅርና ኣህጉርነት ጠብቦ የብሄር፣ የሃገርና የኣህጉር ድንበር ሳይገድባቸው በተያያዙ ጥቂት ግዙፍ ኩባንያዎች ስር በምትመራ ኣለም</u> ውስጥ ሆነን የብሄር ብሄረሰብ እድልንና ልማትን በትንሽ ክልል ደረጃ ከማሰብና «የብሄር ኣባሎቻችን ክልላችሁን ኣልሙ» ከሚል ጠባብ ማእቀፍ ማለፍ ኣይበዛብንም። በዚህ ኣቅጣጫ ከታሰበ ሃዋሳ ከተማ የደቡብ ብሄር ብሄሰረቦች ክልል ዋና ከተማ ስትሆን ከሁሉም በበለጠ የልማት ማእከል መሆናቸውን በማስተዋል ሲዳማዎች መደሰት ይገባቸዋል። ሁሉም ዜጋ መልካም ውሃ እንዲጠጣ፣ የትኞቹም አካባቢዎችና ወንዞች ከብክለት እንዲፀዱ፣ ሁሉም ከተሞች ቆሻሻና ፍሳሻቸውን ለገጠሩም ሆነ ለከተማው ጤና ችግር በማይሆን ዘዴ እንዲያስወግዱ ከማሰብና ከመታገል ፈንታ ኣዲስ ኣበባ በኦሮሚያ ውስጥ በመሆኗና የመጠጥ ውሃና የፍሳሽ ኣገልግሎቷ በኦሮሚያ ላይ የተደገፈ ስለሆነ ክፍያ ልትፈፅም ይገባል የሚል ኣስተሳሰብ ዘንድሮም ያላቸው ካሉ ወደ ሂላ ቀርተዋል። «በክልሎች ውስጥ ፌዴራላዊ መንግስት ለኢንቨስትመንት መሬት ሲወስድ ኪራይ ይከፍላል ወይ?» የሚል ጥያቄ በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ መነሳቱም ኣስገራሚና የማይጠበቅ ይሆናል። በፌደራል መንግስት የድጎማ ገንዘብ ድርሻ ስሌት ላይ ከመብሰልሰልም በኣጠቃላይ የልማት ስርጭት ሚዛናዊነትና እድገትን የማጠጋጋት ጥረት ረገድ እየተሰራ ያለውን መመርመር ይበልጣል።
- የድርሻ ጉዳይ ሌላ ኣይነት መንፀባረቂያም ኣለው። በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የኢኪኖሚ ሃብት ክፍፍል ከብሄር ብሄረሰብ ኣኳያ የሚያሰሉና የኣማራ፣ የጉራጌ፣ የትግሬ፣ የኦሮሞ፣ ሃረሬ ወዘተርፈ ምን ያክል ሃብታም ኣለ ምን ያክል ካፒታልስ ደርሶታል እያሉ ከህዝብ ብዛት ጋር የሚያነፃፅሩ ተፈጥረዋል። የዚህ ኣይነት ኣሰላል ህብረተሰብን ለማቃቃር የሚውል መበላለጥን እየፈለጉ ከማቅረብ በስተቀር የሚሰጠው ጥቅም የለም። ሰንጠረዥና ቀመር ሰርቶ የዚህ ወገን ድርሻ በዝቷልና ከዚህ ወደዚህ ይቀነስ ወይም የዚህኛው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ቆሞ የዚህኛው ይስፋ ሊባል ኣይችልም። ያልተመጣጣነ እድገት ኣጠቃላይ የሰው ልጅ ታሪክ ባህርይ ነው። ማድረግ የሚቻለው ኣድላዊነት መወገዱንና ኣቀራራቢ የልማት ፖሊሲ መኖሩን በትግል ማረጋገጥና በዚያ ውስጥ መጣር ነው። የዚህ ኣይነት ፖሊሲ ተይዞ ሲጣርም እንኳ ከኣድሎ ውጪ በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች መበላለጥ መከሰቱ ኣይቀርም።
- የብሄርተኛ የድርሻ ስሌት በፖለቲካ ስልጣንም ውስጥ ይገባል። በኦ.ነ.ግ. አካባቢ ኦሮሞዎችና ኦሮሚያ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ሁሉ በፖለቲካውም ቁልፍ ሚና ሊይዙ ይገባል የሚል ኣመለካከት ኣለ። የህወሃቶችን ገዢነት ተገቢ ኣለመሆን ለማመልከት ሲባልም የትግራይ ህዝብ ቁጥር ተደጋግሞ ሲጠቀስ ይሰማል። እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው ኣስተዋፅኦና በቁጥሩ ብዛት ልክ የስልጣን ድርሻው ይመጠን የሚባል ከሆነ የሚወራው ስለዲሞክራሲ ኣይሆንም።

በዲሞክራሲና በኢኮኖሚ ግንባታ ትግሉ ውስጥ ኦሮሞዎች የአሰባሳቢነቱንና የአንቀሳቃሽነቱን ቁልፍ ሚና መጫወት ኣለባቸው ማለት ተፈልጎ ከሆነ የኦሮሞ

ፖለቲካዊ ምሁራን በደንብ ያላስተዋሉትን ሃላፊነት የሚያስገነዝብ ትልቅ እውነት ነው። ዋና ታጋይና አታጋይ መሆን በስልጣን ወደ መምራትም ይወስዳል። በኣራቱም መኣዘን ከመሃል እስከዳር በሰፊ መልከኣምድር ተሰራጭቶና ኣብላጫውን የብሄር ቁጥር ይዞ መገኘትም በርካታ የስልጣን ወንበር ለማግኘት የሚመች ነው። የምንነጋገረው ስለዲሞክራሲዊ የመንግስት ስልጣን ከሆነ የድርሻ ስርጭቱን በስተመጨረሻው የሚወስነው የህዝቦች ድምፅ ነው። እራሱን በራሱ እያረመና እያጎለበተ የሚራመድ ዲሞክራሲ እስካለና ምርጫና የምርጫ ውጤት እስከተግባቡ ድረስ የየትኛውም ብሄር ብሄረሰብ አባላት የስልጣን ወንበር መበርከት/ማነስ ወይም ርእሰብሄርነትን መያዝ ችግር ኣይሆንም። ችግር የሚመጣው የትንሽም ይሁን የትልቅ ብሄር የበላይነትን እንደመብት/እንደስርኣት ለመዘርጋትና ለማቆየት ሲፈለግ ነው።

የመምህር ገብረኪዳን ደስታ አስተሳሰብ ከላይ በአነሳነው ችግር የተጠመደ ነው። እጠቅሳሁ።

> «ብሄረ ትግራይም የባህል፣የታሪክ፣የአንድነት፣ የጅግንነት፣የመቻቻል የእኩልነት፣ የአልበገር ባይነትና የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኔ እምብርት እንደሆነች ሁሉ፣ካብያ ነበረኒስ እኒህኒ’ ነውና ዛሬም ያለፈውን ታሪክ ለመድገም የስራ፣የባህል፣የእውቀት፣የምርምር፣የአንድነት፣የእድገትና የብልፅግና ማእከል ሆና መቀጠል ይኖርባታል። እነዚህ ነገሮች ተግባራዊ ሳይሆኑ ከቀሩ ግን፣በትግራይ ህዝብ የዓመታት ታጋድሎ፣ ጅግኖች በከፈሉት ክቡር የሕይወት መስዋእትነት የተጎናፀፍነው፣ብሔራዊ እኩልነትና ሃገራዊ አንድነት፣ለትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች መጋለጡ አይቀርም» ( የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ ፣ 9-10)

ትግራይ የብዙ ነገር ማእከል ሆና መቀጠል ኣለባት በማለት ውስጥ የስልጣን መሪነቱም ከእኛው መውጣት የለበትም የሚል ኣስኳል አለ። የመከራከሪያ ነጥቦቹ ሁለት ናቸው። ቀድሞም ትግራይ ማእከል ነበረችና ዛሬም ማእከል ሆና መቀጠል ኣለባት፣ማእከል ካልተሆነ ለደመኛ ጠላት መጋለጥ ይመጣል የሚሉ ናቸው።

ኣብዩ ስህተት የሚገኘውም በመከራከሪያ ነጥቦቹ ላይ ነው። ጥንት ማእከል ስለነበርን ዛሬም ማእከል መሆን ይገባናል ባይነት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋናውን ድርሻ የሚያበረክተው የኔ ብሄር ነውና የስልጣን ዋና ባለድርሻ መሆን አለብኝ ከሚል አስተሳሰብ ጋር እርቀቱ እጅግም ነው። በዛሬው ዘመን የሚፈለገው ሁሉም አካባቢዎች በተጠጋጋ እድገት ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያበረክቱት ዝንጉርጉር ድርሻ ዳብሮና ፈክቶ እንዲወጣ ነው። ኣብዛኛው ነገር ከኔ እየተገኘ የሚል ክርክርና የሌላውን ድርሻ በንቀት ማየት የሚወገደው በዚህ መንገድ ነው። ኣንድ ኣካባቢ የሁሉ ነገር ማእከል ልሁን ቢል ሌላ ዝንፈት መፍጠርና እየተናጩ ለመውድቅ መምረጥ ይሆናል።

የትግራይ ህዝብ «ለደመኛ ጠላት» የማይጋለጠው የሁሉ ነገር ማእከል በመሆን ኣይደለም። የያንዳንዱ ኣካባቢ ልማት በየራሱ አቅም ብቻ ኣይሳካም። የተሳሰርነው በጋራ ታሪክ ብቻ ኣይደለም። ከኣካባቢ ኣካባቢ ተበላልጠውና ተጓድለው የሚገኙ የሃብት ስብጥሮችን ኣስተባብሮ በኢንዱስትሪ፣በግብርናና ባገልግሎት የለማች ሃገር ለመገንባት መያየዛችን ስለሚጠቅመንም ነው። ከዚህ ኣኳያ ያንዱ ኣካባቢ ልማት መሳካትና ኣለመሳካት ከሌላውም ጋር የተሳሰረ ነው። ሁሉም ክልሎች የልማት፣የምርምር፣የባህል፣ የዲሞክራሲና የእኩልነት ግስጋሴ የሚፍለቀለቅባቸው ማእከሎች በሚሆኑበት ኣቅጣጫ ተያይዞ መጓዝ ከተቻለ ጥላቻ፣ ትምክህትና ጥበት ድራሻቸው መጥፋቱ ኣይቀሬ ነው።

# 3 የመፍትሄ ኣቅጣጫዎች

**ህብረብሄራዊ ኣደረጃጀት**

ቀደም ሲል የተጠቃቀሱት የብሄረተኝንት ድጦችና የትምክህት ችግሮች በኢትዮጵያ ውስጥ በተግባር ታይተዋል:: ዛሬም በተለያየ ደረጃ ይንፃባረቃሉ:: ክልልተኞች፣ ወገንተኞችና ትምክህተኞች በሚፈጥሯቸው ቅራኔዎችና ፍርሃቶች ውስጥ መኖር የሚስማማው ህዝብ የለም:: የ1997 ምርጫ ተመክሮም ይህንኑ ያስገነዘበ ነበር:: መንግስትም ካንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ እየሮጠ ሁከት በማብረድና በማስታረቅ ችግሮቹን መጨረስ ኣይችልም:: ከነዚህ ችግሮች ጋር መኖር ግድ ኣይደለም::ብሄረተኛነት የብሄር ወገንን ከኣስተዳደራዊና ከሙስና በደሎች የማዳን ውሰጠ ባህርይ የለውም:: የብሄረተኛ በዳይ ሞልቷል:: ለዲሞክራሲ፣ ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ለሰላምና ለብልፅግና የሚደረገው ትግል የልዩ ልዩ ብሄረተኛ ድርጅቶችን መፈጠርና መቀጠል የግድ ኣስፈላጊ ኣያደርገውም:: የብሄር ብሄረሰቦች ራስን የማስተዳደር፣በቋንቋ የመማርና የመስራት ባህልን የመንከባከብና የማበልፀግ መብቶች ተፈፃሚነትም ከህብረ ብሄራዊ ኣመለካከትና ኣደረጃጀት ጋር የሚጋጭና ብሄረተኛነትን ትክክል የሚያስብል ኣይደለም:: ብሄረተኛ ቡድኖች በግንባር ተያይዘው ሊሰሩ መቻላቸውም ህብረብሄራዊ ኣደረጃጀትን ኣይተካውም ወይም ኣላስፈላጊ ኣያደርገውም:: በህብረብሄራዊ ኣደረጃጃችና በብሄርተኛ ኣደረጃጀት መሃከል መሰረታዊ የኣመለካከት ልዩነት ኣለ:: ልዩነቱን ለመረዳት ባንድ ፕሮግራም ዙሪያ ልዩ ልዩ የብሄር ብሄረሰብ ኣባላት ያደራጀ ድርጅትና ብዙ ብሄረተኛ ድርጅቶች ባንድ ምክር ቤት ውስጥ ቢቀመጡ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች እጥረትና ርዝማኔ መገመት ያግዛል:: የብሄር ኣደረጃጃት ዛፍ ዛፉን የማየት ባህርይ ያጋደለበት ሲሆን ህብረ ብሄራዊ ኣኣደረጃጀት ግን የዛፉን ስብስብ (ደኑን) የማየት ባህርይ ያመዝንበታል:: የብሄር ቡድኖች ቢያያዙ የየኣካባቢ ፕግራሞቻቸውን ሳይጥሉ ነው:: በህብረብሄር ኣደረጃጃት ውስጥ ሲገቡ ግን የሚኖረው ኣካባቢያዊ ጥቅሞችን ያቻቻለ ኣንድ ሃገራዊ የፓርቲ ፕሮግራም ነው:: የብሄር ቡድኖች ኣላማቸውን የተቀበሉ የብሄር ወገኖችን በየበኩላቸው በኣባልነት የሚይዙ ሲሆኑ ህብረ ብሄራዊ ድርጅት ግን የብሄርና የቋንቋ ልዩነት ሳያደርግ ኣላማውን ተቀብለው የሚተገብሩ ዜጎችን የሚያሰባስብ ነው:: በብሄር ብሄረሰቦች የርስበርስ ግንኙነቶች ውስጥ የሚንፀባረቅ ጥርጣሬና ስጋትን ለማደከምና ትምክህትን ለማምከን፣ግለሰባዊ ፀቦችን ከግልነት እንዳያልፉ ለማድረግ የተሻለ አቅም የሚሰጥም ይህው ኣደረጃጀት ነው:: ኣግላይና ተገላይ ኣስጎንባሽና ኣጎንባሽ ማህበረሰብ ሳይኖር ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እጅ ለእጅ ተያይዘው ለመትጋት የሚቀና፣በመተላለቅና በመፈናቀል ፍርሃት መበርገግ የሚደርቅበት፣ በብሄር ድርጅትነቴ ወኪልህ ነኝ እያሉ ለማደናገር የማይመች ጎደና ነው:: ወደ ህብረብሄራዊ ፓርቲ አደረጃጃት ቢዞርም ያንዱ ወይ የሌላ ብሄር አመዛኝነት በሚታይባቸው ክልሎች ውስጥ የፓርቲው ቅርንጫፍ ባንድ ብሄር ኣባላት መዋጡ፣በስልጣን ኣያያዝም ላይ ይህ መሆኑ የማይቀር ነው:: ወገናዊ የመጠቃቀም ሙከራዎችም በቶሎ የሚጠፉ አይሆኑም:: ነገር ግን ህብረብሄራዊ ፓርቲ የሚያሳየው ባህርይ ከብሄረተኛ ፓርቲ በጣም የተለየ ነው:: ዲሞክራሲያዊነት ከስም ጌጡ ይልቅ እስትንፋሱ ያደረገ፣ ህብረብሄራዊነትንም በስብስቡ ያሟላ ድርጅት ለወገናዊነትም ሆነ ለትምክህት ኣይመችም:: ያመለካከት ማእዘኑ ሁሉንም ብሄር

ብሄረሰብ የማየት፣የማሳተፍና የማዳመጥ ባህርይ ስላለው ከሌላው ኣደረጃጀት በተሻለ ተማምኖና ተጋግዞ ኣድላዊነትን ለመዋጋት የሚያስችል ነው:: ንኡሳን ክፍሎች ወይም ውሁዳን ወገኖች በቁጥር ከሚያይሉት ብሄር ብሄረሰቦች ጋር ተጣጥሞ ለመስራት፣ በፓርቲው ውስጥና ከፓርቲው ውጪ መብቶቻቸውን ለማስከበር፣ ኣድላዊነት እንዲጋለጥና እንዲታረም ለማድረግ በበለጠ ይበረታታሉ:: «ስደተኛ»፣ «በሀገሬ መጥቶ» የሚሉ ጥበቶችንና የነዚህ ተቃራኒ የሆኑ ትምክህቶችን እየበጣጠሱ በየትኛውም ስፍራ ዜጎች እየሰሩና ካፒታላቸውን እያንቀሳቀሱ ልማትን ለማንደርደር ከብሄረተኛ ኣደረጃጅት በጣሙን የተሻለ ነው:: ይህ ሰባኪ የማያስፈልገው እውነት ነው:: የጎሰኛ ኣድሎን በጎሰኛ ኣድሎ መመከትና ማሸነፍ እንደመይቻል፣ እነንትና ካዳሉ እኔስ ለምን ኣላደርገው የሚል ጉዞ የጥፋት መሆኑ ከተሞክሮ ታይቷል:: ብሄርተኛ ድርጅቶች በክልል ደረጃ ስልጣን ይዘው በጎሰኝነት የቱን ያህል እንደነጎዱ፣በግንባር ስም ተሸፍኖ የፌዴራል መንግስት ዋና ገዢ ቡድን ቢኮንም ከጎሰኛ የስልጣን ቁጥጥርና ዘረፋ እንዳልተመለጠ እስኪያቅር ታይቷል:: ስልጣን ላይ ገና ያልወጡ ብሄርተኛ ድርጅቶች ስለብሄርተኝነት ድጥ ለመማርና ከወዲሁ ለመስተካከል የ16 አመት ልምድ ኣያንሳቸውም:: በዚህ ረገድ በሰኔ 1999 የተወሰኑ ቡድኖች የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲን መፍጠራቸው ጥሩ ጅምር ነው:: የተቀሩትም፣ ኢህኣዴግና ኣጋሮቹም ወደ ህብረብሄራዊ ኣደራጃጀት ሙሉ ለሙሉ ቢገቡ ለሃገሪቱ ትልቅ እርምጃ ይሆናል::

ከዚህ ቀደም በሂደት መዋሀድ ኣላማው መሆኑን ኢህኣዴግ ገልፆ ነበር:: ሆኖም መስከረም 21፣1999 ኣ.ም. ጠቅላይ ሚንስትሩ በሰጡት ቃለመጠይቅ የመወሃዱ ግብ እንደተጠበቀ ቢሆንም በኣሁኑ ጊዜ ገና እንደሆነና የሚያስገደድ ሁኔታ እንደሌለ ተናግረዋል:: ላይ ላዩን ከምንመለከተው እንደምንረዳው የኢህኣዴግ ኣባል ድርጅቶች ያላቸው ኣንድ ከመሆን ብዙም ያልራቀ የኣቋምና የኣሰራር መግባባት ወደ ህብረብሄራዊ ኣደረጃጃት ለመሄድ የሚያስችላቸው ይመስላል:: ከይመስላል በላይ ማለት ኣይቻልም:: ከትምክህትና ከጠባብነት እንዲሁም ከመልካም ኣስተዳደርና ልማት ጋር የተያያዙ ችግሮቻችን ግን መዋሀድን የዘገየ እንጂ ገና የሚያደርጉ ኣይደሉም:: ምናልባት ወደ ውህደት ሲኬድ ከውጭ ያሉ ተቃዋሚ ብሄረተኞች የብሄራዊ ድርጅቶችን ህልውና ወያኔ ጨፍልቆ ክልላዊ ስልጣኖችን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጠረ የሚል ቅስቀሳ ይጀምራሉ ተብሎ ተፈርቶ ከሆነ የዚያ ኣይነት ቅስቀሳ መከሰቱ ይገመታል:: ቢከሰትም ግን ውህደቱ እውነተኛ ከሆነና ከቅርብ ኣመታት ወዲህ እየተከናወነ ያለው የልማት ተግባር ፍጥነትና ጥልቀት እያገኘ ከሄደ ቅስቀሳው ችግር ኣያመጣም::

መለስ ዜናዊ «የመቻቻልና የፍቅር ተምሳሌት» ያሏት ሃረር ለዚህ ምሳሌነት የበቃችው የተሰባጠሩ ነዋሪዎቿ የተሳሰበ ትስስር ለማዳበር በመቻላቸው ነው:: አሁንም ትስስሩ እንዳይፈርስ ዋናውን ጥረት የሚያደርጉት ነዋሪዎቿ ናቸው:: ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ህዝቦችም አብሮነታቸው እንዳይበላሽ የተቻላቸውን እየተንገዳገዱ እዚህ ደርሰዋል:: ሃላፊነት የጎደለው ፖለቲካ እንደመብዛቱ ቢሆንማ ኖሮ ዛሬ ባሉበት የመቻቻል ደረጃም ላይ ባልተገኙም ነበር:: ገዢው ፓርቲም ሆነ ሌሎቹ ሊገባቸው ከቻለ፣ ድሬዳዋ በጎርፍ በተጎዳች ጊዜ ያለቀስቃሽ ተካሂዶ የነበረው የድጋፍ ርብርብ ከድጋፍም ባሻገር «በከፋፋይ ፖለቲካ መታመስ መረረን! በነፃነትና በፍቅር መኖር ራበን!» የሚል የኣቋም መግለጫ ድሬዳዋን ምልክት(symbol) በማድረግ የተላለፈበትም ነበር:: አሁንም አዲሱ ሺኛ ኣመት «ሃገራችን ሃረርን የምትሆንበት መባቻ ነው» መባሉ ከልብ ከሆነ ከፖለቲካ ጥለኝነት፣ ከጠባብ አስተሳሰብና ፖለቲካዊ ስብስብ መውጣት የግድ ነው::

**የታደሰ ኢትዮጵያዊነት**

የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ተሃድሶ ማግኘቱና የሃገሪቱን ህዝቦች እንደስሚንቶ ሊያያይዝ መቻሉ ለመፃኤ እድላችን ወሳኝ ነው። ይህንን ያሳካሉ የሚባሉ ሶስት ቁምነገሮችን እናስቀምጥ።

1) እስከዛሬ ባለን የሃገር ፍቅር ስሜት ውስጥ የሚንፀባረቀው ብሄረተኛ ያየዘውን ነገር የመራቅና ከትምክህት ጋር የመሳሳብ ግንኙነት መስተካከል ይኖርበታል። በብሄረተኝነት ውስጥ የሚወናገረው የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተጣርቶ የኢትዮጵያዊነት ኣንድ ዋልታ መሆኑ ግድ ነው። በንቀትና በሽሙጥ የሚገለፅ እኔ እበልጥ ባይ ኣላዋቂነት ተሰብሮ የሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦች ማንነት፣ባህልና ቋንቋ የማክበር ስልጡንነት ጥብቅ መሰረት ማግኘት ይኖርበታል። ከጥንታዊ ቅርሶቻችን ጋር የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋዎች፣ ባህሎችና የኪነጥበብ ሃብቶች የኢትዮጵያ መመኪያና መታወቂያ ሆነው እንዲያድጉ ማድረግ፣የመላ ብሄር ብሄረሰቦች ታሪክ ከየተጓዘበት ዘመን የእድገት ደረጃና የንቃት ህሊና እውነታ ሳይነጠል ከተረቶች እየጠራ ተሰናድቶ የኢትዮጵያዊነት ግንዛቤ እንዲሆን ማድረግ፣ብሎም የዛሬን ችግሮች ለመወጣት ሃይልና ብርታት በሚሆን መልኩ መጠቀም ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ የኢትዮጵያን ታሪክ ባለኣንድ መሰረት ኣድርጎ ሲያቀርብ የኖረውን ኣመለካከት መሄስ ተገቢ ነው።ጥንታዊ ታዋቂነት ያለው ስልጣኔ የታየበትና ረዥም ጊዜን ያካለለ የታሪክ መረጃ የተገኘበት ሰሜናዊው ክፍል በመሆኑ፣በመላው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሰሜነዊው ገዢዎች መስፋፋት የበላይነት ሚና የተጫወተና ታሪክ ፀሃፊዎቹም ከሞላ ጎደል ይህው ተዛነፍ የሚጫናቸው ስለነበሩ የኢትዮጵያን ታሪክ ባለኣንድ መስመር ኣድርጎ መመልከት ሰፍኖ ቆይቷል። ዛሬም ይህ ኣመለካከት በተስተካከለ ኣዲስ እይታ ኣልታረመም። ብሄረ ትግራይን የኢትዮጵያ ህዝብ ስልጣኔ መሰረት ብለው ገብረኪዳን ደስታ በልበሙልነት ደጋግመው መናገር የቻሉትም ኣንድም ከዚህ መጓደል ይሆናል።

> « የአክሱማውያን ሐውልቶች፣ የማሕሌታይ ያሬድ ዜማዎች፣ የአበሻ ልብሶች፣ የወርቅና የብር ጌጣጌጦች ወዘተ ሁሉ እኮ የትግራይ ህዝብ ቅርሶችና የስልጣኔ መገላጫዎች ናቸው። የኢትዮጵያ ፊደል፣ የኢትዮጵያ ስርዓት መንግስት፣ ስርዓት ሃይማኖት፣ ጤፍ፣ እንጀራ፣ ጠላ፣ ጠጅ ወዘተ የእነዚህ ሁሉ ምንጭና ባለታሪክ እኮ የትግራይ ሕዝብ ነው።» (ከላይ የተጠቀሰው፣ 111)

በእጅ ያሉ የታሪክ ስራዎችን ባግባቡ ፈልፍሎና ኣገናዝቦ ለመረዳት ቢሞከር የሚደረስበት ግንዛቤ ከዚህ የራቀ ነው። የኣክሱም ስልጣኔ ከበስትጀርባ የነባር ህዝቦችና ከእስያ የፈለሱ ህዝቦች ተራክቦ ያለበት ነበር። ዛሬ የምናውቀው የብሄር ባህርይና ኣስተሳሰብ የቅርብ እንጂ ወደ 1600 ኣመታት የሂሊት ተመልሰን 4ኛው ክ/ዘመን ላይ ለመቆም ብናስብ ልዩነቱ ከግምት ኣድመሳችን ውጪ ይሆናል። በዛሬ ትግራይ ሰሜናዊ ክፍል ውስጥ የምትገኘው ኣክሱም የኣክሱምች ስልጣኔ ማእከል ነበረች። ትግሪኛ፣ ትግረ፣ ግእዝ ሌሎችም ቋንቋዎች ባካባቢው ይነገሩ ነበር። ነገር ግን የኣክሱሞች ስልጣኔ በትግሬነትና በትግሪኛ ማእቀፍ ውስጥ የነበር ስልጣኔ አልነበረም። ተፅፈው የተገኙትም የፅሁፍ ቅርሶች ከዚህ ማጠቃለያ ጋር የሚስማሙ ናቸው። ልዩ ልዩ ቋንቋ ከመነገሩ በስተቀር በጊዜው የነበሩት የኣካባቢው ማህበረሰቦች በተዋረ ባህርያቸው ተመሳሳይ የነበሩ ይመስላሉ። የአክሱሞች ግዛት ባንድ አክሱም ያልተወሰነ በየአቅጣጫው የመስፋፋት ባህርይ የነበረው ነበር። ከሂደት ሂደት ሌሎች ህዝቦች በኣክሱም ግዛትና የስልጣኔ ይዞታ ውስጥ ገብተዋል። ኣገው-ላስታዎች የኣክሱሞች ስልጣኔ ኣስወጋጆች ሳይሆኑ ቀጣዮች መሆን የቻሉት ኣስቀድሞ በኣክሱም ስልጣኔና የባህል ይዞታ ውስጥ ተካትተው ስለነበር ነው። ከኣገዎች ደግሞ ሰለሞናዊያኑ እንደገና ይቀጥላሉ።

የኢትዮጵያ አገነባብ ታሪክ ቢያንስ ባለሁለት ኣቅጣጫ ነው። የንግድ እንቅስቃሴ መስመሮች ኣካሄድ፣የልዩ ልዩ አካባቢ ገዢዎች የመስፋፋትና የመገዛዛት ትግል፣ የህዝቦች እንቅስቃሴና የኣሰፋፈር ለውጥ የሚያስገነዝበንም ይህንኑ ነው። ከኣክሱም

ተነስተን ባንድ አቅጣጫ ቁልቁል ከማየት ስንወጣና ከገዢዎች ዘመቻ ውጪ ያሉትን ሌሎች የታሪክ ኣክርማዎች መለየት ስንችል ነው የማይገናኙ የሚመስሉ የታሪክ ሃይሎች ወደፊትና ወደ ሂላ በሚል ኣካሄድ እየተያያዙና ካንዱ ጉድኝት ወደሌላ ጉድኝት እያለፉ ለሰፊ ሃገር ግንባታ የተጫወቱትን ሚና የምናጤነው:: ገና ብዙ ጥናት የሚፈልጉ ጉዳዮች ቢኖሩም እስካሁን የታወቀውን ያህል የሚወሱት የበስተደቡብ ህዝቦች ታሪኮች በኢትዮጵያ ግንባታ ታሪክ ውስጥ ባላቸው የድርሻ ጉልህነት አኳያ ከሰሜኑ ታሪክ ጋር በኣግባቡ መሰናኘት ያልቻሉት በዚህ ኣመለካከትና ዘዴ መጓደል ምክንያት ነው:: ታሪኮች የዝምድና ግንኙነታቸው ሳይነጥር የፍንግጥግጥ መቀመጣቸውን ኣየለ በክሪ ልብ ብሎታል:: በራሱም መንገድ ሰልፍ ሊያስገባ ሞክሯል:: (http://tadias.Com/p123, **01/05/2007)** የችግሩ መጠቆም ተገቢ ነው:: መፍቻው ግን ብዙ ሥራን ይጠይቃል:: አንዱ ምኒልክዬ ሲል ሌላው ዮሐንስዬ፣ አባጅፋርዬ፣ ጦናዬ የሚባልበትን የተጋነነ የታሪክ ጀግና ግንባታን ተሻግሮ የመሃበረሰቦች ታሪካዊ የውስብስቦሽ ደረጃ ስላለፈው ያለውን ጠቋሚነት ማስተዋል፣ የኣፈታሪክ የፅሁፍና የቁሳዊ ቅርስ መረጃዎችን በወጉ ማጥናት፣ አብሮም የታሪክ ዋና አገዳዎችንና ንኡሳኑን ማወቅ፣ ከብዙ ኣቅጣጫ ተነስተው እየተፋተሉ የሚሄዱትንና እስከተለያየ ርቀት በትይዩ የሚጓዙትን የታሪክ ፈትሎች መለየትን ይጠይቃል:: በዚህ በኩል ኣንድ ትልቅ ተግባር ተደቅኗል:: በተረፈ ከኢትዮጵያ የቅድመሰው ታሪክ መገኛነት ተነስቶ የኢትዮጵያን ታሪክ 4.4 ሚሊዮን ኣመታት ወደ ሂላ መዘርጋት (ኣየለ በክሪ እንደሞከረው) ኣጠቃላይ የሰው ልጅ ቅድመ ኣመጣጥን የሚመለከተውን ታሪክ ከኢትዮጵያ ጋር ማሳከር ይሆናል:: የኢትዮጵያን ህዝቦች ታሪክ መቋረጥ ባልታየበት የዝግመት ታሪክ ከነሉሲ ቅድመ-ሰው በሁለት እግር ተራማጆች (hominids) ጋር የሚያያዝ መረጃ የለም:: የኢትዮጵያ አካባቢ የቅድመ-ሰው ምንጭነት ሳይሻር መቆየት ቢችልና ከኢትዮጵያ ኣካባቢ ወደ ሌላው ስፍራዎች ቅድመ-ሰው ተሰራጭቷል ተብሎ ቢታሰብ በዚያ ረዥም ዘመን ውስጥ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰ ስርጭት አለመካሄዱን መድፈን አይቻልም:: የ4 ሚሊዮን ኣመታት ታሪክ ዋጋ ለኩራት ያህል ብቻ የሚሆን ነው::

2) «ሃገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው::» ይህ ለረዥም ጊዜ በኢትዮጵያ ህዝቦች ውስጥ የነበረ፣ መሳከር የሌለባቸውን ሁለት መብቶች ቁልጭ ኣድርጎ የሚያሳይ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ሲጠብቅና ሲፈጠሩ መፍቻ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ቁልፍ የኣብሮነት መመሪያ ነው:: ዛሬም ይህ መመሪያ በዜጎች ግንኙነትና ንቃተህሊና ውስጥ ያለው ዋልታነት መጠንከር ይኖርበታል:: ክርስትናና እስልምና ከውጪ ወደ ኢትዮጵያ በተቀዳዳሚ ጊዜ ውስጥ የገቡ መሆናቸው ይታወቃል:: የሃይማኖቶቹ ኣገባብ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥንተ-ኣመጣጥ ጋር የተያያዘ ኣይደለም:: ይህ እውነት እንደተጠበቀ ሆኖ «ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ የመጣ» የተሰኘው ኣባባል ለሁለቱም ሃይማኖቶች ማገልገግ ይችላል:: ነገር ግን ኢትዮጵያን ከኣንድ ሃይማኖት ጋር የማዛመድም ሆነ በኣካባቢ ደርጃ ያለን የቋንቋና የሃይማኖት ስርጭታዊ ክምችትን መሰረት በማድረግ ኣናሳውን እንደባይተዋር የመቁጠር ኣመለካከት እንዲሁም በቅርብ የገቡ እምነቶችን ተከባሪነት ከኦርቶዶክስ ክርስትናና ከእስልምና ኣሳንሶ ማሰብ የተሳሳተና የሚያሳስት ነው:: ኢትዮጵያ የክርስቲያኖች፣የሙስሊሞች፣የሌሎች እምነት ተከታዮችም ሃገር ነች:: ኢትዮጵያ የጋራችን እምነት የግል::

ከደርግ በፊት ክርስትና የመንግስት ሃይማኖት ነበርና እስልምና በ«ክርስቲያኗ» ኢትዮጵያ ውስጥ ውሱን ስፍራ ያለው እምነት ተደርጎ ይታሰብ ነበር:: ደርግ እስከውድቀቱ መቃረቢያ ጊዜ ድረስ ሃይማኖትንና መንግስትን ከመለየት ዘሎ ሃይማኖቶችን የማፈንና የማዳከም ፖሊሲ ነበረው:: ኢህኣዴግ ደግሞ ከደርግ በፊትና በደርግ ጊዜ የነበረውን ችግር ሊያስወግድ ሞክሯል:: ነገር ግን የፖለቲካ ድርጅቶች ሃይማኖቶችን በድጋፍ ማሰባሰቢያነት ወይም በማስጠሊያነት ሊገለጉባቸው መሞከራቸው ገና አልቀረም:: በ1997 የምርጫ ጊዜ የግል መብቶችን ያጠበቀውን ወገን በመቃረን ኢህኣዴግ ስለቡድን መብት አስፈላጊነት ሲያስረዳ ከብሄር መብት ሌላ ሙስሊሙ ወገን ያገኘውን የእምነት እኩልነት ጠብቆ የማቆየትን ጉዳይ መጠቃቀሱና ተቃዋሚው ወገንም ኢህኣደግ በሙስሊሙ ላይ

ኣደረሰ የሚለውን በደል መቁጠሩ ይታወሳል። ይህን መሰል ሃይማኖቶችን ምርኩዝ ያደረጉ ግልጽና ስውር የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳዎች በተለይ በስልጣን ላይ የተቀመጠውን ፓርቲ ሳንዱ ወይ ለሌላው ሃይማኖት ልዩ ተቆርቋሪነት ያለው የሚያስመስል ግንዛቤ ሊያስከትሉ ይችላሉ። መንግስት ለዚህም ሆነ ለዚያ ሃይማኖት ያዳላል የሚል ኣስተሳሰብ እንዳይፈጠርበት ተጠንቅቆ መስራቱ ለተሰሚነቱም ሆነ ለሃይማኖቶቹ ጤናማ ግንኙነት ብሎም ለሃገሪቱ ሰላም መሰረታዊ ነው።

በኣሁኑ ጊዜ ከወያኔና ከሆዳም ግብረአበሮቹ ቀጥሎ ወሃቢስቶች ምርጥ ዜጎች ሆነዋል የሚልና በኢትዮጵያ ላለው ዜግነት 7 ደረጃዎች ያወጣ ግልብ ግን አደገኛ ቅስቀሳ መኖሩን መረዳት ይገባል። መንግስት የትኛውንም ሃይማኖት በገለልተኛና በእኩል ኣይን የሚያይ ሃገራዊ ተቋም ተደርጎ በህዝብ <u>መታመኑ</u> ወሳኝ ነው። ከመንግስታዊ ጠንቃቃነት በተጨማሪ የዲሞክራሲና የሰብኣዊ መብቶችን የማስረፅና የማስከበር ጥረት መጠናከሩ ዋስትና ነው።

ይህንኑ የሚደግፉ ሌሎች ጥቂት ነጥቦችን እናስቀምጥ።

ሃይማኖትን መስበክ መብት ቢሆንም የሌላው መብት የሚነካበትን ወሰን አበክሮ ማወቅና ማክበር የማይቀር ነው። ኣንድ ሰው በኣንድ ሃይማኖት ውስጥ ረግቶ የሚቆየው ከሎጂክ ይልቅ በእምነት ፅናት ነው። ዛሬ ባለንበት የመቻቻልና የመከራከር ባህል ዝቅተኛነት ደረጃ በተለይ በተራ ኣማኞች ደረጃ የሃይማኖቶች ክርክር መግጠም ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊበልጥ ይችላልና መቆጠቡ ይመረጣል።

በእምነት ተቋምም ውስጥ ሆነ በፅሁፍና በሌላ የመገናኛ ዘዴ የሌላውን እምት እየተቹ እምነትን ማስተማር አደገኛ ትንኮሳ ያለበት ነው። ኣንድ ሃይማኖት ማስተማር ያለበት ለእምነቱ ምሶሶ የሆኑ የራሱን መፅሃፍት ተመስርቶ እንጂ ከሌላው የእምነት መፅሃፍ እየመዘዘ መሆን ኣይኖርበትም። ከተወሰኑ ኣመታት በፊት በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈሩ ትንቢቶችን እየጠቀሱ የተነገሩት ለእየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን ለነብዩ መሃመድ ነው የሚሉና ሌሎች ተጨማሪ ፅሁፎች የኣቶ ኣለማየሁ ሞገስን የከረረ ምላሽ እንዳስከተሉ ምላሹም በፋንታው ቅዋሜ ፈጥሮ እንደነበር ይታወሳል። የትኛውም ወገን የማንኛውንም እምነት የማረምና የመተቸት መብት የለውም። እምነቴ ስህተት ነው የሚል ሃይማኖተኛ በኣለም የለም። <u>የእኔ ሃይማኖት ልክ ነው ባይነት ግን የሌላውን ልክ ነኝ ባይነት ከማክበር ጋር መጣመር ይኖርበታል</u>። ለዚህ ነው ክርስቲያን ነኝ ብሎ የሚያምንን ወገን ሌላው ተነስቶ «ያፍ ክርስቲያን» ነህ ወይም «ከእርዳታ የተገኘ ሃይማኖት ነው ያለህ» ብሎ ቢነቅፈው ትልቅ ነውር የሚሆነው። <u>አሁንም «ሃገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው</u>።» የሌላውን ሃይማኖት ሳያከብሩ የራስን ማስከበር ያዳግታል።

ከዚህ ባሻገር፣ሃይማኖት የተለያየ ፍላጎት መሸፈኛና ማራመጃ ሆኖ የሚያገለገልበት ዘመን ላይ ነው የምንገኘው። የዘንድሮ ሌባ ሳይቀር ሃይማኖት አጥባቂ መስሎ በመቅረብ ሙሉ ለሙሉ እስኪታመን ድረስ ጠብቆ ወፈር ያለ ገንዘብ ማጭበርበር ኣምጥቷል። በኣለም ውስጥ የተደራጀ ቡድንን ጥቅም ለማሟላትና ፖለቲካዊ ጥላቻና በቀልን ለመወጣት ሃይማኖት ሲውል፣ ብሎም የኣእምሮ ቀውሰኞች መጫወቻ ሲሆን ማየት አዲስ አይደለም። በተለያዩ ጊዜት እንደክርስቶስ ሞተን እንነሳለን በማለት ራሳቸውንና ተከታዮቻቸውን በመርዝ የጨረሱ በሽተኞች ተከስተዋል። በኡጋንዳ ውስጥ በህዝብ ላይ ግፍ ሲውል የቆየው LRA ራሱን የጌታ አምላክ ሰራዊት ብሎ የሰየመና ለኦሪት ስርኣት ቆሜየለሁ ባይ ሆኖ ነው። በእስልምናም በኩል ታሪክን ወደ ኋለኛ ዘመን ሊመልሱ የሚሞክሩ አሉ። በጂማ ዞን ውስጥ የተፈጸመውም ጥፋት ለእስልምና እምነት ከመቆም ጋር ፈፅሞ የማይዛመድ የታመመ ተግባር ነው። ለዚህ ኣይነት ጥፋት መዘዝ የሚሆኑ አስተሳሰቦች እርዳታንና አለማቀፋዊ ወንድማማችነትን ተከልለው ሊሰርጉ ይችላሉ። ሰርገውና ተባዝተው ህብረተሰብ እንዳይበጠብጡ የሃይማኖት አባቶችና የሃይማኖት ተቋማት፣ መንግስትና መላ ህብረተሰቡ ነቅቶ የመጠበቁ ሃላፊነት ይመለከታቸዋል።

**3)** በልማት ራእይ የታደሰ ኢትዮጵያዊነትን እንደሃይል ይዞ ወደ ብልፅግና ለመሸጋገር ከተፈለገ ሃገር የምትጎዳባቸውንና የምትጠቀምባቸውን አቅጣጫዎችና ሁኔታዎች ዜጎች ያወቁበትን አጠቃላይ ንቃተህሊና መገንባት የማይቀር ጉዳይ ነው:: በስራ ፈጣሪነትና ፍቅር የተቀረፀ፣ በየዋህነት ወይም በማይረባ ጥቅም የሃገሩን ውድ ቅርስ የማያስመነትፍ፣ ለሃገሩ ሃብት እንክበካቤና ልማት የሚቆርቆር፣ ከውጪ እቃ ኣፍቃሪነትና ከሃገር ውስጥ እቃ ናቂነት ነፃ የወጣ፣ በመጤ ሸቀጦች የተጨናነቀ አኗኗርን ጎጂነት የተረዳ፣ የውጪ ምንዛሪና እውቀት ወደ ሀገር እንዲገባና እንዲስፋፉ መጣር የልማት ተጋድሎ መሆኑ የገባው ዜጋ ያስፈልገናል:: በላኪነትና በኣስመጪነት መስክ በግላዊም ይሁን በመንግስታዊ ኣካል የሚደረጉ የግብይይት ሙስናዎች፣ የኮንትሮባንድ ንግድ፣ የብር ምንዛሪ ግሽበት፣ የውጪ ሸቀጦችና የነዳጅ ዋጋ ንረት የሃገሪቱን ኢኮኖሚ የሚጎዱና ምንዛሪ የሚያስመልጡ መሆናቸውን ያወቀ፣ ከሂላ ቀር ያስተሳሰብና ያሰራር ማነቆዎች የተላቀቀ፣ በዘመናዊ እውቀትና ክህሎት የሚተጋ ኢትዮጵያዊ ልማታችን ይፈልጋል:: ትምህርትና ስልጠናችን፣ ያኗኗርና የኣሰራር ባህላችን ሁሉ በተሃድሶ ኣቢዮት ውስጥ መግባቱ ግድ ነው::

ሃላፊነት የተዋሃደው የሃገር ፍቅር መገንባት እስከተቻለ ድረስ ብዙ ባለሙያ ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ መፍሰሱ አያስፈራም:: ይልቅስ የኢትዮጵያ ሙያተኛ በውጪ በመፈለጉ ተደስተን በተሻለ የችሎታና የስነምግባር ብቃት ገበያውን ለመሙላትና ለማስፋት፣ በሃገሪቱ ውስጥ ያለውን ፍላጎትም ለመሸፈን የሚችል የሰው ሃይል በየጊዜው ማፍራት የምንረባረብበት ኣንድ የልማት እቅዳችን ይሆናል:: የውስጥ ፍላጎት ሲባልም መታሰብ ያለበት ዜጋችን ብቻ ኣይደለም:: ዛሬ ጥራትና ደረጃቸው ከለሙት ሃገሮች ጋር የተመጣጠኑ ኣገልግሎችን (የህክምና የመዝናኛ ወዘተርፈ) በቀለለ ዋጋ ማቅረብ ኣንዱ የውጪ ምንዛሪ መሳቢያ ነውና በዚህ በኩል መዘጋጀት ይጠበቅብናል::

ያለንን ሃብት ሳናባክን ለኢኮኖሚ ግንባታችን መሳሪያ ማድረግን ካወቅንበት ስራዎች አያልቁብንም:: በትግራይና በኣማራ ኣካባቢ ያለው ከትናንሽ  ጌጦችና ከእምነት ምልክቶች ያላለፈ ድንጋይ ነክ እደጥበብ በቅርቧ ኬንያ ውስጥ የሚታየው ኣይነት ዘመናዊ ለውጥ ቢካሄድበት በስራ እድገትና በቱሪዝም ገቢ ጉልህ ለውጥ የሚያመጣ ነው:: በመካከለኛና በረዥም ርቀት ሩጫ ያገኘነውም ኣለማቀፋዊ ዝና ወደልማት መሳሪያነት ሊቀየር ይችላል:: የሩጫ ሜዳዎች፣ የጅምናዚየም፣ የሆቴሎችና ሳቢ የመዝናኛ እንክብካቤዎችን በኣግባቡ ኣደራጅቶ ኣለም የኢትዮጵያ ሩዋጮችን የድል ሚስጥር እንዲቋደስ በመጋበዝ መነገድ እንችላለን:: ታሪካዊና አርኪዮሎጂያዊ ሃብቶቻችንና መገኛ ስፍራዎቻቸው ከቱሪዝም ገበያ አኳያ ገና አልተሰራባቸውም:: የከረዩና የቦረና አሮሞዎች ያልተነካ ውብ ኣዘፋፈን፣ በጌድኦና በሌሎች በርካታ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ሙዚቃ ውስጥ የምናገኘው ድንቅ ህብረ ዝማሬ፣ ገና ዘመናዊ መነካካት ሳያርፍበት ሀበሻና ፈረንጅን ያስደነቀው የደራሼዎች ኣይነቱ የእግር የምት ስልት ሁሉ የሚያጋፍርበት የሙዚቃ ሃብታችን የሚያዳብረው ካገኘ ኣለም ሊሰማው የሚችል ኣልማዝ ነው:: ፈረንጆቹ ሰርቀውና ከራሳቸው ጋር ኣጣጥመው የኛኑ በኛው ላይ ከመነገዳቸው በፊት መፍጠንም ይጠበቅብናል:: የኛ «ዘመናዊ» ሙዚቃ ግን የሮክ፣ የህንድ፣ የላቲን ወዘተርፈ የተባለ ስልት በመቅዳት ልቃሞነት ውስጥ እየዋተተና ኣፍ እስከማኮላተፍ በደረሰ ፈረንጅ የመሆን ምኞታዊነት ተጠምዶ ይገኛል:: ኣንድ ፕሮፌሰር ኣሸናፊ ከበደን ለታሪክ ያህል ይዞ እንደቀረ ሁሉ ብዙ ሙላቱ ኣስታጥቄዎችና ተስፋዬ ለማዎችን መውለድ ቸግሮታል:: ጮርቃው የኢትዮጵያ የፊልም ጥበብ የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦችን ሰፊ ባህልና ሌሎች የቱሪስት መስህቦቻችንን ቢያንስ በድባብነት መጠቀም ቢያውቅ፣ ርኩስና ቅዱስ መንፈሶች ጣልቃ እየገቡ ታሪክን የሚሾፍሩበትን ውዳቂ ስልት ከመቃረምና ከምኞት ማሚያነት ዘለል ብሎ ከሃገራችን ህይወት ጋር እትብቱን ቢያገናኝ፣ መንግስትም ፊልም በትውልድ እነፃ በኩል የሚኖረውን ሃያል ጥቅምና በአፍሪካ ውስጥ ሊያገኝ የሚችለውን ያልተነካ የገበያ እድል ቢያስተውልና ለእድገቱ ቢጨነቅ ልማታችን የሚደገፍበት ኣንዱ ምንጭ ሊሆን በቻለ ነበር::

ለኣገልግሎታዊ ገቢ ዝቅኛ ግምት የሚሰጡ ቢኖሩ ይህ ዘርፍ(ፊልምን ጨምሮ) በህንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ብልጫ ድርሻ ቀርበው ቢያጠኑ ትምህርት ያገኛሉ።

**ልብ እንግዛ**

የኢትዮጵያ የውስጥና የውጪ ሰላም እጅግ በጣም የተጠላለፉ ናቸው። በኢህኣዴግ የምትመራው ኢትዮጵያ ሁለት ጊዜም ወደሶማሊያ የገባችበት ጣጣ ከሸኣቢያ ሴራ ጋር የተያያዘ ነው። ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር የተያያዘ ጣጣዋን በድል ተወጣሁ ማለት የምትችለውም በሶማሊያ ህዝብ ላይ አበልጅ መንግስት የመጫን ፍላጎት እንዳሌላት ለማስመስከር ከበቃችና ሶማሌዎች የኣገራቸውን መፀኤ እድል ራሳቸው እንዲወስኑ በፅናት ከታገለች ነው። ሶማሊያውያን ኢትዮጵያውያንን ማማረሪያ የማያደርጉት በዚህ አቅጣጫ ከተሄደ ብቻ ነው።

የሶማሊያ ጉዳይ በየትኛውም አቅጣጫ ቢጓዝ የሸኣቢያ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ትግል የጥንካሬና የስፋት ልዩነት ከማሳየት በስተቀር ኣብሮን ይቆያል። በኢህኣዴግና ኣጋሮቹ ገዢነትና ነፍጥ ባነሱትና በውጪ ባሉት ተቃዋሚዎች መሃል ያለው ግንኙነት የጠላትነት መሆኑ ለውጪ ጠላት ጥቃት ያጋለጠ ነው። ሸኣቢያ ጥቃቱን የሚፈጽመው በዋናነት ከጎረቤት ጋር በማጋጨት ስልት ሳይሆን የተቃውሞ ትግል ኣጋዥ በመምስል ነው። በውስጥ ኣርበኛ በኩል ወይም ስውር ግብረሃይል በማስረግ ድንገት ቱግ ብለው ህዝብ ከህዝብ ሊያባሉ የሚችሉ ግጭቶችን ሊቆሰቁስና ሊያቀጣጥል የሚችልበት ምቹ የፖለቲካ ሁኔታ እንዳለ ነው።

ይህ ሁሉንም ወገን ሊያሳስብ ይገባል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃይሎች ተፋራሽ የሆነ ግንኙነት ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት በዋዛ የሚታይ ኣይደለም። የፍልስጥኤሞቹ ፋታህና ሃማዝ በተፋራሽ መስመራቸው ምክንያት እርስበርስ ለመዋጋትና የእስራኤል መሳቂያ ለመሆን መብቃታቸው ለኛም ትምህርት የሚሰጥ ነው።

ኦ.ነ.ግ.ንና ከእሱ ጋር ጥምረት የፈጠሩትን ሃይሎች በብሄር ብሄረሰቦችና በኢትዮጵያ ላይ የተነሱ ኣድርጎ ማሰብ ችግሩን ተረድቶ መፍትሄ ለመፈለግ ኣያስችልም። እነዚህን ተቃዋሚዎች ከኤርትራው ሸኣቢያ ጋር ደርቦ ከማየት ወጣ ካልን የነሱ ነገር የውስጥ ፖለቲካ ችግራችን ሆኖ እናገኘዋለን። የጥምረቱ ኣባላት ባንድ ወቅት ሰላማዊ ትግል ውስጥ የነበሩ  ወይም ኣዲስ የተፈጠሩ ናቸው። ከሰላማዊው መንገድ ይልቅ የትጥቅ ትግል መንገድን ለምን እንደመረጡና በዚህ መንገድ ውስጥ የተሰማሩት ሃይሎች እየቀነሱ በመሄድ ፋንታ ለምን እየበረከቱ እንደመጡ መስተዋል ይኖርበታል። የጠመንጃ መንገደኞቹ ውስጣዊ ደጋፊ ያላቸው መሆኑ ያደባባይ ሚስጥር ነው። ለምን ድጋፍ ሊኖራቸው እንደቻለም የሸኣቢያን ስውር ጥቃት ከመቁረጥ ኣንፃር ብቻ ሳይሆን ለውስጥ ችግራችን መፍትሔ ከመስጠት ኣንፃር መመርመር ኣለበት። በ*1998* የተፈጸሙት ፍንዳታዎች በሸኣቢያ የተቀናበሩ እንደነበሩ ፖሊስ በየካቲት *1999* ይፋ ከተናገረ በሂላ እንኳ «ሃሰት ነው ኢህኣዴግ ያቀናበረው ነው» እየተባለ ይወራ ነበር። ያለበቂ ማስረጃ ወንጅሎና ኣስሮ፣ ፍርድ ቤት እያመላለሱ ማቆየትና የፍርድ መጓተት እስካልተወገደና ከተቃዋሚዎች ጋር ያለው መጠላላት እስካልተቀየረ ድረስ ሸኣቢያ እያምታታ መቆየት ይችላል። ዶክተር ኣብዱል መጂድ ሁሴንን ለመግደል የሞከሩና በሆቴሎች ላይ ያፈነዱ ጥፋተኞች ፍርድ  ኣስር ኣመት መፍጅቱና ከሶማሊያው የእሰላማዊ ፍርድቤቶች ህብረት ጋር ጦርነት ከተካሄደበት ወቅት ጋር መገኛኘቱ ፍርዱን ፖለቲካዊ ውሳኔ እንዲባል ያደረገ ነበር።

 የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱትን ተቃዋሚዎች በጦርነት ድምጥማጣቸውን ኣጥፍቼ የውስጥ ሰላም ኣሰፍናለሁ ማለት ከንቱ ልፋት ይሆናል። ትግል የሚሞተው ፖለቲካዊ እርባና ሲያጣ እንጂ በወታደራዊ ቅጣት ኣይደለምና የነፍጥ ትግልን ለመርታት ማድረግ

የሚያስፈልገው ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ የሃገር ውስጥ መድረክን በማጎልበት ማሳበቢያ መንፈግ ብቻ ነው።

ሽኣቢያ በኢትዮጵያ ላይ የሚያካሂድው የ«ጣልቃ ገብነት» ስያሜ የሚያንሰው የጥቃት ዘመቻ መቆም ያለበት መሆኑ የሚያነጋግር ኣይደለም። ነገር ግን ኣሁን በምንገኝበት ወቅት ጦርነትን እነደተሻለ መፍትሄ እንዳንመርጥ ኣንደኛ፣ የፈጣን ኢኮኖሚና የመልካም አስተዳደር ግንባታ ፍላቶታችን ይቃወመናል። ሁለተኛ፣ ያለፈው ጦርነት ደም ሳይደርቅ ተመልሶ ወደሌላ ጦርነት መግባት የኢትዮጵያን ገፅታ በኣህጉርና በኣለማቀፍ ደረጃ የሚጎዳ ምንልባትም ከሽኣቢያ ብዙም በማይሻል የጦረኝነት ኣይን እንድትታይ የሚያደርግ ይሆናል።

የኢህኣዴግ መንግስት ከኣፍሪካም ሆነ ከታላላቅ ሃገሮች ኣክብሮትና ተሰሚነት በማግኘት በኩል ሽኣቢያን በተነፃፃሪነት ይበልጠዋል። ይህንን ብልጫ በመጠቀም ሽኣቢያ ወደ ሰላም እንዲመጣ ካልሆነም ከኢትዮጵያ ላይ እጁን እንዲያነሳ መጫን በሽኣቢያ ላይ የሚያሳድረው ውጤት (ዛሬ ባለበት የክስረት ደረጃ) በቀላል አይታይም። በተጨማሪም ሽኣቢያ ከኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ጋር ያለው ግንኙነት ቢቆረጥና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃይሎች ጤናማ ግንኙነት ውስጥ ቢገቡ በኢትዮጵያ ላይ ጉዳት ማድረስ ለሽኣቢያ ተራራ ይሆንበታል። ብዙ ተገናዛቢ ችግሮችም ይቃለላሉ። በህዝብና በህዝብ እንዲሁም በህዝብና በመንግስት መካከል ያለው ግንኙነት ከስከዛሬው በበለጠ ጤናማ ይሆናል። ሽብርተኝነት መዋቅሩን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመዘርጋት ኣዳጋች ይሆንበታል። በውጪ ኢትዮጵያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ኣካባቢ የሚታየው ተቃውሞ ይበተናል። በውስጥና በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን የልማት ተነሳሽነት ይሰፋል። ሰላምን ለሚረብሹ የውስጥ ችግሮች መፍትሄ እያስገኙ ሃገራዊ ጥቅምን ባስተዋለ ብሔራዊ ስሜት የሚካሄድው ዙሪያ መለስ ግንባታ ፈጣን ይሆናል። ይህ በእጃችን ላይ ያለና መተግበር ያለበት እርምጃ ነው።

በፓርላማ ውስጥና ውጪ ከተቃዋሚዎች ጋር ድርድር ይደረግ የሚል ጥያቄ መነሳቱን በጣም ተፈላጊ የሚያደርገውም ይህ ነው። «የግራጫውን/ሶስተኛውን» ኣማራጭ እወክላለሁ የሚለው የኢዴኣፓ-መድህን ፓርቲ በኣንድ የፓርላማ ተወካዩ ኣማካኝነት «ለመሆኑ መጀመሪያስ ነገር ተዋጊዎቹ ድርድር ይፈልጋሉ ወይ?» በማለት የድርድር ጥያቄን ከመደገፍ መራቁ የሚያሳፍርና ግምት ውስጥ የሚከት ነው። የሰላምና የድርድር ግብዣ የሚቀርበው ለግብዣው የታሰቡት ሃይሎች ድርድር መፈለግ ኣለመፈለጋቸው እየተጣራ እንዳልሆነ ኢዴኣፓ-መድህን ያጣዋል ብሎ ማመን የማይመስል ነው። ለኢህኣዴግም ከዚህ ቀደም ከኦነግና ከኦብነግ ጋር ድርድር ለማድረግ ተሞክሮ ኣለመሳካቱ ዛሬ ላለመሞከር ምክንያት መሆን ኣይችልም። ዛሬ፣ ሁለቱ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም ወደሰላም መድረክ እንዲገቡ መሳቢያ ነጥቦችን ኣዘጋጅቶ በይፋ መጥራትንና የምር ጥረት ማድረግን ሊተካው የሚችል ኣማራጭ የለም። ያልተሃደሶና ያለመላ ህዝብ ንቅናቄ በዚህ ሃገር ፈውስ የሚኖር ኣይመስልም። ይህ በህዝብ ተቀባይነት ሳያገኙ ኣይሆንም። ኣሁን በሚታየው ሁኔታ ደግሞ ተቀባይነትን ለመቀዳጀት ቀላሉ መንገድ በእርቅ ከመካረር መውጣት ነው።

ሃምሌ 9 ቀን በቅንጅት መሪዎችና በተያያዥነት በተከሰሱ ሌሎች ሰዎች ላይ የተሰጠው የፍርድ ውሳኔ አሳዛኝ ነበር። ውሳኔው በቴሌቪዥን ሲነገር ተከሳሾቹ ጥፋተኛ ነን ምህረት ይደረግልን ያሉበት ማመልከቻ ከነፊርማቸው እንዲታይ ቢደረግም መላው ህዝብ፣ ፈራጆቹ፣ የሞት ፍርድ የጠየቀባቸው ኣቃቤህግ፣ ራሳቸው ምህረት ጠያቂዎቹና ተጠያቂው መንግስት ጭምር ወንጀል እንዳልፈፀሙ ያቂታል። ከማግስቱ አንስቶ የ1997 የምርጫ ጊዜን እየነካኩ እንዲህ ብለው ነበር እየተባለ ጥፋተኛነታቸውን ለህዝብ ለማሳመን የቀረበውም ቅንብር ላም ባልዋለበት ኩበት ለመልቀም የጣረና የኣስተሳሰብ ነፃነትን ጉዳይ እንደወንጀል ተግባር ኣድርጎ የደረደረ የባዶ ባዶ ነበር። በጊዜው ኢህኣዴግ ድምፅ ያጭበረብራል፣የኢትዮጵያ ህዝብ ድምፄን አላሳርቅም ብሎ መታገል ኣለበት ማለታቸው ፖለቲካዊ አስተሳሰብና እውነት እንጂ ወንጀል አልነበረም። እንደተፈራውም

ሆኗል:: ድምፅ እንዳይሰረቅ መጠበቅም ይሁን በተቋማዊ መንገድ አልሳካ ሲል አደባባይ ድረስ ወጥቶ መታገል ነገም የሚኖር ህገመንግስቱ የፈቀደው መብት ነው:: የኢህኣዴግ መንግስት እንዲህ ያለ ዘላባጅ ፕሮፓጋንዳና ምህረት የማስጠየቅ ድራማ (**farce**) ውስጥ ከሚገባ ክሱን ኣቋርጦ ወደእርቅ ቢዞር ምንኛ ባማረበት ነበር::* ክስ ማቋረጥና መደራደር ከህግ የበላይነት ጋር ኣይቃረንም:: ይልቅስ የሚቃረነው ባልተሰራ ወንጀል ከሶና «ማስረጃ ኣቅርቦ» የእድሜ ልክ ቅጣት ለማስፈረድ መቻል ነው:: በረዳነው ልክ ካላዘዝን ለሚሉ ቦታ የለንም፣የውጪ ኢትዮጵያውያን የሰልፍ ጋጋታ ኣላሳሰበንም፣ የሽማገሌዎቹ ምልጃ ምላሽ ማግኘትም ከኣሜሪካ ምክርቤት ኣካሄድ ጋር ግንኙነት የለውም መባሉም እራስን ለማታለል ያህል ይሁን:: ድራማው ታሳሪዎቹን ከፖለቲካ ጨዋታ ውጪ ሳያደርግ ለመፈታት እስካበቃቸውና ወደ ፖለቲካዊ ድርድር እስከወሰደ ድረስ ግዴለም ይሁን:: የሽማግሌዎቹ ሽምግልናና የኢህኣዴግ ሆደሰፊነት በዚሁ እንደማያበቃ ተስፋችን ነው::

እዚህ ላይ የልደቱ አያሌውና ፓርቲው መግለጫዊ ዘመቻን ጤናቢስነት ማንሳት ግድ ይሆናል:: ለወደፊቱ የዲሞክራሲ ትግል ያሰበ መግለጫ እስረኞቹ ከተፈቱ መፈታት ያለባቸው መብታቸው ሳይገፈፍ መሆኑንና የኣጠቃላይ መግባባትን ኣስፈላጊነት በማመልከት ዙሪያ በተወሰነ ነበር:: እስረኞቹ የተወነጀሉበትን እንዳልፈፀሙትና ጥፋተኛ ነን ማለታቸውም ለመፈታት የተከፈለ መስዋእትነት መሆኑን እንኳን ሃበሻ ፈረንጆቹም የሚያቁት ነው:: እነልደቱ ግን በዚህ በሚቆጠቁጥ ሃቅ ላይ ቆመው «እነሱ ህገመንግስቱን ለማፍረስ በግልም በጋራ ተንቀሳቅሰናል ብለው ካመኑ እነሱ ካሉት አኪያ ነው መናገር ያለብን ... የኢትዮጵያን ህዝብ ጭምር ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው ... እኛ በፊትም ኣካሄዳችሁ ኣደገኛ ነው ብለን ነበር ...ማጣራቱ ባያረካቸው ወደፍርድ ቤት ለመሄድ ከተስማሙ በሁዋላ ወደኣመፅ መሄድ ኣልነበረባቸውም ...መገዳደል ደረሰ ... » እያሉ ወንጀለኛ በማስመሰል የፖለቲካ ቀብር በቶሎ አስፈፅሞ ከታሳሪዎቹ ጋር የነበረውን ሰፊ ድጋፍ ወደራስ በኩል ለማዞር ያደረጉት የመሸታ ንግድ እጅግ ወራዳ ነበር::

የቅንጅት መሪዎች ስህተቶች መፈፀማቸው ኣሌ የማይባል ነው:: የልደቱና ቡድኑ ስህተት ደግሞ የከፋ ነበር:: ቅንጅቶች ፍርድቤት ለመሄድ ፈርመው አለመሄዳቸው ወንጀል ኣይሆንባቸውም:: ፍርድቤትን ትተውም ወደ ኣመፅ ኣልሄዱም:: የወሰዱት የትግል መንገድ ከነድክመቱ ልደቱ እናካሂዳለን ሲለው ከነበረው ብርቱካናማ ኣቢዮት በጣም ያነሰ ነበር:: ልደቱ ብርቱካናማ የኣፍ መፈክሩን ልክና ሰላማዊ ሲል የነሱን «ኣመፅ» ብሎ መጥራቱ ለምን? ሰላማዊነቱን ማን እንዳሳጣው፣ እያነጣጠሩ መግደል እንጂ «መገዳደል» እንዳልነበረ እውነት ኣጥቶት? በዚህ ኣይነት ሞላጫነት የኢትዮጵያን ህዝብ ድጋፍ ኣገኛለሁ ተብሎስ እንደምን ታሰበ?

በ3ኛው ሺኛ ኣመት ዋዜማ ላይ ሆነን ኣድዋን በድምቀት ባከበርንበት ጊዜ የርስበርስ ቅራኔን ወደጎን ብሎ ባንድ ላይ ለሃገር ሆ ብሎ መነሳት የድል ማእዘን መሆኑን የኣሁኑ ትውልድ ከኣድዋ መማር እንዳለበት ተወስቶ ነበር:: በጣም በጣም ትክክል:: ለእነልደቱም የኣድዋ ልቦና ይስጣቸው:: ቅኝ ሊያደርገን የመጣውን ጣሊያንን በኣድዋ ጦርት ኣሳፍረናል:: ዛሬ ደግሞ በድህነትና በርስ በርስ ንችፊያ ማቅቀን እንድንቀር የሚሹትን ሁሉ ባንድነት ተነስተን ማሳፈር አለብን:: ላሚቱም ልጆቿ ለዚህ ጀግንነት እንዲሰባሰቡላት እየተጣራች ነው:: በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ሁለት ነገሮችን ያደርጋል ብለን እንጠብቃለን::

*1ኛ የሽኣቢያን ጠላትነት ከጦርነት በመለስ ለማስቆም የሚቻል መሆኑን ኣምኖ ማሳበቢያ የሆነውን የድንበር ውዝግብ በሰላም ለመጨረስ ጥረቱን ይቀጥላል፣*

---

* «በህግ ውስጥ ጣልቃ አልገባም» እየተባለ ከበስተጀርባ ገና ከመታሰራቸው ደጅ ሲጠኑ ለነበሩት ሽማግሎች፣ መንግስት እስረኞቹን ለመፍታት ይፈልግ የነበረው «በሰሩት ስህተት መፀፀታቸውን እንዲገልፁ ብቻ» እንደነበር(ማለትም ፍቺን ለፖለቲካዊ ግድያ ሊጠቀምበት በጧቱ ኣቅዶ እንደነበር ) ዛሬ ከፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ቃለመጠይቅ ለመገንዘብ በቃን:: (**Abbi Weekly** ሃምሌ 18 ፣1999፣ ገፅ 14) አመት ተኩል የተለፋበት እርቅ ከመጀመሪያው የተለየ ነገር አላመጣም::

ኣብሮም ከመርዘኛ ፕሮፓጋንዳ እስከ እጅ አዙር ወታደራዊ ጣልቃገብነትና ሽብር የረዘመውን ጥቃቱን ለኣለም በማቅረብ መግቻ እንዲያገኝ ይታገላል ብለን ተስፋ እናደርጋን። ከኤርትራ ህዝቦች ምሬት የመነጨና የውስጥና የውጪ ኤርትራውያን ሰፊ ድጋፍ ያለው ትግል መቀጣጠል ለሁለቱም ሃገር ህዝቦች የሚጠቅም ነው። ኢትዮጵያ ከደገፈች መደገፍ ያለበት ሽኣቢያን በፖለቲካ አንኮታኩቶ ለኤርትራውያን ትንሳኤ የሚሆንን ህዝባዊ ትግል ነው።

2ኛ/ ከላይኛው ተግባር ጎን ለጎን በሽኣቢያ የሚታገዙ ተቃዋሚዎችን ወደሰላማዊና ህጋዊ መድረክ እንዲመጡ **ከተሻለ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ጋር ከልብ** ይጥራል፣ ከእስር ከተፈቱት ጋር እጅ ለእጅ የሚያያይዝ ኣዲስ መንፈስ ይፈጥራል ብለን እንጠብቃለን። የኢህኣዴግ መንግስት ይህንን ከተገበረ እንደመንግስት ትልቅ ክብር ማግኘት ብቻ ኣይደለም፣ ተቃዋሚዎች ሬፈረንደም ካልተካሄደ/ያለው መንግስት ፈርሶ የጋራ መንግስት ካልተቋቋመ በማለት የሰላም ጥሪቱን ቢረግጡበትም ባይረግጡበትም የፖለቲካ ድል ያገኛል። ኢህኣዴግ ሰላምን ከመረጡት ጋር ተባብሮ የመልካም ኣስተዳደሩንና የኢኮኖሚ ግንባታውን እስካወቀበት ድረስ ከሰላም የሚያፈነግጡ ሃይሎች ተወግዘውና ተዘንግተው ለመጥፋት ይዳረጋሉ። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችም **ከመተላለቅ ስጋትና የበይ ተመልካች ሆንን ከሚል እምነት ወጥተው ከፊታቸው ኣስደሳች ህይወት እየመጣ መሆኑን ለማየት** እስከቻሉ ድረስ የክልል፣ የቋንቋና የባህል ልዩነትም ሆነ የነጣጣዮች ቅስቀሳ ሳይበግራቸው የሰለጠነችና የበለፀገች ሀገር ለመገንባት በወኔ መዋደቃቸው የማይቀር ነው።

የተቃዋሚዎች መጨረሻ በታሪክ ተረስቶ መቅረት ባይሆን ይመረጣል። ከሽኣቢያ ራሳቸውን እንዲያላቅቁና ከመተኮስ ወጥተው በሰላማዊ ትግል ለኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ዲሞክራሲና ብልፅግና እንዲሰሩ የብዙ ሰዎች ፍላጎት ነው። ከውጭ ሊገቡ የሚችሉትም ሆኑ በፓርላማው ውስጥ የሚገኙት ተቃዋሚዎች ከመቃወም ድርሻ ተሻግረው በግንባታው ተግባራዊ ጥረት ውስጥ እንዲገቡ ሰፊ ስርጭት ባለው የፓርቲ ጋዜጣና በሌላ መንገድ ከህዝብ ጋር እየተገናኙ የሃገራችንንና የዙሪያችንን ሁኔታ እንዲያስተነትኑና ለግንባታችን የሚበጁ ቁምነገሮችን እንዲያነጥሩ ይጠበቃሉ። ልማታችን ሁሉም ወገን ድግሴ የሚለው (በግርግር የማይጓተት) እንዲሆን በተቃዋሚዎች በኩል ያለው የድጋፍና የመቀስቀስ ኣቅም በሃገራዊ የልማት ርብርቡ ውስጥ መካተቱ ወሳኝ ነው።

በሃገራዊ መግባባት ውስጥ ኣማራጭ ሊሆን የሚችል ብስለትን፣ ብልህነትንንና ድርጅታዊ ጥንካሬን ያዳበረ የተቃዋሚ ፓርቲ መፈጠርንና ስልጣን ካለግርግር በምርጫ ሲተላለፍ ማየትን እንጓጓለን። ተቃዋሚዎቹ የጉጉታችን ተካፋይ ከሆኑ ኢህኣዴግ በሰላም አብሮ የመስራት ግብዣ ባያቀርብላቸው እንኳ አስቀድመው በሽኣቢያ ላይ ቁርጠኛ አቋም በመውሰድ እንደራደር እያሉ መወትወት ሃላፊነታቸው ነው። «ስርኣት ቀልባሾች»፣ «አንኮበራዊ» ምንትስ ለሚል ማጭበርበር የማይመች (የስልጣን ጥመኞች በጣም የሚፈሩትን) ብሄረ ብዙ ይዘት ያለው የትግል ህብረትና የፖለቲካ ብስለት ይዘው ከመጡ ጆሮ ለመንሳት ቢሞከር እንኳ እንዳይቻል የሚያደርግ ህዝባዊ ግለት መፍጠር ይችላሉ። ይህ ተሳክቶ የተፎካካሪ ፓርቲዎች በጠላትነት መተያየትና እርስ በርስ መሳለል የተረሳበት፣ ስልጣን ላይ የወጣ ወገን ተቃዋሚውን በመንግስታዊ የደህንነት ሃይል ለማዋከብ የማያስብበትና የማይደፍርበት፣ የህግ የበላይነት ከኣፍና ከተውኔት ይልቅ በተግባር የሚከበርበት፣ ተቃዋሚ የመገናኛ ብዙሃን ችግር ኣጋጠመኝ የማይልበት፣ ህዝብ ስለሃገሩ ለማወቅ ወደ ውጪ የዜና ማሰራጫዎች ወደሹክሹክታ የማይሮጥበትና ከውጪ በበለጠ የሀገሩን ማሰራጫ የሚያምንበት ጊዜ እንዲመጣ እንመኛለን።

# 4. መደምደሚያ

የምኞቶቻችን ተጨባጭነት «ሀ» ብሎ የሚጀምረው የኢትዮጵያ ችግሮች ባንድ ፓርቲ ገዢነትና መንከውከው ወይም ከዳር ቆሞ በማማረር ወይም በጠመንጃ ሃይል እንደማይቃለሉ ከማወቅ ነው። እስካሁን በ16 ኣመታት ውስጥ ኢህኣዴግ ብቻውን ዲሞክራሲን በመገንባት በኩል ያደረገው ጥረት የሚፈለገውን ያህል ውጤት ኣላስገኘም። የጠላትነት ፖለቲካ ህዝብ ድረስ ዘልቆ ማወኩ እድገት እያሳየ እንጂ እየቀነሰ ኣለመምጣቱና ሃሳብን በመግለፅ በኩል የነበረው ውስን ነፃነት በድህረ 1997 ምርጫ ወደሂላ መመለሱ የዚሁ ምስክር ነው። በጥላቻና በፍጥጫ መስክ ላይ ዲሞክራሲ ሊገነባ ኣይችልም። ኢህኣዴግ ከወደቀ ሃገሪቱ ትበታተናለች፣ የብሄር መጨፋጨፍ ይመጣል በሚል ፍርሃትና እምነት ላይ ዲሞክራሲ ሊገነባ አይችልም። ይህ ፍርሃት እንዲጠነክር የሚሹም ዲሞክራሲን ሊያጎለብቱ ኣይችሉም። በዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ሃይሎች ላይ ላዩን እየተሳሳቁም ሆነ በለየለት ጠላትነት ውስጥ ተጣምደው የሚገኙበት አጥፊ ሁኔታ መቀየር አለበት። በ1997 የምርጫ ጊዜ ኣከባቢ ይባል እንደነበረው የገዢ ፓርቲና የተቃዋሚዎች ኣብሮ መስራት ዛሬም ሲብዛ ኣስፈላጊ ነው። ኣብሮነት በስልጣን ላይም ቢገለፅ ጥሩ ይሆናል። ነገር ግን ኣብሮ የመስራት ቅድመ ግዴታ ሊሆን ኣይገባም።

በኣሁኑ ወቅት ከልዩነት ጋር ተቻችሎ ኣብሮ የመስራቱ ሂደት ካንድ ትልቅ ኮንፍራንስ ተነስቶ ኣላማው የሰፋ የፓርቲዎች የጋራ መድረክ በመፍጠር በሃገሪቱ ልዩ ልዩ ችግሮች ላይ በመመካከርና በመተጋገዝ ሊጀምር ይችላል። ቅርበታቸውን እያሻሻሉና ከህዝቦች ጋር እየተጣጣሙ እስከ 2002 ምርጫ ድረስ ብዙ ተግባር ሊያከናውኑ ጊዜ ኣላቸው። የ2002 ምርጫንም ከስልጣን መሻኮቻነት ይበልጥ ተባብረው የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታውን ለማሳካት የሚጓዙበትና የመላውን ሕዝብ ይሁንታ ያገኘ ርብርብ መክፈቻ ሊያደርጉት ይችላሉ።

የፖለቲካ ሃይሎች ኣብሮ መስራት ከጀመሩ ፀረዲሞክራሲያዊና ኣድላዊ የሆኑ ችግሮችንና ግርግሮችን ማቃለል ኣስቸጋሪ ኣይሆንም። ያንድ ፓርቲ ባህርይ በራሱ የውስጥ ማንነት ብቻ ሳይሆን በተቀናቀኙም ባህርይ የሚወሰን ነውና በጎ ግንኙነት የሁለት ወገን የጠባይ መሻሻልን ማስከተሉ ኣይቀርም። በብሄራዊ መግባባት ውስጥ እየተለያዩና እየተከራከሩ፣ እየተተቻቹና እየተራረሙ ህዝቦች በስሜት የሚሳተፉበት የዲሞክራሲ፣ የፍትህና የኢኮኖሚ ጉልህ እርምጃ ሊያቀጣጥሉ እንደሚችሉ ኣያጠራጥርም። ምክንያቱም በህዝቦች ውስጥ ሲታዩ የቆዩት የመሸካከር፣ የመፈራራትና የዝምታ ገፅታዎች ዞሮዞሮ ከፖለቲካ ቡድኖች የሚመነጩ ነበሩና የፓለቲካ ሃይሎች ኣብሮ መስራት በቀጥታ የብሄር ብሄረሰቦችን መተማመን ይዞ ይመጣል። ሌሎች ጥቅሞችም ይኖራሉ።

- የመንግስት ከግጭቶችና ከሁከቶች ጋር መሯሯጥ ይመናመናል።
- ከስልጣን ተፈጥፍጦ ላለመውደቅ የሚውለው ኣቅም ( ገንዘብ፣ ጉልበት፣ ኣእምሮና ጊዜ) ኣቅጣጫውን ቀይሮ በተሃድሶና በለውጥ ላይ ያተኩራል። ከዚህ ኣይነት የመንግስት ወጪ ጋር ተያይዞ ከሚመጣ የዋጋ ግሽበት ለመዳን ይቻላል። (በ1999 ለታየው የዋጋ ግሽበት የመንግስት የተስፋፋና የናረ የቢሮክራሲ፣የፀጥታ ፍጆታ በማተም/በብድር ገበያ ውስጥ የረጨው ብርና ለወራት የቆየው የሶማሊያ ውስጥ ወታደራዊ ዘመቻ የራሱ ጉልህ ድርሻ ኣለው።)
- በትምህርት ጥራት ውድቀት ላይ በወጣት አጥፊነት በእፅ ተገዥነትና በኤድስ ስርጭት ላይ ፈጣን መዳከም የሚያስከትል የለውጥ ስሜት ይያያዛል።
- የብሄር ወገንን በስልጣንና በሌላ ጥቅም ዙሪያ የማሰባሰብ ሩጫ ይቀንሳል። ደም መቃባት በሌለበት መንገድ ለቅሬታ ምንጭ የሆኑ ቡድናዊና ጎሰኛ የስልጣንና የቡጥቦጣ መረቦችን መፍትሄ ለመስጠት የተሻለ ሁኔታ ይፈጠራል።

- ፖለቲካዊ ኩርፊያ፣ ኣድላዊነትና የሚያስከትለው ቅሬታ፣ ከነዚህም የሚራባው ሙስና በጉልህ ይቀንሳል።
- ነጋዴው ዘራፊ ትርፍ ለማግኘትና ገቢውን ቡድን ኣንገላትቶ ለመጣል የዋጋ ንረትን ከመጠቀም ርቆ በሃገራዊ ራእይ ጤናማ የግብይይት ባህልን ወደማዳበር እንዲሄድ የሚያግዝ ህሊናዊ ሁኔታ ይፈጠራል።
- በመንግስት ቢሮክራሲ ውስጥ ኣልቻል ያለውን የነቀዝ ሹሞችና ምንዝሮች ህገወጥ ያገልግሎት ኪራይ መጣጭነት (በተለይም በመሬት ይዞታ በኩል) ለማዳከምና የተሻለ ስርኣት ውስጥ ለማስገባት የሚመች ፖለቲካዊ ኣቅም ይፈጠራል።
- ከከተማ እስከገጠር ያለው ግብርና ታክስ የመክፈል ፍላጎት በጉልህ ይሻሻላል።
- መንግስት ህዝብን ከሚደልሉ ፕሮጀክቶች ተላቆ ቀዳሚና ኣስፈላጊ በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ ለማተኮር ነፃ ይሆናል።
- የተቃውሞ ወገኖች ተሰግስገው እቅዴን እንዳያከሽፉብኝ በሚል ፍርሃት ካብአይገቤ የፖለቲካ ታማኞችን ከመለቃቀም ተወጥቶ ስራን፣ የሙያ ችሎታንና የስራ ስሜትን ለማገናኘት የሚስማማ ሁኔታ ይገኛል።
- ያንዱ ወይም የሌላው ታላቅ ሃገር ጫማ ላሽ ለመሆን የሚያጋልጥ ውስጣዊ የቀዋሚ ግፊት ኣለመኖር ከጎረቤትም ሆነ ከሩቅ ሃገራት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ከሃገር ግንባታ አኳያ እያስተዋሉ የመፈፀምን ልበሙሉነት ያስታጥቃል።
- የጥቂቶች ጠቅላይነት በሰፈነበት በኣለማችን ኢኮኖሚ(oligopoly capitalism) ውስጥ የሚታዩ ባዘቶዎችን ማለትም፦ የኣንበሳውን ድርሻ ከሚወስዱና ትክላቸውን (base) ኣሜሪካ፣ ኣውሮፓ/ጃፓን ካደረጉ ግዙፍ የኣለም ኩባንያዎች ጋር ተሰካክቶ ውሱን ትርፍ በመካፈል ኣለመርካት የሚፈጥረውን ፍትጊያ፣ በሃገራዊ/ በክፍለሀጉራዊና በኣህጉራዊ የኩባንያዎች ቅንብር ተቃናቃኝ ግዙፍ ኩባንያና የንግድ ምልክት ፈጥሮ ገበያ በመናጠቅ ትግል ውስጥ እየሆነ ያለውን (በቻይናና በምእራቡ፣ በኣውሮፓና በኣሜሪካ ለምሳሌ በበረራ ምህንድስና መስክ፣ በኣሜሪካና በሩሲያ ለምሳሌ የኢራንን ኣደገኝነት በመከላከል ሽፋን ቼክና ፖላንድ ላይ ሚሳኤል ጠምዶ በአውሮፓ-ሩሲያ መያያዝ መሃል የመሰንቀር ትግል)፣ ከዚህ በተቃራኒ ሃገራዊና ኣህጉር ነክ ስብሶቦሽን እየተሻገረና እየሰበረ የተፈጠረውና እየተፈጠረ ያለው ኣለማቀፋዊ የኩባንያዎች መያያዝ በትላልቅና በትናንሽ ሃገሮች ኢኮኖሚ ላይ በተለይም በኣፍሪካ ላይ የሚያሳድረውን ጫናና ለውጥ በሙሉ ንቃት እየተከታተሉና እየመረመሩ የሚያወጣ ኣካሄድን ለመቀየስ የተሻለ መረጋጋት ይገኛል።
- የውጪ ኢንቨስትመንት መሳብ የልመና ያህል የሆነበት ሁኔታ ለኣድርቆ-በረሮች ያጋልጣል። የፖለቲካ መረጋጋትና በህዝቦች የታቀፈ መንግስት ባለበት ግን የሃገርን ጥቅም የተሻለ ማስጠበቅ ይቻላል። የውጭ ባለሃብቶችን በሚኖራቸው የቆይታ ርዝማኔ፣ ባላቸው ውጥን፣ በካፒታል ኣቅማቸው፣ በሚያስገቡት ቴክኖሎጂ ተፈላጊነት፣ ባላቸው ነባር ዝና ሁሉ የመምረጥ እድሉ (ስኬታማና ኣዋጪ የሆኑትን ከማገዝና ከመንከባከብ ጋር) ይዳብራል። ስሙን «ብልህነት»/«ምንተፋ» ወይም «ግፍ» በሉት የቅርቦቹን እሲያውያን ጨምሮ በ«ንፁህ» ንግድ የከበረ ሃገር በኣለም የለም። የሚታለል ባለበት ኣታላይ ይኖራልና ዛሬም ነገም ንቁ መሆን የግድ ይለናል። ሰላምና ሃገራዊ መግባባት ለዚህ ይበጃል።
- የሃገር ውስጥ ኩባንያዎቻችንም ሙስናን ከመቆጣጠር ገበያን ከማግኘት፣ ከማዝለቅና ከማስፋት ጥረትና ሴኬታማነታቸው ጋር መንግስታዊ ድጎማና ድጋፍን በማያያዝ ጊዜው የሚጠይቀው እድገት ላይ እንዲደርሱ መታገል፤ እንዲሁም
- ጥራት የለሽና ብልሹ ምርቶች ወደውጪ ገበያ ሾልከው መጥፎ ስም የማያመጡበት፣ የውስጥ ሸማቹም የዚህ ኣይነት የውስጥና የውጪ ምርቶች ማጣሪያ የማይሆንበትን ተከባሪ ስርኣት መዘርጋት የማይቀር ይሆናል።

ብሎልን የፖለቲካው ሃይሎች የላሟን እምቧ እምቧ ሰምተውና እርቅ ኣውርደው ለኣዲስ ህይወት ግንባታ እጅ ለእጅ ከተያያዙ፣ ከኤርትራ ጋር ያለን ጣጣ በዘዴ ካለቀና በኣፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሰላምና የመረጋጋት ንፋስ እየጨመረ ከሄደ የሺኛ በኣላችን የኣፍሪካ በኣልነት ትርጉም ይኖረዋል። እውነትም፣ ቅራኔን ኣቻችሎ ክንድ መግጠምን ከኣድዋ መማራችንን እናረጋግጣለን። በ1999 ኣድዋ ላይ ያስቀመጥነው የመሰረት ድንጋይም መታሰቢያነቱ ላለፈው ድል ብቻ ሳይሆን ለዛሬም ይሆናል። በኣዲስ ህይወት ግንባታ የምናገኘውም ስኬታማነት የመላው ኣፍሪካ ኩራት ይሆናል።

እስካሁን የተባለውን ብዙዎች እንደሚጋሩት ይገመታል። የተሻለ ኣማራጭ ያላቸው ይተንፍሱ። ሁሉም ዝም ዝምን ከወደደና ኢህኣዴግ በብቻ ጉዞው ከቀጠለ ዘርፈብዙ የልማት ትግላችን ቅዝቃዜ ይበዛበታል። ኣስጊ ሁኔታዎችም ኣይወገዱም። ይህን እውነት ሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች እንዲረዱ ቸር ልቦና ይስጣቸው። ቀላሉ እርቅ ምናልባት በግትርነት ምኞት ሆኖ ቢቀር እንኳ ኣንዲት ነገር። የሰው ልጅ በረዥም ታሪኩ ውስጥ ከኢኮኖሚ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ብዙ ነውሮች ፈፅሟል። ከሁሉ ግን ሮማውያን መሰላቸውን ፍጡር(ግላዲያተሮችን) እርስ በርስና ከእንስሳት ጋር እያጋጠሙ መዝናኛ ካደረጉበት ተግባር ቀጥሎ የሰው ልጅ በኣውሮፓዊነቱና በጀርመንነቱ ብቻ ሳይሆን <u>በሰው ልጅነቱ</u> እጅግ የሚያፍርበት ወራዳነት የተፈፀመው በጅምላ ጥላቻ ይሁዶችን እንደኣይጥ መመራመሪያ እያደረጉና እያጋዩ ለመጨረስ የተካሄደው የሁለተኛ ው ኣለም ጦርነት የናዚዎች እብደት ነው። ኣለም ግን ይህ ኣይነቱ እብደት ዳግም እንዳይከሰት ቁርጠኛ ዝግጁነት ያደረገ ኣይመስልም። በሰርቦችና በኮሰቮዎች መሀል የጥላቻ ጭፍጨፋ ተፈፅሟል። በሩዋንዳ የሆነውን እናውቃለን። በኛም ሃገር በስልጣን ለመቆየትም ሆነ ከስልጣን ለመፈንቀል የጥላቻ ፕሮፓጋንዳን በመጠቀምና ለጥላቻ መብቀያ የሚሆኑ ሁኔታዎችን በመፍጠር የመጨፋጨፍ እድልን ማልማት ከተጀመረ ውሎ ኣድሮዋል። የጥፋት ብልጭታዎቹም ታይተዋል። እናም ሌላው ቢቀር በጅምላ ጥላቻ የመጨፋጨፍ እብደት እንዳይበላን ሲባል ፖለቲካዊ ጨዋነት እንዲጀመር ተማፅኗችን ነው። ሁላችንም በሃገር ውስጥና በውጪ በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች እየተወያየንና ድምፃችንን እያሰማን (ሽማገሌዎችም ከውስጥና ከውጪ ተጨምረውበት) ሁለቱንም የፖለቲካ ወገኖች ሳንታክት ለመጎትጎት ብርታቱን ይስጠን።